# ዮሐንስ የጻፈው

# የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል

## መግቢያ

የዮሐንስ ወንጌል ኢየሱስን የሚያቀርበው ሥጋ ለብሶ በሰዎች መካከል እንደተገኘ ሕያው የእግዚአብሔር ቃል አድርጎ ነው ፤ መጽሐፉ ራሱ እንደሚገልጠው ፥ ይህ ወንጌል የተጻፈው አንባቢዎች ኢየሱስ አዳኝ ሆኖ ይመጣል የተባለው የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን እንዲያምኑና በእርሱም በማመናቸው ምክንያት የዘላለም ሕይወት እንደሚኖራቸው እንዲረዱ ነው (20፥31) ።

የወንጌሉ መጀመሪያ ክፍል ዘላለማዊ የሆነው የእግዚአብሔር ቃልና ኢየሱስ አንድ መሆናቸውን በመግቢያ መልክ ካቀረበ በኋላ ፥ ኢየሱስ አዳኝ ሆኖ ይመጣል የተባለው የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን የሚያሳዩትን ልዩ ልዩ ተአምራት ያቀርባል ፤ ከዚያም ከእነዚህ ተአምራት ምን ውጤት እንደተገኘ የሚያስረዱት ታሪኮች ይከተላሉ ፤ ይህኛው ክፍል የሚተርከው አንዳንድ ሰዎች በኢየሱስ አምነው የእርሱ ተከታዮች ስለመሆናቸው ፥ ሌሎች ደግሞ እንዴት እንደተቃወሙትና በእርሱ አናምን እንዳሉ ነው ፤ ከምዕራፍ 13-17 ኢየሱስ በተያዘበት ምሽት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ምን ያህል የጠበቀ ግንኙነት እንደነበረውና በስቅለቱም ዋዜማ የመዘጋጀትና የመጽናናት ቃል እንዳሰማቸው ይናገራሉ ። የመጨረሻዎቹ ምዕራፎች ስለ ኢየሱስ መያዝና ለፍርድ መቅረብ ፥ ስለ ስቅለቱና ትንሣኤው ፥ እንዲሁም ከትንሣኤው በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ ስለ መገለጡ የሚያወሱ ናቸው ።

ስታመነዝር የተያዘችው ሴት ታሪክ (8፥1-11) በቅንፍ ውስጥ የተቀመጠው ብዙዎች ቅጂዎችና የጥንት ትርጉሞች ስለማይጨምሩት ፥ ሌሎች ደግሞ በሌላ ቦታ ስለሚያስገቡት ነው ።

ዮሐንስ ጐላ አድርጎ የሚያሳየው በክርስቶስ በኩል ስለሚገኘው የዘላለም ሕይወት ነው ፤ ይህ በስጦታ የሚገኘው የዘላለም ሕይወት የሚጀምረው በአሁን ሕይወት ሲሆን የዚህ ሕይወት ባለቤት የሚሆኑት ኢየሱስ መንገድ ፥ እውነትና ሕይወት መሆኑን የሚያረጋግጡ ናቸው ፤ የዮሐንስን ወንጌል ልዩ የሚያደርገው መንፈሳዊ እውነቶችን ለማስረዳት የተለመዱና በዕለታዊ ኑሮ የምንጠቀምባቸውን ፥ ማለትም እንደ ውሃ ፥ እንጀራ ፥ ብርሃን ፥ እረኛ ፥ በጎች ፥ የወይን ተክልና የወይን ፍሬ የመሳሰሉ ነገሮች በምሳሌ መጠቀሙ ነው ።

---

## ምዕራፍ 1

### የሕይወት ቃል

1 ቃል በመጀመሪያ ነበረ ፤ ቃልም በእግዚአ
ብሔር ዘንድ ነበረ ፤ ይህም ቃል እግዚአብሔር
ነበረ ። 2 እርሱ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር
ዘንድ ነበረ ። 3 ሁሉ ነገር በእርሱ ተፈጠረ ፤
ከተፈጠረው ሁሉ ፥ አንድም ነገር ያለ እርሱ
የተፈጠረ የለም ። 4 በእርሱ ሕይወት ነበረች ፤
ይህች ሕይወት የሰዎች ብርሃን ነበረች ። 5 ብር
ሃን በጨለማ ያበራል ፤ ጨለማ ብርሃንን ከቶ
አያሸንፈውም ።
6 ከእግዚአብሔር የተላከ ዮሐንስ የሚባል
አንድ ሰው ነበረ ፤ 7 በእርሱ ምስክርነት ሰው
ሁሉ እንዲያምን ስለ ብርሃን ምስክር ሆኖ
መጣ ። 8 እርሱ ስለ ብርሃን ሊመሰክር መጣ
እንጂ እርሱ ራሱ ብርሃን አልነበረም ። 9 ይህ
ብርሃን ወደ ዓለም የሚመጣና ለሰው ሁሉ ብር
ሃን የሚሰጥ እውነተኛ[*] ብርሃን ነበረ ።
10 እርሱም በዓለም ነበረ ፤ ዓለምም የተፈጠ
ረው በእርሱ ነው ፤ ዓለም ግን አላወቀውም ።
11 ወደ ወገኖቹ መጣ ወገኖቹ ግን አልተቀበሉ
ትም ። 12 ይሁን እንጂ ለተቀበሉትና በስሙ
ላመኑ ፥ የእግዚአብሔር ልጆች የመሆንን
መብት ሰጣቸው ። 13 እነርሱም ከእግዚአብሔር
ተወለዱ እንጂ ከሰው ዘር ፥ ማለትም ከሥጋ
ልማድ ወይም ከሰው ፈቃድ አልተወለዱም ።
14 ቃልም ሥጋ ሆነ ፤ ጸጋንና እውነትንም
ተመልቶ በእኛ አደረ ፤ አንድ ልጅም ከአባቱ
ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን ።

---

[*] 1፥9 እውነተኛ ፦ የሐሰት ተቃራኒ ብቻ ሳይሆን ፥ የእግዚአብሔርንም እውነተኛነት የሚገልጥ ነው (ዮሐ. 14፥6) ።
1፥6 ፦ ማቴ. 3፥1 ፤ ማር. 1፥4 ፤ ሉቃ. 3፥1-2 ።





15 ዮሐንስም "ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ
ይበልጣል ፤ ምክንያቱም ከእኔ በፊት ነበረ ብዬ
የነገርኋችሁ እንሆ ይህ ነው" እያለ መሰከረ ።
16 ከእርሱ የጸጋ ሙላት እኛ ሁላችን በጸጋ
ላይ ጸጋ ተቀብለናል ። 17 ሕግ በሙሴ በኩል
ተሰጠ ፤ ጸጋና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ
በኩል ተሰጠ ። 18 እግዚአብሔርን ያየው ከቶ
ማንም የለም ፤ ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር
አብ ዘንድ ያለው አንድ ልጁ ብቻ ገልጦታል ።

### የአጥማቂው ዮሐንስ ምስክርነት

(ማቴ. 3፥1-12፤ ማር. 1፥1-8፤ ሉቃ. 3፥1-8)

19 አይሁዳውያን ባለሥልጣኖች ከኢየሩሳ
ሌም ካህናትንና ሌዋውያንን ወደ ዮሐንስ
ልከው "አንተ ማንነህ?" ብለው ባስጠየቁት
ጊዜ ፥
20 ዮሐንስ "እኔ መሲሕ አይደለሁም" ሲል
መሰከረ እንጂ አልካደም ።
21 እነርሱም "ታዲያ አንተ ማን ነህ? ኤል
ያስ ነህን?" ሲሉ ጠየቁት ።
እርሱም "አይደለሁም" ሲል መለሰላቸው ።
እነርሱም "ይመጣል የተባለው ነቢይ
ነህን?" አሉት ።
እርሱም "አይደለሁም" አለ ።
22 እነርሱም "ታዲያ አንተ ማን ነህ? ለላ
ኩን ሰዎች መልሱን እንድንነግር ፥ ስለ ራስህ
ምን ትላለህ?" አሉት ። 23 እርሱም "ነቢዩ
ኢሳይያስ እንደተናገረው ፤
እኔ 'የእግዚአብሔርን መንገድ አቅኑ'
እያለ
በበረሓ የሚጮኽ ሰው ድምፅ ነኝ"
አለ ።
24 ሰዎቹ የተላኩት ከፈሪሳውያን ነበረ ፤
25 ስለዚህ "አንተ መሲሕ ወይም ኤልያስ
ወይም ይመጣል የተባለው ነቢይ ካልሆንህ
ታዲያ ስለምን ታጠምቃለህ?" ሲሉ ጠየቁት ።
26 ዮሐንስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፥
"እኔ የማጠምቀው በውሃ ነው ፤ ነገር ግን እና
ንተ የማታውቁት በመካከላችሁ ቆሞአል ።
27 እርሱ ከእኔ በኋላ የሚመጣ ነው ፤ እኔ የጫ
ማውን ማሰሪያ ለመፍታት እንኳ የበቃሁ አይደ
ለሁም ።"
28 ይህ ሁሉ የሆነው ዮሐንስ ያጠምቅ በነበረ
በት ስፍራ በቢታንያ ነው ፤ ቢታንያ ከዮርዳኖስ
ወንዝ ማዶ የምትገኝ ከተማ ናት ።

### የእግዚአብሔር በግ

29 በማግሥቱ ዮሐንስ ኢየሱስን ወደ እርሱ
ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ ፥ "እነሆ የዓለምን
ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ይህ
ነው! 30 'ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ ይበል
ጣል ፤ ምክንያቱም ከእኔ በፊት ነበረ' ያልኋ
ችሁ ይህ ነው ። 31 እኔም ራሴ አላውቀውም
ነበር ፤ ነገር ግን እርሱ ለእስራኤል ሕዝብ እን
ዲገለጥ እኔ በውሃ እያጠመቅሁ መጣሁ ።"
32 ቀጥሎም ዮሐንስ እንዲህ ሲል መሰከረ ፥
"መንፈስ ቅዱስ እንደ ርግብ ከሰማይ ሲወርድና
ሲያርፍበት አየሁ ፤ 33 እኔ ራሴ አላውቀውም
ነበር ፤ ነገር ግን በውሃ እንዳጠምቅ የላከኝ
'መንፈስ ቅዱስ ሲወርድና ሲያርፍበት የምታ
የው ፥ በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ እርሱ
ነው' ሲል ነግሮኛል ። 34 እኔም ይህን አይቻ
ለሁ ፤ ስለዚህ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆ
ኑን እመሰክራለሁ ።"

### የመጀመሪያዎቹ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት

35 በማግሥቱ ዮሐንስ ከሁለት ተማሪዎቹ
ጋር እንደገና እዚያ ቆሞ ነበር ፤ 36 ዮሐንስ ኢየ
ሱስን በዚያ ሲያልፍ አይቶ "እነሆ የእግዚአብ
ሔር በግ!" አለ ።
37 ሁለቱ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ዮሐንስ
ይህን ሲል ሰምተው ኢየሱስን ተከተሉት ።
38 ኢየሱስ መለስ ብሎ ሲከተሉት አየና "ምን
ትፈልጋላችሁ?" አላቸው ።
እነርሱም "ረቢ! የምትኖረው የት ነው?"
አሉት ። (ረቢ ማለት መምህር ማለት ነው ።)
39 እርሱም "ኑና እዩ" አላቸው ። ስለዚህ
ሄዱና የት እንደሚኖር እዩ ። በዚያን ቀን ከእ
ርሱ ጋር አብረው ዋሉ ፤ ጊዜው ወደ ዐሥር
ሰዓት ገደማ ነበር ።
40 ዮሐንስ የተናገረውን ቃል ሰምተው ኢየ
ሱስን ከተከተሉት ደቀ መዛሙርት አንዱ የስም
ዖን ጴጥሮስ ወንድም እንድርያስ ነበር ። 41 እን
ድርያስ በመጀመሪያ ወደ ወንድሙ ወደ ስም
ዖን ሄደና "መሲሕን እኮ አገኘነው!" አለው ።
(መሲሕ ማለት ክርስቶስ ማለት ነው ።) 42 ከዚህ
በኋላ እንድርያስ ስምዖንን ወደ ኢየሱስ አመ
ጣው ።
ኢየሱስም ትኵር ብሎ ተመለከተውና
"አንተ የዮና ልጅ ስምዖን ነህ ፤ ከእንግዲህ
ወዲህ ግን ኬፋ ትባላለህ" አለው ። (ኬፋ
ማለት ጴጥሮስ ወይም አለት ማለት ነው ።)

### ኢየሱስ ፊልጶስንና ናትናኤልን ጠራ

43 በማግሥቱ ኢየሱስ ወደ ገሊላ ለመሄድ
ፈለገ ፤ ፊልጶስንም አገኘውና "ተከተለኝ"
አለው ። 44 ፊልጶስ እንደ እንድርያስና እንደ
ጴጥሮስ የቤተ ሳይዳ ከተማ ሰው ነበረ ። 45 ፊል
ጶስ ናትናኤልን አግኝቶ "ሙሴ በሕግ መጽ
ሐፍ ፥ ነቢያትም በትንቢት መጻሕፍት ስለ
እርሱ የጻፉለትን አገኘነው ፤ እርሱም የዮሴፍ
ልጅ የናዝሬቱ ኢየሱስ ነው" አለው ።

---

1፥21 ፦ ዘዳ. 18፥15 ፥18 ፤ ሚል. 4፥5 ። 1፥23 ፦ ኢሳ. 40፥3 ።

46 ናትናኤል ግን "ከናዝሬት መልካም ነገር
ከቶ ሊገኝ ይችላልን?" አለው ።
ፊልጶስም "መጥተህ እይ" አለው ።
47 ኢየሱስ ናትናኤል ወደ እርሱ ሲመጣ
አይቶ "እነሆ ተንኰል የሌለበት እውነተኛ የእ
ስራኤል ሰው!" ሲል ስለ እርሱ ተናገረ ።
48 ናትናኤልም "እንዴት አወቅኸኝ"
አለው ።
ኢየሱስም "ፊልጶስ ሳይጠራህ በፊት ከበለስ
ዛፍ ሥር ሆነህ አይቼሃለሁ" ሲል መለሰለት ።
49 በዚህ ጊዜ ናትናኤል "መምህር ሆይ!
አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ! አንተ የእስራ
ኤል ንጉሥ ነህ!" አለ ።
50 ኢየሱስም እንዲህ አለ ፥ "አንተ ያመን
ኸው 'ከበለስ ዛፍ ሥር ሆነህ አይቼሃለሁ' ስላል
ሁህ ነውን? ከዚህ የበለጡ ነገሮች ገና ታያለህ ።
51 እውነት ፥ እውነት እላችኋለሁ ፥ ሰማይ ሲከ
ፈት የእግዚአብሔር መላእክትም በሰው ልጅ
ላይ ሲወጡና ሲወርዱ ታያላችሁ ።"

## ምዕራፍ 2

### ኢየሱስ በገሊላ ቃና በሠርግ ግብዣ ላይ

1 በሦስተኛው ቀን በገሊላ ክፍለ ሀገር በምት
ገኘው ቃና በምትባል ከተማ ሠርግ ነበረ ፤ የኢ
የሱስ እናትም በዚያ ነበረች ። 2 ኢየሱስና ደቀ
መዛሙርቱም ወደ ሠርጉ ተጠርተው ነበር ።
3 በሠርጉ ግብዣ ላይ የወይን ጠጅ ባለቀ ጊዜ
የኢየሱስ እናት ኢየሱስን "የወይን ጠጅ የላቸ
ውም እኮ!" አለችው ። 4 ኢየሱስም "አንቺ
ሴት! ከአንቺ ጋር ምን አለኝ? ጊዜዬ ገና አል
ደረሰም እኮ" አላት ።
5 በዚያን ጊዜ እናቱ እዚያ ለነበሩት አገል
ጋዮች "እርሱ የሚላችሁን አድርጉ አለቻ
ቸው ።"
6 አይሁዳውያን የመንጻት ሥርዓት ስለነበራ
ቸው ስድስት የድንጋይ ጋኖች በዚያ ነበሩ ፤
እያንዳንዱ ጋን ሁለት ወይም ሦስት እንስራ
ውሃ ለመያዝ ይችል ነበር ። 7 ኢየሱስ አገልጋዮ
ቹን "ጋኖቹን ውሃ ሙሉአቸው" አላቸው ፤
እነርሱም እስከ አፋቸው ሞሉአቸው ። 8 ከዚህ
በኋላ ኢየሱስ አገልጋዮቹን "በሉ አሁን ቀድታ
ችሁ ለግብዣው ኀላፊ ስጡት" አላቸው ። እነ
ርሱም ወስደው ሰጡት ። 9 የግብዣው ኀላፊ
ወደ ወይን ጠጅ የተለወጠውን ውሃ በቀመሰ
ጊዜ ከየት እንደመጣ አላወቀም ፤ ውሃውን የቀ
ዱት አገልጋዮች ግን ያውቁ ነበር ። ስለዚህ የግ
ብዣው ኀላፊ ሙሽራውን ጠርቶ እንዲህ
አለው ፤ 10 "ሰው ሁሉ አስቀድሞ የሚያቀር
በው ጥሩውን የወይን ጠጅ ነው ፤ ተጋባዦቹ
ከሰከሩ በኋላ መናኛውን ያቀርባል ፤ አንተ ግን
ጥሩውን የወይን ጠጅ እስከ አሁን አቆየህ ።"
11 ኢየሱስ ይህን የተአምራት ሁሉ መጀመ
ሪያ የሆነውን ተአምር በገሊላ ክፍለ ሀገር
በቃና ከተማ አደረገ ፤ በዚህም ዐይነት ክብሩን
ገለጠ ፤ ደቀ መዛሙርቱም በእርሱ አመኑ ።
12 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ከእናቱና ከወንድ
ሞቹ ፥ ከደቀ መዛሙርቱም ጋር ወደ ቅፍርና
ሆም ወረደ ፤ በዚያም ጥቂት ቀኖች ተቀመጠ ።

### ኢየሱስ በቤተ መቅደስ የሚነግዱትን አስወጣ
(ማቴ. 21፥12-13፤ ማር. 11፥15-17፤
ሉቃ. 19፥45-46)

13 የአይሁድ ፋሲካ በዓል ቀርቦ ስለ ነበር
ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ ፤ 14 በቤተ መቅደ
ስም በሬዎችንና በጎችን ፥ ርግቦችንም የሚሸጡ
ትን ሰዎች አገኘ ፤ ገንዘብ ለዋጮችንም ገንዘብ
በመለወጥ ላይ እንዳሉ አገኘ ። 15 በዚህ ጊዜ የገ
መድ ጅራፍ አበጅና ሰዎችን ሁሉ ፥ በጎችንና
በሬዎችንም ከቤተ መቅደስ አስወጣቸው ፤ የገን
ዘብ ለዋጮችንም ገንዘብ በተነ ፤ ጠረጴዛዎቻቸ
ውንም ገለበጠ ። 16 ርግብ የሚሸጡትንም
ሰዎች "ይህን ሁሉ ወዲያ ውሰዱ ፤ የአባቴን
ቤት የንግድ ቤት አታድርጉት" አላቸው ።
17 በዚህ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ "ስለ ቤትህ
ያለኝ ቅንአት እንደ እሳት አቃጠለኝ" ተብሎ
እንደተጻፈ አስታወሱ ።
18 ከዚህ በኋላ አይሁዳውያን ባለሥልጣኖች
ኢየሱስን "አንተ ይህን ለማድረግ መብት እንዳ
ለህ ምን ተአምር ታሳየናለህ?" አሉት ።
19 ኢየሱስም "ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱ
ትና እኔ በሦስት ቀን እሠራዋለሁ" አላቸው ።
20 እነርሱም "ይህን ቤተ መቅደስ ለመሥ
ራት አርባ ስድስት ዓመት ፈጅቶአል ፤ ታዲያ
አንተ በሦስት ቀን ውስጥ ትሠራዋለህን?"
አሉት ።
21 ኢየሱስ ግን "ቤተ መቅደስ" ብሎ የተና
ገረው ስለ ሰውነቱ ነበር ። 22 ስለዚህ ኢየሱስ
ከሞት በተነሣ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ይህን አስ
ታወሱ ፤ በዚህ ምክንያት በመጽሐፍ የተጻፈው
ንና ኢየሱስ የተናገረውን ቃል አመኑ ።
23 ኢየሱስ በፋሲካ በዓል ጊዜ በኢየሩሳሌም
ሳለ ያደረጋቸውን ተአምራት በማየታቸው ብዙ
ሰዎች በእርሱ አመኑ ። 24 ኢየሱስ ግን ሰዎችን
ሁሉ ያውቅ ስለነበር አላመናቸውም ፤ 25 እርሱ
በሰው ልብ ያለውን ሁሉ ያውቅ ስለነበር ስለ
ሰው ማንም እንዲነግረው አያስፈልገውም
ነበር ።

1፥51 ፦ ዘፍ. 28፥12 ። 2፥12 ፦ ማቴ. 4፥13 ። 2፥13 ፦ ዘጸ. 12፥1-27 ። 2፥17 ፦ መዝ. 69፥9 ።
2፥19 ፦ ማቴ. 26፥61 ፤ 27፥40 ፤ ማር. 14፥58 ፤ 15፥29 ።



## ምዕራፍ 3

### ኢየሱስና ኒቆዲሞስ

1 ኒቆዲሞስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ ፤
እርሱ ከፈሪሳውያን ወገን የሆነ የአይሁድ አለቃ
ነበረ ። 2 ይህ ሰው በሌሊት ወደ ኢየሱስ መጥቶ
"መምህር ሆይ! እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር
ካልሆነ በቀር እነዚህን አንተ የምታደርጋቸውን
ተአምራት ሊያደርግ የሚችል ማንም የለም ፤
ስለዚህ አንተ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣህ
መምህር እንደሆንህ እናውቃለን" አለው ።
3 ኢየሱስም "እውነት ፥ እውነት እልሃለሁ ፤
ሰው እንደገና ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔ
ርን መንግሥት ሊያይ አይችልም" አለው ።
4 ኒቆዲሞስም "ታዲያ ሰው ከሸመገለ በኋላ
እንዴት ሊወለድ ይችላል? ዳግመኛ ወደ እናቱ
ማሕፀን ገብቶ መወለድ ይችላልን?" ሲል
ጠየቀ ።
5 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ ፥ "እውነት ፥
እውነት እልሃለሁ ፥ ሰው ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ
ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት
ሊገባ አይችልም ። 6 ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው ፤
ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው ። 7 ስለዚህ 'ዳግ
መኛ መወለድ ያስፈልጋችኋል' ስላልኩህ አትደ
ነቅ ። 8 ነፋስ ወደ ፈለገው አቅጣጫ ይነፍሳል ፤
ድምፁንም ትሰማለህ ነገር ግን ከየት እንደሚመ
ጣና ወዴትም እንደሚሄድ አታውቅም ፤ ከመን
ፈስ የተወለደ ሁሉ እንዲሁ ነው ።"
9 ኒቆዲሞስም "ይህ እንዴት ሊሆን ይች
ላል?" ሲል ጠየቀው ።
10 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት ፥
"አንተ የእስራኤል መምህር ሆነህ ይህን አታው
ቅምን? 11 እውነት ፥ እውነት እልሃለሁ ፥ የምና
ውቀውን እንናገራለን ፤ ያየነውንም እንመሰክራ
ለን ፤ እናንተ ግን ምስክርነታችንን አትቀበሉ
ትም ። 12 የምድርን ነገር ስነግራችሁ የማታምኑ
ከሆነ ፥ የሰማይን ነገር ስነግራችሁ እንዴት
ታምናላችሁ? 13 ከሰማይ ከወረደው ከሰው ልጅ
በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም ።[2*]
14 "ሙሴ በበረሐ እባብን ከፍ አድርጎ እንደ
ሰቀለ እንዲሁም የሰው ልጅ ከፍ ብሎ ሊሰቀል
ይገባዋል ። 15 ምክንያቱም በእርሱ የሚያምን
ሁሉ የዘላለምን ሕይወት እንዲያገኝ ነው ።
16 "እግዚአብሔር ዓለምን እጅግ ስለ ወደደ
አንድ ልጁን ሰጠ ፤ ስለዚህ በልጁ የሚያምን
ሁሉ የዘላለም ሕይወት ይኖረዋል እንጂ አይጠ
ፋም ። 17 እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም የላ
ከው ፥ ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓ
ለም ላይ ለመፍረድ አይደለም ።
18 "በእርሱ የሚያምን አይፈረድበትም ፤ በእ
ርሱ የማያምን ግን አንድ በሆነው በእግዚአብ
ሔር ልጅ ስላላመነ ገና ዱሮ ተፈርዶበታል ።
19 "ፍርዱም ይህ ነው ፥ ብርሃን ወደ ዓለም
መጣ ፤ ሰዎች ግን ሥራቸው ክፉ ስለሆነ ከብር
ሃን ይልቅ ጨለማን ወደዱ ። 20 ክፉ ነገር የሚ
ያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላል ፤ ክፉ ሥራውም
እንዳይገለጥበት ወደ ብርሃን አይመጣም ።
21 እውነት የሆነውን ነገር የሚያደርግ ግን ወደ
ብርሃን ይመጣል ፤ ወደ ብርሃን የሚመጣውም
በእግዚአብሔር ትእዛዝ መሠረት የተደረገው
ሥራው እንዲገለጥለት ነው ።"

### ኢየሱስና አጥማቂው ዮሐንስ

22 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ
ጋር ወደ ይሁዳ አገር ሄደ ፥ በዚያም እያጠመቀ
ከእነርሱ ጋር ለጥቂት ጊዜ ቆየ ። 23 በዚያን ጊዜ
ዮሐንስም ብዙ ውሃ ስለነበረበት በሳሌም አቅራ
ቢያ ሄኖን በተባለ ስፍራ ያጠምቅ ነበር ፤ ሰዎ
ችም ወደዚያ እየሄዱ ይጠመቁ ነበር ። 24 በዚ
ያን ጊዜ ዮሐንስ ገና ወደ ወህኒ ቤት አልገባም
ነበር ።
25 በዚያን ጊዜ በዮሐንስ ደቀ መዛሙርትና
በአንድ አይሁዳዊ[3*] መካከል ስለ መንጻት ሥር
ዓት ክርክር ተነሣ ። 26 የዮሐንስ ደቀ መዛሙ
ርት ወደ ዮሐንስ ቀርበው "መምህር ሆይ! ያ
ከዮርዳኖስ ማዶ ከአንተ ጋር የነበረው ፥ አንተ
ስለ እርሱ የመሰከርክለት ፥ እነሆ እርሱም ያጠ
ምቃል ፤ ሰዎችም ሁሉ ወደ እርሱ ይሄዳሉ"
አሉት ።
27 ዮሐንስም እንዲህ ሲል መለሰ ፥ "ማንም
ሰው እግዚአብሔር ካልሰጠው በቀር ምንም
ነገር ሊኖረው አይችልም ፤ 28 'ከእርሱ በፊት
ተልኬአለሁ እንጂ እኔ መሲሕ አይደለሁም'
ብዬ እንደነገርኋችሁ እናንተ ራሳችሁ ምስክ
ሮቼ ናችሁ ። 29 ሙሽሪት ያለችው ሰው ሙሽራ
ነው ፤ የሙሽራው ሚዜ ግን ከሙሽራው አጠ
ገብ ቆሞ ይሰማዋል ፤ የእርሱንም ድምፅ በመስ
ማት ይደሰታል ፤ ስለዚህ የእኔም ደስታ አሁን
ፍጹም ሆኖአል ። 30 እርሱ ከፍ ከፍ እንዲል ፥
እኔም ዝቅ ዝቅ እንድል ያስፈልጋል ።"
31 ከላይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው ፤
ከምድር የሆነ ምድራዊ ነው ፤ የምድርንም
ነገር ይናገራል ፤ ከሰማይ የሚመጣው ከሁሉ
በላይ ነው ። 32 እርሱ ያየውንና የሰማውን
ይመሰክራል ፤ ነገር ግን የእርሱን ምስክርነት
የሚቀበል የለም ። 33 የእርሱን ምስክርነት
የሚቀበል ግን እግዚአብሔር እውነተኛ መሆ
ኑን ያረጋግጣል ። 34 እግዚአብሔር የላከው

[2*] 3፥13 ቍጥር 13 ፦ "በሰማይ ከሚኖረው ከሰው ልጅ በቀር" የሚሉ ቅጂዎች አሉ ። [3*] 3፥25 በአንድ አይሁዳዊ ፦
አንዳንድ ቅጂዎች "በጥቂት አይሁዳውያን" ይላሉ ።
3፥14 ፦ ዘኍ. 21፥9 ። 3፥24 ፦ ማቴ. 14፥3 ፤ ማር. 6፥17 ፤ ሉቃ. 3፥19-20 ። 3፥28 ፦ ዮሐ. 1፥20 ።

የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራል ፤ እግዚአብሔ
ርም መንፈሱን በሙላት ይሰጠዋል ። 35 አባት
ልጁን ይወድዳል ፤ ሁሉንም ነገር በእጁ አስረ
ክቦታል ። 36 በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይ
ወት አለው ፤ በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብ
ሔር ቍጣ በእርሱ ላይ ይኖርበታል እንጂ
ሕይወትን አያገኝም ።

## ምዕራፍ 4

### ኢየሱስና አንዲት ሳምራዊት ሴት

1 በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ከዮሐንስ ይበልጥ
ብዙ ሰዎችን ደቀ መዛሙርት እንደሚያደርግና
እንደሚያጠምቅ ፈሪሳውያን ሰሙ ፤ 2 ሆኖም
ያጠምቁ የነበሩት የእርሱ ደቀ መዛሙርት
እንጂ እርሱ ራሱ አያጠምቅም ነበር ። 3 ስለ
እርሱ የተባለውን ፈሪሳውያን እንደ ሰሙ ባወቀ
ጊዜ ፤ ኢየሱስ የይሁዳን ምድር ትቶ ወደ ገሊላ
ተመልሶ ሄደ ። 4 ወደዚያም ሲሄድ በሰማርያ
በኩል ማለፍ ነበረበት ።

5 ስለዚህ ሲካር ወደምትባል ወደ ሰማርያ
ከተማ መጣ ። ሲካር ያዕቆብ ለልጁ ለዮሴፍ በሰ
ጠው ቦታ አጠገብ የምትገኝ ከተማ ናት ፤ 6 በዚ
ያም የያዕቆብ የውሃ ጕድጓድ ነበረ ፤ ኢየሱስ
መንገድ ከመሄድ የተነሣ ስለ ደከመው
በጕድጓዱ አጠገብ ተቀመጠ ፤ ጊዜውም ወደ
ስድስት ሰዓት ገደማ ነበረ ።

7 በዚያን ጊዜ አንዲት የሰማርያ አገር ሴት
ውሃ ልትቀዳ ወደ ጕድጓዱ መጣች ፤ ኢየሱስም
"ውሃ አጠጪኝ!" አላት ። 8 በዚያን ወቅት ደቀ
መዛሙርቱ ምግብ ሊገዙ ወደ ከተማ ሄደው
ነበር ። 9 ይህችም ሳምራዊት ሴት ኢየሱስን
"አንተ አይሁዳዊ ሆነህ እንዴት እኔን ሳም
ራዊቷን 'ውሃ አጠጪኝ!' ብለህ ትጠይቀኛ
ለህ?" አለችው ፤ ይህን ማለትዋ አይሁዳውያን
ከሳምራውያን ጋር ኅብረት ስላልነበራቸው
ነው ።

10 ኢየሱስም "የእግዚአብሔርን ስጦታና
'ውሃ አጠጪኝ' የሚልሽም ማን እንደሆነ ብታ
ውቂው ኖሮ እርሱን መለመን የሚገባሽ አንቺ
ነበርሽ ፤ እርሱም የሕይወትን ውሃ ይሰጥሽ
ነበር" አላት ።

11 እርስዋም እንዲህ ስትል መለሰች ፤ "ጌታ
ሆይ! አንተ መቅጃ የለህም ፤ ጕድጓዱም ጥልቅ
ነው ፤ ታዲያ የሕይወት ውሃ ከየት ታገኛለህ?
12 አንተ ይህን ጕድጓድ ከሰጠን ከአባታችን ከያ
ዕቆብ ትበልጣለህን? እርሱና ልጆቹ ፤ ከብቶ
ቹም ከዚህ ጕድጓድ ጠጥተዋል ።"

13 ኢየሱስ እንዲህ ሲል መለሰላት ፤ "ከዚህ
ውሃ የሚጠጣ ሁሉ እንደገና ውሃ ይጠማዋል ፤
14 እኔ ከምሰጠው ውሃ የሚጠጣ ለዘላለም ከቶ
አይጠማም ፤ ምክንያቱም እኔ የምሰጠው ውሃ ፤
ለሚጠጣው ሰው ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ
ምንጭ ይሆናል ።"

15 ሴትዮዋም "ጌታ ሆይ! ከእንግዲህ ወዲህ
ውሃ እንዳይጠማኝና ወደዚህም ለመቅዳት እንዳ
ልመጣ እባክህ እንዲህ ዐይነቱን ውሃ ስጠኝ"
አለችው ።

16 ኢየሱስም "ሂጂና ባልሽን ጠርተሽ ተመ
ለሽ" አላት ።

17 ሴትዮዋም "ባል የለኝም" ስትል መለ
ሰች ፤

በዚህ ጊዜ ኢየሱስ እንዲህ አላት ፤ "ባል የለ
ኝም ማለትሽ ልክ ነው ፤ 18 ምክንያቱም አም
ስት ባሎች ነበሩሽ ፤ አሁንም ከአንቺ ጋር
ያለው ሰው ባልሽ አይደለም ፤ ስለዚህ እውነቱን
ተናግረሻል ።"

19 ሴትዮዋም እንዲህ አለችው ፤ "ጌታ ሆይ!
አንተ ነቢይ እንደሆንህ አሁን ዐወቅሁ ፤ 20 አባ
ቶቻችን በዚህ ተራራ ላይ ሰገዱ ፤ እናንተ ግን
'ሰዎች መስገድ የሚገባቸው በኢየሩሳሌም
ነው' ትላላችሁ ።"

21 ኢየሱስም እንዲህ አላት ፤ "አንቺ ሴት!
ለእግዚአብሔር አብ በዚህ ተራራ ላይ ወይም
በኢየሩሳሌም ስለ መስገድ ጕዳይ የማትጨነቂ
በት ጊዜ እንደሚመጣ እመኚኝ ፤ 22 እናንተ
ለማታውቁት አምላክ ትሰግዳላችሁ ፤ እኛ ግን
ደኅንነት ከአይሁድ ስለሆነ ለምናውቀው አም
ላክ እንሰግዳለን ። 23 ነገር ግን በእውነት የሚሰ
ግዱ ለእግዚአብሔር አብ በመንፈስና በእውነት
የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል ፤ እንዲያውም
አሁን መጥቶአል ፤ እግዚአብሔር አብም የሚፈ
ልገው እንደዚህ የሚሰግዱለትን ነው ። 24 እግዚ
አብሔር መንፈስ ነው ፤ በእውነት የሚሰግዱለ
ትም በመንፈስ ሊሰግዱለት ይገባቸዋል ።"

25 ሴትዮዋም "መሲሕ እንደሚመጣ ዐውቃ
ለሁ ፤ እርሱ ሲመጣ ሁሉን ነገር ይነግረናል"
አለችው ።

26 ኢየሱስም "እነሆ አሁን የማነጋግርሽ እኔ
እርሱ ነኝ" አላት ።

27 በዚህ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ከሄዱበት
ተመልሰው መጡ ፤ ኢየሱስ ከሴት ጋር በመነጋ
ገሩ ተደነቁ ፤ ይሁን እንጂ "ምን ትፈልጊያለሽ
ወይም ከእርስዋ ጋር ለምን ትነጋገራለህ?"
ብሎ የጠየቀው ማንም አልነበረም ።

28 ከዚህ በኋላ ሴትዮዋ እንስራዋን ትታ ወደ
ከተማ ሄደችና ለሰዎቹ እንዲህ አለች ፤ 29 "የሠ
ራሁትን ሁሉ የነገረኝን ሰው ኑ እዩ! ምናል
ባት እርሱ መሲሕ ይሆንን?" 30 ሰዎቹም ከከ
ተማ ወጥተው ወደ ኢየሱስ ሄዱ ።

31 በዚህ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስን
"መምህር ሆይ! ምሳህን ብላ" ሲሉ ለመኑት ።

3፡35 ፡- ማቴ. 11፡27 ፤ ሉቃ. 10፡22 ። 4፡5 ፡- ዘፍ. 33፡19 ፤ ኢያሱ 24፡32 ። 4፡9 ፡- ዕዝ. 4፡1-5 ፤ ነህ. 4፡1-2 ።



32 እርሱ ግን "እናንተ የማታውቁት እኔ የም
በላው ምግብ አለኝ" አላቸው ።

33 ስለዚህ ደቀ መዛሙርቱ "ሰው ምግብ
አምጥቶለት ይሆን?" ተባባሉ ። 34 ኢየሱስም
እንዲህ አላቸው ፤ "የእኔ ምግብ የላከኝን
ፈቃድ ማድረግና ሥራውንም መፈጸም ነው ።
35 እናንተ 'ገና አራት ወር ቀርቶታል ፤ ከዚያም
በኋላ መከር ይሆናል' ትሉ የለምን? እኔ ግን
'ቀና ብሉና እርሻዎቹ ለመከር እንደደረሱ ተመ
ልከቱ' እላችኋለሁ ። 36 የሚያጭድ ደመወዙን
ይቀበላል ፤ ለዘላለም ሕይወት የሚሆን ፍሬም
ይሰበስባል ፤ ስለዚህ የሚዘራውም ፤ የሚያጭደ
ውም አብረው ይደሰታሉ ። 37 በዚህም ምክን
ያት 'አንዱ ይዘራል ፤ ሌላው ያጭዳል' የተባ
ለው ምሳሌ እውነት ነው ። 38 እኔም ያልደከማ
ችሁበትን እንድታጭዱ ላክሁአችሁ ፤ ሌሎች
በሥራ ደከሙ ፤ እናንተ ግን በድካማቸው ፍሬ
ተጠቀማችሁ ።"

39 ሴትዮዋ "የሠራሁትን ነገር ሁሉ ነገረኝ"
ብላ በመሰከረችው መሠረት ከዚያ ከተማ ብዙ
ሰዎች አመኑ ። 40 ስለዚህ የሰማርያ አገር ሰዎች
ወደ ኢየሱስ በመጡ ጊዜ ከእነርሱ ጋር እንዲ
ቆይ ለመኑት ፤ እርሱም ሁለት ቀን እዚያ ቆየ ።

41 በቃሉም ምክንያት ሌሎች ብዙ ሰዎችም
በእርሱ አመኑ ። 42 ሴትዮዋንም "ከእንግዲህ
ወዲህ እርሱን የምናምነው አንቺ በነገርሽን
ቃል ብቻ ሳይሆን ፤ እኛ ራሳችን ስለሰማንና በእ
ርግጥ የዓለም አዳኝ እንደሆነ ስላወቅን ነው"
አሉአት ።

### ኢየሱስ የሹሙን ልጅ ፈወሰ

43 ኢየሱስ በሰማርያ ሁለት ቀን ከቆየ በኋላ
ወደ ገሊላ ሄደ ። 44 እርሱ ራሱ "ነቢይ በገዛ
አገሩ አይከበርም" ብሎ ተናግሮ ነበር ። 45 ነገር
ግን ወደ ገሊላ በሄደ ጊዜ የገሊላ ሰዎች በጥሩ
ሁኔታ ተቀበሉት ፤ ምክንያቱም ለፋሲካ በዓል
ወደ ኢየሩሳሌም ሄደው በነበረበት ጊዜ እርሱ
በዚያ ያደረገውን ሁሉ አይተው ስለነበር ነው ።

46 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ውሃውን የወይን ጠጅ
ወዳደረገባት ፤ በገሊላ አገር ወደምትገኘው ወደ
ቃና ከተማ እንደገና ሄደ ፤ በዚያን ጊዜ በቅፍር
ናሆም ልጁ የታመመበት አንድ ሹም ነበረ ።
47 እርሱም ኢየሱስ ከይሁዳ አገር ወደ ገሊላ
መምጣቱን ሰምቶ ወደ ኢየሱስ ሄደ ፤ ወደ ቅፍ
ርናሆም እንዲወርድና በጠና ታሞ ሊሞት የተ
ቃረበውን ልጁን እንዲፈውስለት ኢየሱስን ለመ
ነው ። 48 ኢየሱስም "እናንተ እኮ ተአምራትና
ድንቅ ነገር ካላያችሁ በቀር ምንም አታም
ኑም!" አለው ።

49 ሹሙም "ጌታ ሆይ! ልጄ ከመሞቱ
በፊት እባክህ ቶሎ ውረድ" አለው ።

50 ኢየሱስም "ወደ ቤትህ ሂድ ፤ ልጅህ ድና
አል" አለው ።

ሰውየውም ኢየሱስ የተናገረውን ቃል አምኖ
ወደ ቤቱ ሄደ ። 51 ሲሄድም አገልጋዮቹ በመን
ገድ አገኙትና "ልጅህ ድኖአል" ብለው ነገ
ሩት ።

52 እርሱም ልጁ በጎ የሆነበትን ሰዓት ጠየቃ
ቸው ። እነርሱም "ትናንትና በሰባት ሰዓት ላይ
ትኩሳቱ ለቀቀው" አሉት ። 53 አባትየውም ኢየ
ሱስ "ልጅህ ድኖአል" ያለው በዚያኑ ሰዓት
እንደሆነ ዐወቀ ፤ ስለዚህ ከዚያን ቀን ጀምሮ
እርሱና ቤተ ሰቡ ሁሉ በኢየሱስ አመኑ ።

54 ይህ ተአምር ኢየሱስ ከይሁዳ ወደ ገሊላ
በመጣ ጊዜ ያደረገው ሁለተኛው ተአምር ነው ።

## ምዕራፍ 5

### ኢየሱስ አንድ ሽባ ሰው ፈወሰ

1 ከዚህ በኋላ የአይሁድ በዓል ስለነበረ ኢየ
ሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ ። 2 በኢየሩሳሌም በበ
ጎች በር አጠገብ በዕብራይስጥ ቋንቋ ቤተዛታ[4*]
የሚባል አንድ የምንጭ ኩሬ ነበረ ፤ በዚያም
አምስት ባለ ቅስት መተላለፊያዎች ነበሩ ።
3 ብዙ በሽተኞች ፤ ዕውሮች ፤ አንካሶች ፤ ሽባ
ዎች በመተላለፊያዎቹ ተኝተው ነበር ።
[ውሃው እስከሚንቀሳቀስ ይጠባበቁ ነበር ፤
4 አልፎ አልፎ የጌታ መልአክ ወደ ኩሬው
ወርዶ ውሃውን ያናውጥ ነበር ፤ ከውሃው መና
ወጥ በኋላ በመጀመሪያ ወደ ኩሬው የሚገባ
ካደረበት ከማንኛውም በሽታ ይፈወስ ነበር ።][5*]
5 በዚያም ሠላሳ ስምንት ዓመት ሙሉ የታመመ
አንድ ሰው ነበረ ። 6 ኢየሱስ ይህን ሰው እዚያ
ተኝቶ አየውና ከብዙ ጊዜ ጀምሮ መታመሙን
ዐውቆ "መዳን ትፈልጋለህን?" አለው ።

7 በሽተኛውም "ጌታ ሆይ! ውሃው በተንቀሳ
ቀሰ ጊዜ እኔን ወስዶ ወደ ኩሬው የሚያስገባኝ
ሰው የለኝም ፤ እኔ ልሄድ ስል ሌላው ቀድሞኝ
ይወርዳል" አለው ።

8 ኢየሱስም "ተነሥ አልጋህን ተሸክምና
ሂድ" አለው ። 9 ሰውየውም ወዲያውኑ ዳነ ፤
አልጋውንም ተሸክሞ ሄደ ።

ይህም የሆነው በሰንበት ቀን ነበር ፤ 10 ስለ
ዚህ አይሁዳውያን ባለሥልጣኖች ያንን የዳነ
ውን ሰው "ዛሬ ሰንበት ስለ ሆነ አልጋህን መሸ
ከም አልተፈቀደልህም" አሉት ።

4* 5፡2 ቤተዛታ ፡- አንዳንድ ቅጂዎች "ቤተሳይዳ ወይም ቤተሂስዳ" ይላሉ ፤ በአዲሱ አጻጻፍ ግን "ቤተ ዛታ" ይባላል ፤ ትርጕሙም "የምሕረት ቤት" ማለት ነው ። 5* 5፡4 የጥንት ቅጂዎች ከቍ. 3 የመጨረሻ ክፍል አንሥቶ እስከ ቍ. 4 ድረስ ያለውን ክፍል አይጨምሩም ።

4፡44 ፡- ማቴ. 13፡57 ፤ ማር. 6፡4 ፤ ሉቃ. 4፡24 ። 4፡45 ፡- ዮሐ. 2፡23 ። 4፡46 ፡- ዮሐ. 2፡1-11 ። 5፡10 ፡- ነህ. 13፡19 ፤ ኤር. 17፡21 ።

11 እርሱ ግን “ያዳነኝ ሰው አልጋህን ተሸክ
መህ ሂድ” ብሎኛል አላቸው ።
12 እነርሱም “አልጋህን ተሸክመህ ሂድ
ያለህ ማን ነው?” ሲሉ ጠየቁት ።
13 ሕዝብ ስለበዛና ኢየሱስም ከዚያ ራቅ
ብሎ ስለሄደ ያዳነው ማን መሆኑን አያውቅም
ነበር ።
14 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ሰውየውን በቤተ
መቅደስ አገኘውና “እነሆ አሁን ድነሃል!
ከዚህ የባሰ ነገር እንዳይደርስብህ ከእንግዲህ
ወዲህ ኃጢአት አትሥራ” አለው ።
15 ሰውየውም ሄደና ያዳነው ኢየሱስ መሆ
ኑን ለአይሁዳውያን ባለሥልጣኖች ነገረ ።
16 ይህን ነገር በሰንበት ስላደረገ አይሁዳውያን
ባለሥልጣኖች ኢየሱስን ያሳድዱት ጀመር ።
17 ኢየሱስ ግን “አባቴ ሁልጊዜ ይሠራል ፤
እኔም እሠራለሁ” ሲል መለሰላቸው ።
18 ይህም አባባል አይሁዳውያን ባለሥልጣ
ኖች ኢየሱስን እንዲገድሉት በይበልጥ አነሣሣ
ቸው ፤ ምክንያቱም እርሱ ሰንበትን በመሻሩ
ብቻ ሳይሆን “እግዚአብሔር አባቴ ነው” በማ
ለት ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር ስለአስተካከለ
ነው ።

## የእግዚአብሔር ልጅ ሥልጣን

19 ኢየሱስ እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፤
“እውነት ፥ እውነት እላችኋለሁ ፤ አብ ሲሠራ
ያየውን ከመሥራት በቀር ወልድ በራሱ ሥል
ጣን ምንም አይሠራም ። አብ የሚያደርገውን
ወልድም እንዲሁ ያደርጋል ። 20 ምክንያቱም
አብ ወልድን ይወድዳል ፤ የሚሠራውንም ሁሉ
ያሳየዋል ፤ እናንተም እንድትደነቁ ከዚህ የበ
ለጠ ሥራም ያሳየዋል ። 21 አብ የሞቱትን እንደ
ሚያስነሣና ሕይወትን እንደሚሰጣቸው ፥ ወል
ድም እንዲሁ ለፈለገው ሰው ሕይወትን ይሰጠ
ዋል ። 22 አብ በማንም ላይ አይፈርድም ፤ ነገር
ግን የፍርድን ሥልጣን ሁሉ ለወልድ ሰጥቶ
አል ። 23 ይህንንም ያደረገው ሰዎች ሁሉ አብን
እንደሚያከብሩ ፥ እንዲሁም ወልድን እንዲያከ
ብሩ ነው ። ወልድን የማያከብር ፥ ወልድን የላከ
ውን አብንም አያከብርም ።
24 “እውነት ፥ እውነት እላችኋለሁ ፥ ቃሌን
የሚሰማና በላከኝም የሚያምን የዘላለም ሕይ
ወት አለው ፤ እርሱ ከሞት ወደ ሕይወት ተሻ
ገረ እንጂ አይፈረድበትም ። 25 እውነት ፥ እው
ነት እላችኋለሁ ፥ የሞቱ ሰዎች የእግዚአብሔ
ርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ጊዜ ይመጣል ፤
ጊዜውም አሁን ነው ፤ የሚሰሙትም ሁሉ በሕ
ይወት ይኖራሉ ። 26 ምክንያቱም አብ ራሱ የሕ
ይወት ምንጭ እንደሆነ ፥ እንዲሁም ወልድን
የሕይወት ምንጭ እንዲሆን አድርጎታል ።
27 የሰው ልጅ በመሆኑም ፍርድ እንዲፈርድ
ሥልጣን ሰጥቶታል ። 28 በዚህ ነገር አትደነቁ!
ምክንያቱም በመቃብር ውስጥ ያሉት ሁሉ የእ
ርሱን ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል ።
29 መልካም የሠሩ ከሞት ተነሥተው በሕይወት
ይኖራሉ ፤ ክፉ የሠሩ ግን ከሞት ተነሥተው
ይፈረድባቸዋል ።

## ለኢየሱስ የመሰከሩ ሰዎች

30 “እኔ በራሴ ሥልጣን ምንም ማድረግ አል
ችልም ፤ ነገር ግን ከአብ የሰማሁትን እፈርዳ
ለሁ ፤ የላከኝን ፈቃድ እንጂ የራሴን ፈቃድ ስለ
ማላደርግ ፍርዴ ትክክል ነው ።
31 “እኔ ስለ ራሴ ብመሰክር ፥ ምስክርነቴ
እውነት አይደለም ። 32 ነገር ግን ስለ እኔ የሚ
መሰክር ሌላ አለ ፤ እርሱም ስለ እኔ የሚመሰክ
ረው ምስክርነት እውነት መሆኑን ዐውቃለሁ ።
33 እናንተ ወደ ዮሐንስ ሰዎች ልካችሁ ነበር ፤
እርሱም ስለ እውነት መስክሮአል ። 34 ይህንንም
ማለቴ እንድትድኑ ነው እንጂ እኔ የሰው ምስክ
ርነት ስላስፈለገኝ አይደለም ። 35 ዮሐንስ እንደ
ሚነድድና እንደሚበራ መብራት ነበረ ፤ እናን
ተም ለጥቂት ጊዜ በእርሱ ብርሃን ለመደሰት
ፈለጋችሁ ። 36 እኔ ግን ከዮሐንስ ምስክርነት የበ
ለጠ ምስክር አለኝ ፤ ምስክሬም አባቴ እንድሠ
ራው የሰጠኝ ሥራ ነው ፤ ይህም የምሠራው
ሥራ አብ እንደላከኝ ስለ እኔ ይመሰክራል ።
37 የላከኝም አብ ራሱ ስለ እኔ መስክሮአል ፤
እናንተ ግን ድምፁን ከቶ አልሰማችሁም ፤ መል
ኩንም ከቶ አላያችሁም ። 38 እርሱ የላከውን
ስለማታምኑ የእርሱ ቃል በእናንተ ዘንድ አይኖ
ርም ። 39 እናንተ በቅዱሳት መጻሕፍት የዘላለ
ምን ሕይወት የምታገኙ ስለሚመስላችሁ እነር
ሱን ትመረምራላችሁ ፤ እነርሱም ስለ እኔ የሚ
መሰክሩ ናቸው ። 40 ይሁን እንጂ እናንተ ሕይ
ወትን ለማግኘት ወደ እኔ መምጣት አትፈል
ጉም ።
41 “እኔ ክብርን ከሰው አልፈልግም ። 42 እና
ንተ የእግዚአብሔር ፍቅር የሌላችሁ መሆናች
ሁን ዐውቃለሁ ። 43 እኔ በአባቴ ስም መጣሁ ፤
እናንተ ግን አልተቀበላችሁኝም ፤ ሌላ በራሱ
ስም ቢመጣ ግን ትቀበሉታላችሁ ። 44 እርስ በር
ሳችሁ ከሰው ክብርን የምትፈልጉ ፥ ከአንዱ ከእ
ግዚአብሔር የሚገኘውን ክብር ግን የማትፈ
ልጉ ፥ እናንተ እንዴት በእኔ ልታምኑ ትችላላ
ችሁ? 45 እኔ በአባቴ ፊት የምከስሳችሁ አይምሰ
ላችሁ ፤ የሚከስሳችሁ ተስፋ የምታደርጉበት
ሙሴ ነው ። 46 ሙሴን ብታምኑ ኖሮ እርሱ ስለ
እኔ ጽፎአልና እኔንም ባመናችሁ ነበር ።

5፡29 ፦ ዳን. 12፡2 ። 5፡33 ፦ ዮሐ. 1፡19-27 ፤ 3፡27-30 ። 5፡37 ፦ ማቴ. 3፡17 ፤ ማር. 1፡11 ፤ ሉቃ. 3፡22 ።



47 እርሱ የጻፈውን ካላመናችሁ ግን የእኔን ቃል
እንዴት ታምናላችሁ?”

# ምዕራፍ 6

## ኢየሱስ አምስት ሺ ሰዎች መገበ
(ማቴ. 14፡13-21፤ ማር. 6፡30-44፤
ሉቃ. 9፡10-17)

1 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ጥብርያዶስ ወደሚባ
ለው ወደ ገሊላ ባሕር ማዶ ተሻገረ ። 2 ብዙ
ሰዎች ኢየሱስ በሽተኞችን በመፈወስ ያደረገ
ውን ተአምር ስላዩ ተከተሉት ። 3 ኢየሱስ ወደ
ተራራ ወጣና በዚያ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተቀ
መጠ ። 4 የአይሁድ ፋሲካ በዓል ቀርቦ ነበር ።
5 በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ብዙ ሕዝብ ወደ እርሱ
ሲመጣ ቀና ብሎ አየና ፊልጶስን “ለዚህ ሁሉ
ሰው የሚበቃ ምግብ ከየት መግዛት እንችላ
ለን?” አለው ። 6 ኢየሱስ ይህን የተናገረው ፊል
ጶስን ለመፈተን ነበር እንጂ የሚያደርገውንስ
እርሱ ራሱ ያውቅ ነበር ።
7 ፊልጶስም “ለእያንዳንዳቸው ትንሽ ትንሽ
ቍራሽ እንኳ እንዲሰጣቸው የሁለት መቶ ብር
እንጀራ አይበቃቸውም” ሲል መለሰለት ።
8 ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ የስምዖን ጴጥሮስ
ወንድም እንድርያስ እንዲህ አለ ፥ 9 “አምስት
የገብስ እንጀራና ሁለት ዓሣ የያዘ አንድ ልጅ
እዚህ አለ ፤ ነገር ግን ይህ ለዚህ ሁሉ ሕዝብ
ምን ይበቃል?” 10 ኢየሱስም “ሰዎቹ እንዲቀ
መጡ አድርጉአቸው” አለ ። በዚያ ቦታ ብዙ
ሣር ነበረ ፤ ሰዎቹም ተቀመጡ ፤ ቍጥራቸውም
አምስት ሺ የሚያህል ነበር ። 11 ከዚህ በኋላ
ኢየሱስ እንጀራውን አንሥና የምስጋና ጸሎት
አቅርቦ ለተቀመጡት ሰዎች አደላቸው ። እንዲ
ሁም ዓሣዎቹን አከፋፈላቸው ፤ ሁሉም የሚያስ
ፈልጋቸውን ያህል አገኙ ። 12 ሁሉም በልተው
ከጠገቡ በኋላ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን “አን
ድም ነገር እንዳይባክን የተረፈውንም ፍርፋሪ
ሰብስቡ” አላቸው ። 13 እነርሱም ሰዎቹ በል
ተው ከተረፈው ከአምስቱ የገብስ እንጀራ ፍር
ፋሪውን ሰብስበው በዐሥራ ሁለት መሶብ
ሞሉ ።
14 ሰዎቹም ኢየሱስ ያደረገውን ተአምር ባዩ
ጊዜ “በእርግጥ ይህ ወደ ዓለም የሚመጣው
ነቢይ ነው” አሉ ። 15 ሰዎቹ ግን በግድ ወስ
ደው ሊያነግሡት እንዳሰቡ ባወቀ ጊዜ ኢየሱስ
ብቻውን እንደገና ራቅ ብሎ ወደ ኮረብታ
ሄደ ።

## ኢየሱስ በባሕር ላይ እየተራመደ ሄደ
(ማቴ. 14፡22-33፤ ማር. 6፡45-52)

16 በመሸ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ገሊላ
ባሕር ወረዱ ። 17 በጀልባ ተሳፍረው ወደ ቅፍር
ናሆም አመሩ ፤ በዚያን ሰዓት ጊዜው ጨልሞ
ነበር ፤ ኢየሱስም ገና ወደ እነርሱ አልመጣም
ነበር ። 18 ኀይለኛ ነፋስ ይነፍስ ስለነበር ባሕሩ
ተናወጠ ። 19 ደቀ መዛሙርቱ አራት ወይም
አምስት ኪሎ ሜትር ያህል እየቀዘፉ ከተጓዙ
በኋላ ኢየሱስ በባሕሩ ላይ እየተራመደ ወደ ጀል
ባዋ ሲቀርብ አይተው ፈሩ ። 20 እርሱ ግን “እኔ
ነኝ! አትፍሩ!” አላቸው ። 21 እነርሱም በደስታ
ተቀብለው ወደ ጀልባዋ አስገቡት ፤ ወዲያውኑ
ጀልባዋ ወደሚሄዱበት ቦታ ደረሰች ።

## ኢየሱስ የሕይወት እንጀራ

22 በማግሥቱ ከባሕሩ ማዶ ቀርተው የነበ
ሩት ሰዎች በባሕሩ ላይ አንድ ጀልባ ብቻ መኖ
ሩን አዩ ፤ ደቀ መዛሙርቱ ብቻቸውን እንደሄ
ዱና ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር ወደ ጀልባዋ እንዳል
ገባ ዐወቁ ። 23 ሆኖም ሌሎች ጀልባዎች ከጥብ
ርያዶስ ተነሥተው ኢየሱስ የምስጋና ጸሎት
ወደአደረገበትና ሕዝቡ እንጀራ ወደ በላበት
ስፍራ አጠገብ መጡ ። 24 ሰዎቹም ኢየሱስ
ወይም ደቀ መዛሙርቱ በእዚያ እንደሌሉ ባዩ
ጊዜ በነዚያ ጀልባዎች ተሳፍረው ኢየሱስን
ፍለጋ ወደ ቅፍርናሆም ሄዱ ። 25 ከባሕሩ ማዶ
ባገኙትም ጊዜ “መምህር ሆይ! ወደዚህ መቼ
መጣህ?” አሉት ።
26 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፥
“እውነት ፥ እውነት እላችኋለሁ ፥ እናንተ የም
ትፈልጉኝ እንጀራ ስለበላችሁና ስለጠገባችሁ
ነው እንጂ ተአምራት ስላያችሁ አይደለም ።
27 ለሚጠፋ ምግብ አትሥሩ ፤ ይልቅስ የሰው
ልጅ ለሚሰጣችሁ ፥ የዘላለም ሕይወት ለሚሆን
ምግብ ሥሩ ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር አብ
በልጁ የማረጋገጫ ማኅተም አትሞበታል ።”
28 ሰዎቹም “ታዲያ የእግዚአብሔርን ሥራ
ለመሥራት ምን ማድረግ ይገባናል?” አሉት ።
29 ኢየሱስም “የእግዚአብሔር ሥራማ እግዚ
አብሔር በላከው ማመን ነው” ሲል መለሰላ
ቸው ።
30 እነርሱም እንዲህ አሉት ፥ “እኛ አይተን
በአንተ እንድናምን ምን ተአምር ታደርጋለህ?
ምንስ ትሠራለህ? 31 ‘እንዲበሉ ከሰማይ እንጀራ
ሰጣቸው’ ተብሎ እንደተጻፈ አባቶቻችን በበ
ረሓ መና በልተዋል ።”
32 በዚህ ጊዜ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው ፥
“ከሰማይ የወረደውን እንጀራ የሰጣችሁ ሙሴ
አይደለም ፤ እውነተኛውን እንጀራ ከሰማይ የሚ
ሰጣችሁ አባቴ ነው ፤ 33 ምክንያቱም የእግዚአ
ብሔር እንጀራ ከሰማይ የሚወርድና ለዓለም
ሕይወትን የሚሰጥ ነው ።” 34 ስለዚህ ሰዎቹ
“ጌታ ሆይ! ይህን ዐይነት እንጀራ ዘወትር
ስጠን” አሉት ።

6፡31 ፦ ዘጸ. 16፡4 ፡15 ፤ መዝ. 78፡24 ።

35ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፥ “የሕይወት
እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይ
ራብም፤ በእኔ የሚያምን ከቶ አይጠማም፤
36እናንተ ግን አይታችሁኝ በእኔ አላመናች
ሁም አላችኋለሁ። 37አብ የሚሰጠኝ ሁሉ
ወደ እኔ ይመጣል፤ ወደ እኔ የሚመጣውንም
ወደ ውጪ አላባርረውም። 38ምክንያቱም እኔ
ከሰማይ የወረድሁት የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ
እንጂ የራሴን ፈቃድ ለማድረግ አይደለም።
39የላከኝ ፈቃድ፥ ከሰጠኝ ሁሉ አንድ እንኳ
ሳላጠፋ በመጨረሻው ቀን እንዳስነሣ ነው።
40አዎ፥ የአባቴ ፈቃድ ወልድን የሚያይና
በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እን
ዲያገኝ ነው፤ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣ
ዋለሁ።” 41ስለዚህ ኢየሱስ “ከሰማይ የወረደ
እንጀራ እኔ ነኝ” በማለቱ አይሁዳውያን በእ
ርሱ ላይ አጒረመረሙ፤ 42እንዲህም አሉ፥
“ይህ የዮሴፍ ልጅ ኢየሱስ አይደለምን? አባቱ
ንና እናቱንስ እናውቃቸው የለምን? ታዲያ
አሁን እርሱ ‘ከሰማይ ወረድሁ’ እንዴት
ይላል?”
43ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፥
“እርስ በርሳችሁ አታጒረምርሙ፤ 44የላከኝ
አብ የሳበው ካልሆነ በቀር ወደ እኔ መም
ጣት የሚችል ማንም የለም፤ ወደ እኔ የሚ
መጣውንም በመጨረሻ ቀን ከሞት አስነሣዋ
ለሁ። 45በነቢያት መጻሕፍት ‘ሰዎች ሁሉ
ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ’ ተብሎ
ተጽፎአል፤ ስለዚህ ከአብ ሰምቶ የተማረ
ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል። 46ይህም ሲሆን
አብን ያየው ሰው አለ ማለት አይደለም።
አብን ያየው ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣው
ብቻ ነው። 47እውነት፥ እውነት እላችኋ
ለሁ፥ (በእኔ) የሚያምን ሰው የዘላለም ሕይ
ወት አለው። 48እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ፤
49አባቶቻችሁ በበረሓ መና በሉ፤ ነገር ግን
ሞቱ፤ 50ከሰማይ የወረደው እንጀራ ይህ
ነው፤ ይህን እንጀራ የሚበላ ከቶ አይሞ
ትም። 51ከሰማይ የወረደው ሕያው እንጀራ
እኔ ነኝ፤ ከዚህ እንጀራ የሚበላ ሁሉ ለዘላ
ለም ይኖራል፤ ለዓለም ሕይወት እንዲሆን
እኔ የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው።”
52በዚህ ጊዜ አይሁዳውያን “ይህ ሰው ሥጋ
ውን እንድንበላ እንዴት ሊሰጠን ይችላል?”
በማለት እርስ በርሳቸው ተከራከሩ።
53ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፥ “እው
ነት፥ እውነት እላችኋለሁ የሰው ልጅ የሆነውን
(የክርስቶስን) ሥጋ ካልበላችሁ፥ ደሙንም ካል
ጠጣችሁ ሕይወት የላችሁም። 54ሥጋዬን የሚ
በላና ደሜንም የሚጠጣ ሁሉ የዘላለም ሕይ
ወት አለው፤ እኔም በመጨረሻው ቀን ከሞት
አስነሣዋለሁ። 55ምክንያቱም ሥጋዬ እውነተኛ
መብል፥ ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነው።
56ሥጋዬን የሚበላና ደሜን የሚጠጣ ሁሉ
በእኔ ይኖራል፤ እኔም በእርሱ እኖራለሁ።
57ሕያው አብ እንደላከኝና እኔም በእርሱ
ሕያው እንደሆንሁ እንዲሁም ሥጋዬን የሚበላ
ሁሉ በእኔ ሕያው ይሆናል። 58እንግዲህ ከሰ
ማይ የወረደው እንጀራ ይህ ነው፤ እርሱም አባ
ቶቻችሁ እንደበሉት ዐይነት አይደለም፤ ምክን
ያቱም ያን እንጀራ የበሉ ሞተዋል፤ ይህን እን
ጀራ የሚበሉ ግን ዘላለም ይኖራሉ።”
59ኢየሱስ ይህን የተናገረው በቅፍርናሆም
በምኵራብ በሚያስተምርበት ጊዜ ነበር።

የዘላለም ሕይወት ቃል

60ከደቀ መዛሙርቱ ብዙዎቹ ይህን በሰሙ
ጊዜ “ይህ ንግግር ከባድ ነው፤ ማን ሊቀበለው
ይችላል” አሉ።
61ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱ ስለዚህ ነገር
እንዳጒረመረሙ በመንፈሱ ዐውቆ እንዲህ አላ
ቸው፥ “ይህ ነገር ያሰናክላችኋልን? 62የሰው
ልጅ ክርስቶስ ወደነበረበት ተመልሶ ሲወጣ
ስታዩ ምን ልትሉ ነው? 63ሕይወትን የሚሰጥ
የእግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሰው ኀይል ግን
ለምንም አይጠቅምም፤ እኔ ለእናንተ የተናገር
ሁት ቃል ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ነው።
64ነገር ግን ከእናንተ መካከል አንዳንዶች የማያ
ምኑ አሉ፤” ኢየሱስ ይህን የተናገረው ከመጀ
መሪያ አንሥቶ የማያምኑ እነማን እንደነበሩና
አሳልፎ የሚሰጠውም ማን እንደሆነ ያውቅ ስለ
ነበር ነው። 65ቀጥሎም ኢየሱስ “ከአብ የተፈ
ቀደለት ካልሆነ በቀር ወደ እኔ መምጣት የሚ
ችል የለም ያልኋችሁ ስለዚህ ነው” አለ።
66በዚህም ምክንያት ከደቀ መዛሙርቱ ብዙ
ዎቹ ወደ ኋላ ተመለሱ፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮም
ኢየሱስን መከተል ተዉ። 67ስለዚህ ኢየሱስ
ዐሥራ ሁለቱን “እናንተም ደግሞ መሄድ ትፈ
ልጋላችሁን?” አላቸው።
68በዚህ ጊዜ ስምዖን ጴጥሮስ እንዲህ ሲል
መለሰ፥ “ጌታ ሆይ! ወደ ማን እንሄዳለን?
አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ። 69እኛስ
አምነናል፤ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ አንተ
እንደሆንህም ዐውቀናል።” 70ኢየሱስም “እናን
ተን ዐሥራ ሁለታችሁን መርጬአችሁ የለምን?
ታዲያ እኮ ከእናንተ አንዱ ዲያብሎስ ነው”
አላቸው። 71ይህንንም ያለው ስለ ስምዖን ልጅ
ስለ አስቆሮታዊው ይሁዳ ነበር፤ ምክንያቱም
ይሁዳ ምንም እንኳ ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ ቢሆ
ንም ኢየሱስን አሳልፎ የሚሰጥ እርሱ ስለነበር
ነው።

6፥45 ፦ ኢሳ. 54፥13። 6፥68-69 ፦ ማቴ. 16፥16፤ ማር. 8፥29፤ ሉቃ. 9፥20።



## ምዕራፍ 7

### ኢየሱስ ለዳስ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ

1ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በገሊላ ይዘዋወር
ነበር፤ በይሁዳ ግን ሊዘዋወር አልፈለገም፤
ምክንያቱም አይሁዳውያን ባለሥልጣኖች ሊገ
ድሉት ይፈልጉ ነበር። 2በዚያን ጊዜ የአይሁዳ
ውያን የዳስ በዓል ቀርቦ ነበር። 3ስለዚህ ወንድ
ሞቹ ወደ ኢየሱስ ቀርበው እንዲህ አሉት፥
“ደቀ መዛሙርትህ የምታደርገውን ሥራ እንዲ
ያዩ ከዚህ ተነሥተህ ወደ ይሁዳ አገር ሂድ፤
4ምክንያቱም በግልጥ ለመታወቅ የሚፈልግ
ሰው ሥራውን በስውር አያደርግም፤ አንተም
እነዚህን ነገሮች ሁሉ ስታደርግ ራስህን ለዓለም
ልትገልጥ ያስፈልጋል።” 5ይህንንም ያሉበት
ምክንያት ወንድሞቹ እንኳ በእርሱ ስላላመኑ
ነው።
6ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፥ “የእኔ ጊዜ
ገና አልደረሰም፤ የእናንተ ጊዜ ግን ዘወትር
የተመቸ ነው። 7ዓለም እናንተን ሊጠላ አይች
ልም፤ እኔን ግን ይጠላኛል፤ ምክንያቱም እኔ
ሥራው ክፉ መሆኑን ስለምመሰክርበት ነው።
8እናንተ ወደ በዓሉ ሂዱ፤ እኔ ግን ጊዜዬ ገና
ስላልደረሰ ወደዚህ በዓል አልሄድም።” 9ይህን
ንም ብሎ እርሱ በገሊላ ቀረ።

### ኢየሱስ በዳስ በዓል ላይ ተገኘ

10ነገር ግን ወንድሞቹ ወደ በዓሉ ከሄዱ
በኋላ እርሱ በይፋ ሳይሆን በስውር ወደ በዓሉ
ሄደ። 11በበዓሉም ላይ “የት ነው?” እያሉ
አይሁዳውያን ባለሥልጣኖች ይፈልጉት ነበር።
12ሕዝቡም ስለ እርሱ በሹክሹክታ ይነጋገሩ
ነበር፤ አንዳንዶቹ “እርሱ ጥሩ ሰው ነው”
ሲሉ፥ ሌሎች ደግሞ “አይደለም፥ እርሱ ሕዝ
ቡን ያስታል” ይሉ ነበር። 13ይሁን እንጂ አይ
ሁዳውያን ባለሥልጣኖችን በመፍራት ማንም
ስለ እርሱ በግልጥ አልተናገረም።
14በበዓሉም አጋማሽ ላይ ኢየሱስ ወደ ቤተ
መቅደስ ሄዶ ያስተምር ጀመር። 15አይሁዳው
ያን ባለሥልጣኖችም “ይህ ሰው ሳይማር ይህን
ሁሉ እንዴት ሊያውቅ ቻለ?” እያሉ ይደነቁ
ነበር።
16ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ ሲል መለሰ፥
“የእኔ ትምህርት ከላከኝ ከአብ የተገኘ ነው
እንጂ ከእኔ አይደለም። 17የላከኝን ፈቃድ ማድ
ረግ የሚፈልግ ቢኖር፥ ይህ ትምህርት ከእግዚአ
ብሔር የተገኘ ወይም እኔ የተናገርሁት መሆ
ኑን ያውቃል። 18ከገዛ ራሱ የሚናገር፥ የገዛ
ራሱን ክብር ይፈልጋል፤ የላኪውን ክብር የሚ
ፈልግ ግን እውነተኛ ነው፤ ሐሰትም የለበ
ትም። 19ሙሴ ሕግን ሰጥቶአችሁ የለምን?
ነገር ግን ከእናንተ ሕግን የሚፈጽም ማንም
የለም። እናንተ ለምን ልትገድሉኝ ትፈልጋላ
ችሁ?”
20ሕዝቡም “አንተ ጋኔን አለብህ! ማን ሊገ
ድልህ ይፈልጋል?” አሉት።
21ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፥
“እኔ አንድ ሥራ ሠራሁ፤ እናንተም ሁላችሁ
በዚህ ሥራ ትደነቃላችሁ። 22ሙሴ የግዝረትን
ሥርዓት ሰጣችሁ፤ ይህም ሥርዓት የተገኘው
ከአባቶች ነው እንጂ ከሙሴ አይደለም፤ ታዲያ
እናንተ በሰንበትም እኮ ሰውን ትገርዛላችሁ።
23እንግዲህ የሙሴ ሕግ እንዳይሻር ሰው በሰን
በት ቀን የሚገረዝ ከሆነ፥ ታዲያ እኔ በሰንበት
ቀን የሰውን ሁለንተና በመፈወሴ ስለምን ትነቅ
ፉኛላችሁ? 24በቅንነት ፍረዱ እንጂ የሰው
ፊት አይታችሁ በማዳላት አትፍረዱ።”

### ስለ መሲሕ የተነሣ ክርክር

25ከኢየሩሳሌም ሰዎች አንዳንዶቹ እንዲህ
አሉ፥ “ሊገድሉት የሚፈልጉት ሰው ይህ አይ
ደለምን? 26እነሆ እርሱ በግልጥ ይናገራል፤
እነርሱም ምንም አላሉትም፤ ይህ ሰው መሲሕ
መሆኑን ባለሥልጣኖች በእውነት ዐውቀው
ይሆን? 27ታዲያ እኛ ይህ ሰው ከወዴት እንደ
ሆነ እናውቃለን፤ መሲሕ ሲመጣ ግን ከወዴት
እንደሆነ የሚያውቅ ማንም የለም።”
28ስለዚህ ኢየሱስ በቤተ መቅደስ ሲያስተ
ምር ድምፁን ከፍ አድርጎ እንዲህ አለ፥ “እኔን
ታውቁኛላችሁ፤ ከወዴትም እንደ መጣሁ
ታውቃላችሁ፤ ነገር ግን እኔ በራሴ ሥልጣን
አልመጣሁም፤ የላከኝ እውነተኛ ነው፤ እናን
ተም አታውቁትም። 29እኔ ግን ከእርሱ ዘንድ
ስለመጣሁና እርሱ ስለላከኝ ዐውቀዋለሁ።”
30በዚያን ጊዜ ሊይዙት ፈልገው ነበር፤
ነገር ግን ጊዜው ገና ስላልደረሰ ማንም አልያዘ
ውም። 31ሆኖም ከሕዝቡ ብዙዎቹ በእርሱ
አመኑ፤ እንዲህም አሉ፥ “መሲሕ በሚመጣበ
ትስ ጊዜ ይህ ሰው ካደረጋቸው ተአምራት የበ
ለጠ ያደርጋልን?”

### ኢየሱስን እንዲይዙ ወታደሮች ተላኩ

32ሕዝቡ ስለ ኢየሱስ በሹክሹክታ ሲነጋገሩ
ፈሪሳውያን ሰሙ፤ ስለዚህ የካህናት አለቆችና
ፈሪሳውያን ኢየሱስን ለማስያዝ ወታደሮች
ላኩ። 33በዚያን ጊዜ ኢየሱስ እንዲህ አለ፥
“ከእናንተ ጋር ጥቂት ጊዜ እቆያለሁ፤ ከዚያ
በኋላ ወደ ላከኝ እሄዳለሁ፤ 34እናንተ ትፈልጉ
ኛላችሁ፤ ግን አታገኙኝም፤ እኔ ወዳለሁበት
እናንተ መምጣት አትችሉም።”
35ስለዚህ አይሁዳውያን ባለሥልጣኖች እን
ዲህ ተባባሉ፥ “እኛ እንዳናገኘው ይህ ሰው

7፥2 ፦ ዘሌ. 23፥34፤ ዘዳ. 16፥13። 7፥22 ፦ ዘፍ. 17፥10፤ ዘሌ. 12፥3። 7፥23 ፦ ዮሐ. 5፥9።

ወዴት ሊሄድ ነው? ምናልባት በግሪኮች መካ
ከል ወደ ተበተኑት አይሁዳውያን ሄዶ ግሪኮችን
ያስተምር ይሆን? 36 ‘ትፈልጉኛላችሁ፤ ነገር
ግን አታገኙኝም፤ እኔ ወዳለሁበት እናንተ ልት
መጡ አትችሉም’ ሲል ምን ማለቱ ነው?”

### የሕይወት ውሃ

37 የበዓሉ መጨረሻ በሆነው በታላቁ ቀን
ኢየሱስ ቆመና ድምፁን ከፍ አድርጎ እንዲህ
አለ፥ “ውሃ የጠማው ቢኖር ወደ እኔ መጥቶ
ይጠጣ፤ 38 በእኔ የሚያምን፥ መጽሐፍ እንደ
ሚለው፥ የሕይወት ውሃ ምንጭ ከውስጡ ይፈ
ልቃል።” 39 ይህንንም የተናገረው በእርሱ የሚ
ያምኑ ስለሚቀበሉት ስለ መንፈስ ቅዱስ ነበር።
ምክንያቱም ኢየሱስ የሚከብርበት ጊዜ ስላልደ
ረሰ፥ መንፈስ ቅዱስ ገና አልተሰጠም ነበር።

### በሕዝቡ መካከል መለያየት ሆነ

40 ስለዚህ ከሕዝቡ አንዳንዶቹ ይህን ቃል
በሰሙ ጊዜ “ይመጣል የተባለው ነቢይ በእር
ግጥ ይህ ነው” አሉ።
41 ሌሎች “ይህ መሲሕ ነው” አሉ።
ሌሎቹ ግን “መሲሕ የሚመጣው ከገሊላ
ነውን? 42 መሲሕ ከዳዊት ዘር እንደሚወለድና
ከዳዊት ከተማ ከቤተልሔም እንደሚመጣ በመ
ጽሐፍ ተጽፎ የለምን?” አሉ። 43 ስለዚህ በእ
ርሱ ምክንያት በሕዝቡ መካከል መለያየት
ሆነ። 44 አንዳንዶቹ ሊይዙት ፈልገው ነበር፤
ነገር ግን ማንም አልያዘውም።

### የአይሁዳውያን ባለሥልጣኖች አለማመን

45 ከዚህ በኋላ ወታደሮቹ ወደ ካህናት አለቆ
ችና ወደ ፈሪሳውያን ሄዱ፤ እነርሱም “ስለምን
አላመጣችሁትም?” አሉአቸው።
46 ወታደሮቹም “ይህ ሰው እንደሚናገረው
ዐይነት ማንም ተናግሮ አያውቅም” ሲሉ
መለሱ።
47 ፈሪሳውያን ግን እንዲህ አሉ፥ “እናንተም
ደግሞ ተሳሳታችሁን? 48 ለመሆኑ ከባለ ሥልጣ
ኖች ወይም ከፈሪሳውያን በእርሱ ያመኑ አሉን?
49 ይህ የሙሴን ሕግ የማያውቅ ሕዝብ በእርግጥ
የተረገመ ነው።”
50 ከዚህ በፊት ወደ ኢየሱስ ሄዶ የነበረውና
ከፈሪሳውያን አንዱ የሆነው ኒቆዲሞስ፥
51 “በሕጋችን መሠረት አንድ ሰው የክስ መልስ
አስቀድሞ ሳይሰማለትና ምን እንዳደረገ ሳይታ
ወቅ ይፈረድበታልን?” አላቸው።

52 እነርሱም “አንተም ከገሊላ ነህን? ነቢይ
ከገሊላ እንደማይነሣ መርምረህ ተረዳ”
አሉት። [53 እያንዳንዱም ወደየቤቱ ሄደ።

## ምዕራፍ 8

### በምንዝር የተያዘችው ሴት

1 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ወደ ደብረ ዘይት
ሄደ። 2 በማግሥቱም ጠዋት በማለዳ ወደ ቤተ
መቅደስ ተመልሶ መጣ፤ ሕዝቡም ሁሉ ወደ
እርሱ መጡ፤ እርሱም ተቀምጦ ያስተምር
ጀመር። 3 የሙሴ ሕግ መምህራንና ፈሪሳው
ያን፥ ስታመነዝር የተያዘች ሴት አመጡና በሕ
ዝቡ መካከል አቆሙአት። 4 ኢየሱስንም እን
ዲህ አሉት፥ “መምህር ሆይ! እነሆ ይህች ሴት
ስታመነዝር ተይዛለች፤ 5 እንዲህ ዐይነትዋ ሴት
በድንጋይ ተወግራ እንድትሞት ሙሴ በሕጋችን
አዝዞናል፤ አንተስ ስለ እርስዋ ምን ትላለህ?”
6 ይህንንም ያሉት በእርሱ ላይ የክስ ምክንያት
እንዲያገኙ ሊፈትኑት ፈልገው ነበር፤ ኢየሱስ
ግን ጐንበስ ብሎ በጣቱ በመሬት ላይ ይጽፍ
ጀመር።
7 ደጋግመው በጠየቁት ጊዜ ቀና አለና “ከእ
ናንተ መካከል ኃጢአት የሌለበት በመጀመሪያ
ድንጋይ ይወርውርባት” አላቸው። 8 ከዚህም
በኋላ እንደገና ጐንበስ ብሎ በመሬት ላይ ጻፈ።
9 እነርሱም ይህን በሰሙ ጊዜ ከሽማግሌዎቹ
ጀምሮ ሁሉም አንድ በአንድ ከዚያ ሄዱ፤ ስለ
ዚህ ኢየሱስ ከሴትዮዋ ጋር ብቻውን ቀረ።
10 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ቀና ብሎ “አንቺ ሴት
ከሳሾችሽ የት አሉ? የፈረደብሽ ማንም የለ
ምን?” አላት።
11 እርስዋም “ጌታ ሆይ! ማንም የለም”
አለች።
ኢየሱስም “እኔም አልፈርድብሽም፤ ሂጂ፥
ዳግመኛ ኃጢአት አትሥሪ” አላት።][6*]

### ኢየሱስ የዓለም ብርሃን

12 እንደገናም ኢየሱስ “እኔ የዓለም ብርሃን
ነኝ፤ እኔን የሚከተል ሁሉ የሕይወት ብርሃን
ያገኛል፤ በጨለማም አይመላለስም” ሲል ተናገ
ራቸው።
13 ፈሪሳውያን “አንተ ስለ ራስህ ትመሰክራ
ለህ፤ ምስክርነትህ እውነት አይደለም” አሉት።
14 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
“ምንም እንኳ እኔ ስለ ራሴ ብመሰክር፥ ከየት
እንደመጣሁ፥ ወዴትም እንደምሄድ ስለማውቅ
ምስክርነቴ እውነት ነው፤ እናንተ ግን ከየት
እንደመጣሁና ወዴት እንደምሄድ አታውቁም።

[6*] 8፡11 ብዙ ቅጂዎችና የጥንት ትርጉሞች ይህን ክፍል (7፡53–8፡11) አይጨምሩም፤ አንዳንዶቹ ከዮሐ. 21፡24 በኋላ ያስገቡታል፤ ሌሎች ደግሞ ከሉቃ. 21፡38 በኋላ ያስገቡታል፤ አንድ ቅጂ ደግሞ ከዮሐ. 7፡36 በኋላ አስገብቶታል።

7፡37 ፡- ዘሌ. 23፡36። 7፡38 ፡- ሕዝ. 47፡1፤ ዘካ. 14፡8። 7፡42 ፡- 2ሳሙ. 7፡12፤ ሚክ. 5፡2። 7፡50 ፡- ዮሐ. 3፡1-2።
8፡5 ፡- ዘሌ. 20፡10፤ ዘዳ. 22፡22-24። 8፡12 ፡- ማቴ. 5፡14፤ ዮሐ. 9፡5። 8፡13 ፡- ዮሐ. 5፡31።



15 እናንተ በሥጋዊ አስተሳሰብ ትፈርዳላችሁ፤
እኔ በማንም ላይ አልፈርድም። 16 እኔ ብፈር
ድም ፍርዴ እውነት ነው፤ ምክንያቱም እኔ
ብቻዬን አልፈርድም፤ የላከኝ አብ ከእኔ ጋር
ነው። 17 የሁለት ሰዎች ምስክርነት እውነት
እንደሆነ በሕጋችሁ ተጽፎአል። 18 ስለዚህ እኔ
ስለራሴ እመሰክራለሁ፤ የላከኝ አብም ስለ እኔ
ይመሰክራል።”
19 እነርሱም “አባትህ የት አለ?” ሲሉ ጠየ
ቁት።
ኢየሱስም “እኔንም ሆነ አባቴን አታው
ቁም፤ እኔን ብታውቁኝ ኖሮ አባቴንም ባወቃ
ችሁ ነበር” ሲል መለሰላቸው።
20 ኢየሱስ ይህን ቃል የተናገረው በቤተ
መቅደስ፥ በገንዘብ መቀበያ ሣጥን አጠገብ ሲያ
ስተምር ነው። ታዲያ ጊዜው ገና ስላልደረሰ
ማንም አልያዘውም።

### ስለ አለማመን የተሰጠ ማስጠንቀቂያ

21 እንደገናም ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፥
“እኔ እሄዳለሁ፤ እናንተም እኔን ትፈልጉኛላ
ችሁ፤ ነገር ግን ከነኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ፤
እኔ ወደምሄድበት እናንተ ልትመጡ አትች
ሉም።”
22 አይሁዳውያን ባለሥልጣኖችም “‘እኔ
ወደምሄድበት እናንተ ልትመጡ አትችሉም’
ማለቱ ራሱን ሊገድል ይሆን?” ተባባሉ።
23 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፥ “እና
ንተ ከታች ናችሁ፤ እኔ ከላይ ነኝ፤ እናንተ
ከዚህ ዓለም ናችሁ፤ እኔ ከዚህ ዓለም አይደለ
ሁም፤ 24 ከነኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ ያልሁ
አችሁ ስለዚህ ነው፤ ምክንያቱም የእኔን ማን
ነት ሀውቃችሁ ባታምኑ ከነኃጢአታችሁ ትሞ
ታላችሁ።”
25 እነርሱም “አንተ ማን ነህ?” አሉት።
ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፥ “ከመጀመሪያ
አንሥቼ እንደ ነገርሁአችሁ ነኝ፤ 26 ስለ እና
ንተ የምናገረውና የምፈርደው ብዙ ነገር
አለኝ፤ ይሁን እንጂ የላከኝ እውነተኛ ነው፤
እኔም ለዓለም የምናገረው ከእርሱ የሰማሁትን
ብቻ ነው።”
27 እነርሱ ግን ስለ አብ እንደተናገራቸው
አልገባቸውም። 28 ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ አላ
ቸው፥ “የሰውን ልጅ ከፍ አድርጋችሁ በምትሰ
ቅሉት ጊዜ እኔ ‘ያለሁና የምኖር’ እንደሆንሁ
ታውቃላችሁ፤ እንዲሁም አብ ያስተማረኝን
እንደምናገር እንጂ በራሴ ሥልጣን ብቻ ምንም
እንደማላደርግ ያን ጊዜ ታስተውላላችሁ።
29 የላከኝ ከእኔ ጋር ነው፤ ዘወትር የማደርገው
እርሱን ደስ የሚያሰኘውን ነገር ስለሆነ ብቻዬን
አልተወኝም።”

30 ኢየሱስ ይህን በተናገረ ጊዜ ብዙ ሰዎች
በእርሱ አመኑ።

### ከኃጢአት ባርነት ነፃ ስለመውጣት

31 ኢየሱስ በእርሱ ላመኑት አይሁዳውያን
እንዲህ አለ፥ “እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእር
ግጥ ደቀ መዛሙርቴ ትሆናላችሁ፤ 32 እውነትን
ታውቃላችሁ፤ እውነትም ነፃ ያወጣችኋል።”
33 እነርሱ ግን “እኛ የአብርሃም ዘር ነን፤
ከቶ ለማንም ባሪያ ሆነን አናውቅም፤ ታዲያ
አንተ ‘ነፃ ትወጣላችሁ’ የምትለን እንዴት
ነው?” አሉት።
34 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፥
“እውነት፥ እውነት እላችኋለሁ፥ ኃጢአት
የሚሠራ ሁሉ የኃጢአት ባሪያ ነው፤ 35 ባሪያ
ሁልጊዜ በቤት ውስጥ አይኖርም፤ ልጅ ግን
ሁልጊዜ በቤት ውስጥ ይኖራል። 36 ስለዚህ
ወልድ ነፃ ካወጣችሁ፥ በእርግጥ ነፃ ትሆናላ
ችሁ። 37 የአብርሃም ዘር መሆናችሁንማ ዐውቃ
ለሁ፤ ነገር ግን ቃሌን ስለማትቀበሉ ልትገድ
ሉኝ ትፈልጋላችሁ። 38 እኔ ከአባቴ ዘንድ ያየሁ
ትን እናገራለሁ፤ እናንተ ግን ከአባታችሁ የሰማ
ችሁትን ታደርጋላችሁ።”
39 እነርሱም “አባታችንማ አብርሃም ነው”
ሲሉ መለሱለት።
ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፥ “የአብርሃም
ልጆችስ ብትሆኑ ኖሮ የአብርሃምን ሥራ በሠራ
ችሁ ነበር፤ 40 እኔ ከእግዚአብሔር የሰማሁትን
እውነት ነገርኋችሁ፤ እናንተ ግን ልትገድሉኝ
ትፈልጋላችሁ፤ አብርሃም እንዲህ አላደረገም።
41 እንግዲህ እናንተ የምትሠሩት የአባታችሁን
ሥራ ነው።”
እነርሱም “እኛ በምንዝር የተወለድን ዲቃላ
ዎች አይደለንም፤ አንድ አባት አለን፤ እርሱም
እግዚአብሔር ነው” አሉት።
42 ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፥ “እግዚአብ
ሔር አባታችሁ ቢሆንማ እኔን በወደዳችሁኝ
ነበር፤ ምክንያቱም እኔ እዚህ ያለሁት ከእግዚ
አብሔር ዘንድ መጥቼ ነው፤ የላከኝ እርሱ
ነው እንጂ እኔ በራሴ ሥልጣን አልመጣሁም።
43 ስለ ምን ንግግሬ አይገባችሁም? ቃሌን መቀ
በል ስለማትፈልጉ ነው። 44 እናንተ የአባታ
ችሁ የዲያብሎስ ልጆች ናችሁ፤ ፍላጎታች
ሁም የአባታችሁን ምኞት መፈጸም ነው፤
እርሱ ከመጀመሪያ አንሥቶ ነፍሰ ገዳይ ነበረ፤
እውነት በእርሱ ስለሌለ ከእውነት ጋር ምንም
ግንኙነት የለውም፤ እርሱ ሐሰተኛና የሐሰት
አባት ስለሆነ ሐሰት በሚናገርበት ጊዜ ከገዛ
ራሱ አውጥቶ ይናገራል። 45 እኔ ግን እውነትን
የምናገር ስለሆንሁ አታምኑኝም፤ 46 ለመሆኑ
ከእናንተ ‘ኃጢአተኛ ነህ’ ብሎ የሚወቅሰኝ

8፡33 ፡- ማቴ. 3፡9፤ ሉቃ. 3፡8።

ማን ነው? እውነትን የምናገር ከሆንሁ ታዲያ
ለምን አታምኑኝም? 47 ከእግዚአብሔር የሆነ
የእግዚአብሔርን ቃል ይሰማል ፤ እንግዲህ እና
ንተ የእግዚአብሔርን ቃል የማትሰሙት ከእግ
ዚአብሔር ስላልሆናችሁ ነው ።”

### ኢየሱስ ከአብርሃም በፊት ነበረ

48 አይሁዳውያንም “አንተ ሳምራዊ ነህ ፤
ጋኔንም አለብህ ፤ ማለታችን ልክ አይደለምን?”
አሉት ።
49 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፤
“እኔ ጋኔን የለብኝም ፤ ነገር ግን አባቴን አከብ
ራለሁ ፤ እናንተም ታዋርዱኛላችሁ ። 50 ይሁን
እንጂ እኔ የራሴን ክብር አልፈልግም ፤ የእኔን
መክበር የሚፈልግና የሚፈርድ ሌላ አለ ።
51 እውነት ፤ እውነት እላችኋለሁ ፤ ቃሌን የሚ
ጠብቅ ከቶ አይሞትም ።”
52 አይሁዳውያንም እንዲህ አሉት ፤ “ጋኔን
እንዳለብህ አሁን ዐወቅን ፤ አብርሃም እንኳ
ሞቶአል ፤ ነቢያትም ሞተዋል ፤ አንተ ግን
‘ቃሌን የሚጠብቅ ከቶ አይሞትም’ ትላለህ ፤
53 ለመሆኑ አንተ ከሞተው አባታችን ከአብር
ሃም ትበልጣለህን?” ነቢያት ሞተዋል ፤ ታዲያ
አንተ ራስህን ማን ትላለህ?
54 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ ፤ “እኔ የራ
ሴን ክብር ብፈልግ ፤ ክብሬ ዋጋ የለውም ፤
እኔን የሚያከብረኝ አባቴ ነው ፤ እርሱም ‘አም
ላካችን’ የምትሉት ነው ። 55 እናንተ ግን እር
ሱን አላወቃችሁትም ፤ እኔ ዐውቀዋለሁ ፤ እኔ
አላውቀውም ብል ፤ እንደ እናንተ ሐሰተኛ በሆ
ንሁ ነበር ፤ እኔ ግን ዐውቀዋለሁ ፤ ቃሉንም
እጠብቃለሁ ። 56 የአባታችሁ የአብርሃም
ምኞት የእኔን ቀን አይቶ ለመደሰት ነበር ፤ አይ
ቶም ተደሰተ ።”
57 በዚህ ጊዜ አይሁዳውያን “አንተ ገና
ኀምሳ ዓመት አልሆነህም ታዲያ እንዴት አብር
ሃምን አየሁ ትላለህ?” አሉት ።
58 ኢየሱስም “እውነት ፤ እውነት እላችኋ
ለሁ ፤ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ” አላ
ቸው ።
59 ስለዚህ አይሁዳውያን ሊወግሩት ድንጋይ
አነሡ ፤ ኢየሱስ ግን ተሰወረባቸውና ከቤተ
መቅደስ ወጥቶ ሄደ ።

## ምዕራፍ 9

### ኢየሱስ ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው አዳነ

1 ኢየሱስ በመንገድ ሲያልፍ ፤ ዕውር ሆኖ
የተወለደውን ሰው አየ ። 2 ደቀ መዛሙርቱ ኢየ
ሱስን “መምህር ሆይ! ይህ ሰው ዕውር ሆኖ
የተወለደው በማን ኀጢአት ምክንያት ነው?
በራሱ ኃጢአት ነውን ወይስ በወላጆቹ?” ሲሉ
ጠየቁት ።
3 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ ፤ “ይህ የታ
ወረው በእርሱ ወይም በወላጆቹ ኀጢአት ምክ
ንያት አይደለም ፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር
ሥራ በእርሱ እንዲገለጥ ነው ። 4 ቀን ሆኖ ሳለ
የላከኝን ሥራ መሥራት አለብኝ ፤ ማንም ሰው
ሊሠራ የማይችልበት ሌሊት ይመጣል ። 5 በዓ
ለም ላይ ሳለሁ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ ።”
6 ይህን ከተናገረ በኋላ በመሬት ላይ እንትፍ
አለና በምራቁ ዐፈር ለወሰ ፤ በጭቃውም የዕው
ሩን ዐይኖች ቀባና ፤ 7 “ሄደህ በሰሊሆም መጠ
መቂያ ታጠብ” አለው ። (ሰሊሆም የተላከ
ማለት ነው ።) ስለዚህ ሰውየው ሄዶ ታጠበና
እያየ ተመለሰ ።
8 ጐረቤቶቹና ቀድሞ ሲለምን ያዩት የነበሩ
ሰዎች “ይህ ሰው ያ ተቀምጦ ይለምን የነበረው
አይደለምን?” አሉ ።
9 አንዳንዶች “አዎ እርሱ ነው!” አሉ ፤
ሌሎች ደግሞ “እርሱን ይመስላል እንጂ እርሱ
አይደለም!” አሉ ።
እርሱ ግን “እኔው ነኝ” አለ ።
10 ሰዎቹም “ታዲያ ዐይኖችህ እንዴት ተከ
ፈቱ?” አሉት ።
11 እርሱም “ኢየሱስ የተባለ ሰው ጭቃ
ለውሶ ዐይኖቼን ቀባና ‘ወደ ሰሊሆም ሄደህ
ታጠብ’ አለኝ ፤ እኔም ሄጄ ታጠብሁና ለማየት
ቻልሁ” ሲል መለሰ ። 12 እነርሱም “ሰውየው
አሁን የት አለ?” አሉት ። እርሱም “የት እን
ዳለ እኔ አላውቅም” አላቸው ።
13 ከዚህ በኋላ ሰዎቹ ዕውር የነበረውን ሰው
ወደ ፈሪሳውያን ወሰዱት ። 14 ኢየሱስ ጭቃ
ለውሶ የሰውየውን ዐይኖች ያዳነው በሰንበት
ቀን ነበር ፤ 15 ፈሪሳውያን “እንዴት ማየት
ቻልህ?” ብለው ሰውየውን እንደገና ጠየቁት ።
እርሱም “ዐይኖቼ ላይ ጭቃ አደረገልኝና ታጠ
ብሁ ፤ ስለዚህ ማየት ቻልሁ” አለ ።
16 በዚህ ጊዜ ከፈሪሳውያን አንዳንዶቹ “ይህ
ሰው ሰንበትን ስለማያከብር ከእግዚአብሔር አይ
ደለም” አሉ ።
ሌሎች ግን “ታዲያ ኀጢአተኛ የሆነ ሰው
እነዚህን ተአምራት እንዴት ማድረግ ይች
ላል?” አሉ ። በዚህ ምክንያት በመካከላቸው
መለያየት ሆነ ።
17 ስለዚህ ዕውር የነበረውን ሰው “አንተስ
ዐይኖችህን አዳነልኝ ስለምትለው ስለዚያ ሰው
ምን ትላለህ?” ሲሉ ደግመው ጠየቁት ።
እርሱም “ነቢይ ነው” አለ ።
18 ይህ ሰው ዕውር እንደነበረና ዐይኖቹም
በኋላ እንደተከፈቱ ወላጆቹን ጠርተው እስከ





ጠየቁአቸው ድረስ አይሁዳውያን ባለሥልጣኖች
አላመኑም ነበር ። 19 ስለዚህ ወላጆቹን “ዕውር
ሆኖ ተወለደ የምትሉት ልጃችሁ ይህ ነውን?
አሁንስ እንዴት ማየት ቻለ?” ሲሉ ጠየቁአ
ቸው ።
20 ወላጆቹም እንዲህ ሲሉ መለሱ ፤ “ይህ
ሰው ልጃችን መሆኑንና ዕውር ሆኖ መወለዱን
እናውቃለን ፤ 21 ነገር ግን አሁን እንዴት እንደ
ሚያይና ዐይኖቹንም ማን እንደአዳነለት አናው
ቅም ፤ እርሱን ጠይቁት ፤ እርሱ በዕድሜው
ሙሉ ሰው ስለሆነ ስለ ራሱ መናገር ይች
ላል ።” 22 ወላጆቹ ይህን ያሉት አይሁዳውያን
ባለሥልጣኖችን በመፍራት ነበር ፤ ምክንያቱም
ኢየሱስን “መሲሕ ነው” የሚል ሰው ቢኖር
ከምኵራብ ሊያስወጡት አይሁዳውያን ባለሥል
ጣኖች ተስማምተው ስለ ነበር ነው ። 23 ስለዚህ
ወላጆቹ “እርሱ በዕድሜው ሙሉ ሰው ነው ፤
እርሱን ጠይቁት” አሉ ።
24 በዚህ ምክንያት ዕውር የነበረውን ሰው
እንደገና ጠርተው “አንተ እውነቱን በመናገር
እግዚአብሔርን አክብር ፤ ይህ ሰው ኀጢአተኛ
መሆኑን እኛ እናውቃለን” አሉት ።
25 ዕውር የነበረውም ሰው “እርሱ ኀጢአ
ተኛ መሆኑን እኔ አላውቅም ፤ እኔ የማውቀው
ዕውር እንደነበርሁና አሁን ማየት እንደቻልሁ
ብቻ ነው” ሲል መለሰ ።
26 እነርሱም “ምን አደረገልህ? ዐይኖችህንስ
ያዳነው እንዴት ነው?” አሉት ።
27 እርሱም “አስቀድሜ ነገርኋችሁ ፤ እና
ንተ ግን መስማት አልፈለጋችሁም ፤ ታዲያ ስለ
ምን እንደገና መስማት ትፈልጋላችሁ? እናን
ተም የእርሱ ደቀ መዛሙርት መሆን ትፈልጋላ
ችሁን?” አላቸው ።
28 እነርሱም እንዲህ እያሉ ሰደቡት ፤ “የእር
ሱስ ደቀ መዝሙር አንተ ነህ ፤ እኛ ግን የሙሴ
ደቀ መዛሙርት ነን ፤ 29 እግዚአብሔር ሙሴን
እንዳነጋገረው እናውቃለን ፤ ይህ ሰው ግን ከየት
እንደሆነ አናውቅም ።”
30 ሰውየውም እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፤
“ይህ ሰው ከየት እንደሆነ አለማወቃችሁ ያስደ
ንቃል! ነገር ግን ዐይኖቼን ያዳነ እርሱ ነው ።
31 እግዚአብሔር ኀጢአተኞችን እንደማይሰማ
የታወቀ ነው ፤ ነገር ግን እግዚአብሔርን የሚፈ
ራና ፈቃዱንም የሚፈጽም ሲኖር እርሱን እግ
ዚአብሔር ይሰማዋል ። 32 ዕውር ሆኖ የተወለደ
ውን ሰው ዐይኖች ያዳነ አለ ሲባል ፤ ዓለም ከተ
ፈጠረ ጀምሮ ተሰምቶ አይታወቅም ። 33 ይህ
ሰው ከእግዚአብሔር ባይሆን ኖሮ ምንም ለማድ
ረግ ባልቻለም ነበር ።”
34 እነርሱም “ሁለንተናህ በኀጢአት ተወርሶ
የተወለድህ! አንተ እኛን ልታስተምር ነውን?”
አሉና ከምኵራብ አስወጡት ።

### የልብ ዕውርነት

35 ሰውየውን ከምኵራብ እንዳስወጡት ኢየ
ሱስ ሰማ ፤ ባገኘውም ጊዜ “የሰው ልጅ በሆ
ነው በክርስቶስ ታምናለህን?” አለው ።
36 እርሱም “ጌታ ሆይ! በእርሱ እንዳምን
እርሱ ማንነው?” አለ ።
37 ኢየሱስ “ገና ድሮ አይተኸዋል ፤ አሁንም
የሚያነጋግርህ እርሱ ነው” አለው ።
38 እርሱም “ጌታ ሆይ! አምናለሁ” ብሎ
ሰገደለት ።
39 ኢየሱስም “የማያዩ እንዲያዩ ፤ የሚያዩም
እንዲታወሩ ፤ እኔ ወደዚህ ዓለም ለፍርድ መጥ
ቼአለሁ” አለ ።
40 በዚያን ጊዜ በኢየሱስ አጠገብ የነበሩ ፈሪ
ሳውያን “ታዲያ እኛም ዕውሮች መሆናችን
ነውን?” አሉት ።
41 ኢየሱስም “ዕውሮች ብትሆኑማ ኖሮ
ኀጢአት ባልሆነባችሁም ነበር ፤ አሁን ግን እና
ያለን ስለምትሉ ኀጢአተኞች ሆናችሁ ትቀራላ
ችሁ” አላቸው ።

## ምዕራፍ 10

### ኢየሱስ መልካም እረኛ ነው

1 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፤ “እው
ነት ፤ እውነት እላችኋለሁ ፤ ወደ በጎች በረት
በበር ሳይሆን በሌላ በኩል የሚገባ ሰው ሌባና
ወንበዴ ነው ። 2 በበሩ የሚገባ ግን የበጎች
እረኛ ነው ። 3 ለእርሱ የበር ጠባቂው በሩን ይከ
ፍትለታል ፤ በጎቹ ድምፁን ይሰማሉ ፤ እርሱም
የራሱን በጎች በየስማቸው ይጠራቸዋል ፤ እየመ
ራም ወደ ውጭ ይወስዳቸዋል ። 4 የራሱን በጎች
ካስወጣ በኋላም እፊት እፊታቸው ይሄዳል ።
በጎቹም ድምፁን ስለሚያውቁ ይከተሉታል ።
5 የሌላውን ድምፅ ግን ስለማያውቁ ከእርሱ ይሸ
ሻሉ እንጂ አይከተሉም ።”
6 ኢየሱስ ይህን ምሳሌ ነገራቸው ፤ እነርሱ
ግን የተናገረውን አላስተዋሉም ።
7 ስለዚህ ኢየሱስ እንደገና እንዲህ አላቸው ፤
“እውነት ፤ እውነት እላችኋለሁ ፤ እኔ የበጎች
በር ነኝ ፤ 8 ከእኔ በፊት የመጡት ሁሉ ሌቦችና
ወንበዴዎች ናቸው ፤ በጎቹ ግን አልሰሙአቸ
ውም ። 9 በሩ እኔ ነኝ ፤ በእኔ በኩል የሚገባ
ይድናል ፤ ይገባል ፤ ይወጣል ፤ መሠማሪያም
ያገኛል ። 10 ሌባው የሚመጣው ለመስረቅና
ለማረድ ለማጥፋትም ብቻ ነው ፤ እኔ ግን የመ
ጣሁት ሕይወት እንዲያገኙና የተትረፈረፈ ሕይ
ወት እንዲኖራቸው ነው ።
11 “መልካም እረኛ እኔ ነኝ ፤ መልካም
እረኛ ሕይወቱን ስለ በጎቹ አሳልፎ ይሰጣል ።
12 በጎቹ የራሱ ያልሆኑ ቅጥረኛ እንጂ እውነ
ተኛ ያልሆነ እረኛ ግን ፤ ተኵላ ሲመጣ ባየ

ጊዜ በጎቹን ትቶ ይሸሻል ፤ ተኲላውም በጎቹን
ነጥቆ ይበታትናቸዋል ። 13 እረኛው የሚሸሸ
ውም ቅጥረኛ ስለሆነና ለበጎቹም ስለማያስብ
ነው ። 14 መልካም እረኛ እኔ ነኝ ፤ እኔ በጎቼን
ዐውቃለሁ ፤ በጎቼም እኔን ያውቁኛል ። 15 እኔ
እነርሱን የማውቃቸው ፥ አብ እኔን እንደሚያ
ውቀኝና እኔም አብን እንደማውቀው ዐይነት
ነው ፤ እኔ ስለ በጎቼ ሕይወቴን አሳልፌ እሰጣ
ለሁ ። 16 በዚህ መንጋ ውስጥ ያልሆኑ ሌሎች
በጎች አሉኝ ፤ እነርሱንም ማምጣት ይገባኛል ፤
እነርሱ ድምፄን ይሰማሉ ፤ አንድ መንጋም ይሆ
ናሉ ፤ እረኛውም አንድ ይሆናል ።
17 "እንደገና መልሼ የምወስዳትን ሕይወ
ቴን አሳልፌ ለመስጠት ፈቃደኛ ስለሆንሁ አብ
እኔን ይወድደኛል ። 18 ሕይወቴን በፈቃዱ አሳ
ልፌ እሰጣለሁ እንጂ ከእኔ የሚወስዳት ማንም
የለም ፤ ሕይወቴን አሳልፌ ለመስጠትና መል
ሼም ለመውሰድ መብት አለኝ ፤ ይህን ትእዛዝ
የተቀበልሁት ከአባቴ ነው ።"
19 ከዚህ ንግግር የተነሣ በአይሁዳውያን መካ
ከል እንደገና መለያየት ሆነ ። 20 ከእነርሱም
ብዙዎቹ "እርሱ ጋኔን አለበት ፤ አብዶአል ፤
ስለምን ትሰሙታላችሁ?" አሉ ።
21 ሌሎች "ይህ ንግግር ጋኔን ካለበት ሰው
እንደበት የሚወጣ አይደለም ፤ ጋኔን የዕውሮችን
ዐይን ማዳን ይችላልን?" አሉ ።

### ኢየሱስ የሰው ልጅ ነው

22 በኢየሩሳሌም የቤተ መቅደስ መታደስ
በዓል የሚከበርበት ጊዜ ደረሰ ፤ ወራቱም ክረ
ምት ነበር ፤ 23 ኢየሱስ በቤተ መቅደስ በሰሎ
ሞን መተላለፊያ ይመላለስ ነበር ። 24 በዚያን
ጊዜ አይሁዳውያን በዙሪያው ተሰብስበው
"እስከ መቼ በጥርጣሬ ታቆየናለህ? አንተ
መሲሕ እንደሆንህ በግልጥ ንገረን" አሉት ።
25 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፥
"እኔ ፥ ነግሬአችኋለሁ ፤ እናንተ ግን አታም
ኑም ፤ በአባቴ ስም የምሠራው ሥራ ስለ እኔ
ይመሰክራል ። 26 እናንተ ግን ከበጎቼ መንጋ ስላ
ልሆናችሁ አታምኑም ። 27 በጎቼ ድምፄን ይሰ
ማሉ ፤ እኔም ዐውቃቸዋለሁ ፤ እነርሱም ይከተ
ሉኛል ። 28 እኔ የዘላለም ሕይወት እሰጣቸዋ
ለሁ ፤ ስለዚህ ከቶ አይጠፉም ፤ ከእኔ እጅ
ማንም ነጥቆ አይወስዳቸውም ። 29 እነርሱን
ለእኔ የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል ። ከአብ
እጅ እነርሱን ነጥቆ መውሰድ የሚችል ማንም
የለም ። 30 እኔና አብ አንድ ነን ።"
31 በዚህ ጊዜ አይሁዳውያን ኢየሱስን ለመው
ገር እንደገና ድንጋይ አነሡ ። 32 ኢየሱስም
"ከአብ የተሰጡኝን ብዙ መልካም ሥራዎች
አሳየኋችሁ ፤ ታዲያ የምትወግሩኝ ስለየትኛው
ሥራ ነው?" አላቸው ።
33 እነርሱም "እኛ የምንወግርህ በእግዚአብ
ሔር ላይ የስድብ ቃል ስለመናገርህ ነው እንጂ
ስለ መልካም ሥራህ አይደለም ፤ እንዲሁም
አንተ ሰው ሆንህ ሳለ ራስህን አምላክ ስላደረግህ
ነው" ሲሉ መለሱለት ።
34 ኢየሱስም እንዲህ አላቸው ፥ "በሕጋች
ሁስ 'እናንተ አማልክት ናችሁ አልሁ' የሚል
ተጽፎ የለምን? 35 የእግዚአብሔር ቃል የማይ
ሻር መሆኑ የታወቀ ነው ፤ እንግዲህ እነዚያን
የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸውን ሁሉ 'አማ
ልክት' ብሎ ጠርቶአቸዋል ። 36 ታዲያ አብ የቀ
ደሰውንና ወደ ዓለም የላከውን 'የእግዚአብሔር
ልጅ ነኝ' ስላለ 'በእግዚአብሔር ላይ የስድብ
ቃል ትናገራለህ' ትሉታላችሁን? 37 እኔ የአባ
ቴን ሥራ የማልሠራ ከሆንሁ አትመኑኝ ።
38 የአባቴን ሥራ የምሠራ ከሆንሁ ግን በእኔ
እንኳ ባታምኑ በሥራዬ እመኑ ፤ በዚህ ዐይ
ነት ፥ አብ በእኔ እንደሆነና እኔም በአብ እንደ
ሆንሁ በሚገባ ታውቃላችሁ ።"
39 እነርሱም እንደገና ሊይዙት ፈለጉ ፤
እርሱ ግን ከእጃቸው አምልጦ ሄደ ።
40 እንደገናም 'ዮርዳኖስን ተሻግሮ ዮሐንስ
መጀመሪያ ያጠምቅበት ወደነበረው ስፍራ
መጣ ፤ በዚያም ቆየ ። 41 ብዙ ሰዎች ወደ
እርሱ መጥተው "ዮሐንስ ምንም ተአምር አላ
ደረገም ፤ ነገር ግን ዮሐንስ ስለዚህ ሰው የተናገ
ረው ሁሉ እውነት ነው" አሉ ። 42 እዚያም
ብዙ ሰዎች በእርሱ አመኑ ።

## ምዕራፍ 11

### የአልዓዛር መሞት

1 በቢታንያ የሚኖር አልዓዛር የሚባል ሰው
ታሞ ነበር ፤ ቢታንያ ማርያምና እኅትዋ ማርታ
የሚኖሩባት መንደር ነበረች ። 2 ማርያም የጌታን
እግር ሽቶ የቀባችውና በጠጕርዋ ያበሰችው
ናት ፤ የታመመውም አልዓዛር የእርስዋ ወንድም
ነበር ። 3 እኅትማማቾቹም "ጌታ ሆይ! ወዳጅህ
ታሞአል" ብለው ወደ ኢየሱስ ላኩበት ።
4 ኢየሱስም ይህን በሰማ ጊዜ "ይህ ሕመም
ለሞት የሚያደርስ አይደለም ፤ ነገር ግን ለእግዚ
አብሔር ክብር እንዲሆንና የእግዚአብሔር
ልጅም በዚህ ምክንያት እንዲከበር ነው" አለ ።
5 ኢየሱስ ማርታንና እኅትዋን ማርያምን ወን
ድማቸውን አልዓዛርንም ይወድድ ነበር ።
6 ሆኖም የአልዓዛርን መታመም በሰማ ጊዜ በነበ
ረበት ቦታ ሁለት ቀን ቆየ ። 7 ከዚህ በኋላ ደቀ
መዛሙርቱን "ወደ ይሁዳ ክፍለ ሀገር እንደገና
እንሂድ" አላቸው ።

10፥15 ፦ ማቴ. 11፥27 ፤ ሉቃ. 10፥22 ። 10፥33 ፦ ዘሌ. 24፥16 ። 10፥34 ፦ መዝ. 82፥6 ። 10፥40 ፦ ዮሐ. 1፥28 ።
11፥1 ፦ ሉቃ. 10፥33-39 ። 11፥2 ፦ ዮሐ. 12፥3 ።



8 ደቀ መዛሙርቱም "መምህር ሆይ! አይሁ
ዳውያን ከጥቂት ጊዜ በፊት ሊወግሩህ ይፈልጉ
ነበር ፤ ታዲያ እንደገና ወደዚያ ተመልሰህ ትሄ
ዳለህን?" አሉት ።
9 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፥
"በቀን ውስጥ ያለው ጊዜ ዐሥራ ሁለት ሰዓት
አይደለምን! በቀን የሚመላለስ የዚህን ዓለም
ብርሃን ስለሚያይ አይሰናከልም ። 10 ነገር ግን
በሌሊት የሚመላለስ ብርሃን ስለሌለው ይሰናከ
ላል ።" 11 ኢየሱስ ይህን ካላቸው በኋላ "ወዳጃ
ችን አልዓዛር አንቀላፍቶአል ፤ እኔ ግን ከእንቅ
ልፉ ላስነሣው እሄዳለሁ" አለ ።
12 ደቀ መዛሙርቱም "ጌታ ሆይ! አንቀላፍ
ቶስ ከሆነ ተሽሎታል ማለት ነው" አሉት ።
13 ኢየሱስ ይህን የተናገረው ስለ አልዓዛር
መሞት ነበር ፤ እነርሱ ግን ስለ እንቅልፍ የተና
ገረ መሰላቸው ። 14 ስለዚህ ኢየሱስ በግልጥ እን
ዲህ አላቸው ፥ "አልዓዛር ሞቶአል ፤ 15 እናንተ
እንድታምኑ እዚያ ባለመኖሬ ስለ እናንተ ደስ
ብሎኛል ፤ አሁን ግን ወደ እርሱ እንሂድ ።"
16 በዚህ ጊዜ ዲዲሞስ[7*] የተባለው ቶማስ
ሌሎቹን ደቀመዛሙርት "ከእርሱ ጋር እንድን
ሞት እኛም እንሂድ" አላቸው ።

### ኢየሱስ ትንሣኤና ሕይወት ነው

17 ኢየሱስ እዚያ በደረሰ ጊዜ አልዓዛር ከተቀ
በረ አራት ቀን ሆኖት ነበር ። 18 ቢታንያ ከኢየ
ሩሳሌም የምትርቀው ሦስት ኪሎ ሜትር ያህል
ነው ። 19 ብዙ አይሁዳውያን ማርታንና ማርያ
ምን ስለ ወንድማቸው ሞት ለማጽናናት ወደ
እነርሱ መጥተው ነበር ።
20 ማርታ የኢየሱስን መምጣት በሰማች ጊዜ
ልትቀበለው ሄደች ፤ ማርያም ግን በቤት ቀርታ
ነበር ። 21 ማርታ ኢየሱስን "ጌታ ሆይ! አንተ
እዚህ ብትሆን ኖሮ ወንድሜ ባልሞተም ነበር ፤
22 ነገር ግን አሁንም የምትለምነውን ሁሉ እግ
ዚአብሔር እንደሚሰጥህ ዐውቃለሁ" አለችው ።
23 ኢየሱስም "ወንድምሽ ከሞት ይነሣል"
አላት ።
24 ማርታም "በመጨረሻው ቀን በትንሣኤ
ጊዜ ከሞት እንደሚነሣ ዐውቃለሁ" አለችው ።
25 ኢየሱስም "ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ ፤
በእኔ የሚያምን ቢሞት እንኳ በሕይወት ይኖ
ራል ፤ 26 በሕይወት የሚኖርና በእኔም የሚያ
ምን ሁሉ ከቶ አይሞትም ፤ ይህን ታምኛለሽ?"
አላት ።
27 እርስዋም "አዎ ጌታ ሆይ! አንተ ወደ
ዓለም የሚመጣው መሲሕ የእግዚአብሔር ልጅ
መሆንህን አምናለሁ" አለችው ።
28 ማርታ ይህን ከተናገረች በኋላ ሄደችና
እኅትዋን ማርያምን "መምህር መጥቶአል ፤ አን
ቺንም ይጠራሻል" ብላ በስውር ጠራቻት ።
29 ማርያም ይህን በሰማች ጊዜ በፍጥነት ተነ
ሥታ ወደ እርሱ ሄደች ። 30 ኢየሱስ ፥ ማርታ
እርሱን በተቀበለችበት ስፍራ ነበር እንጂ ወደ
መንደር ገና አልገባም ነበር ። 31 እርስዋን ለማ
ጽናናት በቤት ውስጥ አብረዋት የነበሩ አይሁዳ
ውያን ፥ ማርያም በፍጥነት ተነሥታ ስትወጣ
አይተው ፥ ወደ አልዓዛር መቃብር ሄዳ የምታለ
ቅስ መስሎአቸው ተከተሉዋት ።
32 ማርያም ኢየሱስ ወደ ነበረበት መጥታ
ባየችው ጊዜ በእግሩ ሥር ወደቀችና "ጌታ
ሆይ! አንተ እዚህ ብትሆን ኖሮ ወንድሜ ባል
ሞተም ነበር" አለችው ።
33 ኢየሱስ እርስዋ ስታለቅስና አብረዋት የመ
ጡትም አይሁዳውያን ሲያለቅሱ ባየ ጊዜ በመን
ፈሱ አዝኖ በመታወክ ፥ 34 "የት ነው የቀበራች
ሁት!" አለ ።
እነርሱም "ጌታ ሆይ ! ና እይ" አሉት ።
35 ኢየሱስም እንባውን አፈሰሰ ። 36 ስለዚህ
አይሁዳውያን "እንዴት ያፈቅረው እንደነበረ
ተመልከቱ" አሉ ።
37 ከእነርሱ አንዳንዶቹ ግን "የዕውሩን ዐይ
ኖች ያበራ ይህ ሰው እንዳይሞት ሊያደርግ አይ
ችልም ነበርን?" አሉ ።

### ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት አስነሣ

38 ኢየሱስ እያዘነ ወደ መቃብሩ ሄደ ፤ መቃ
ብሩ በድንጋይ የተዘጋ ዋሻ ነበር ። 39 ኢየሱስ
"ድንጋዩን አንሡት" አለ ።
የሟቹ እኅት ማርታ "ጌታ ሆይ! ከሞተ
አራት ቀን ሆኖታል ፤ አሁን ይሸታል እኮ" አለ
ችው ።
40 ኢየሱስም "ካመንሽ የእግዚአብሔርን
ክብር ታያለሽ ብዬሽ አልነበረምን?" አላት ።
41 ሰዎቹም ድንጋዩን አነሡት ፤ ከዚህ በኋላ
ኢየሱስ ወደ ላይ ተመልክቶ "አባት ሆይ! ስለ
ሰማኸኝ አመሰግናለሁ ፤ 42 ሁልጊዜም እንደም
ትሰማኝ ዐውቃለሁ ፤ ነገር ግን ይህን ያልሁት
እዚህ የቆሙት ሰዎች አንተ እንደላክኸኝ እንዲ
ያምኑ ብዬ ነው" አለ ። 43 ኢየሱስ ይህን ከተና
ገረ በኋላ "አልዓዛር! ና ውጣ!" ብሎ በታላቅ
ድምፅ ጮኸ ። 44 ሟቹ አልዓዛርም እጆቹና እግ
ሮቹ በመገነዣ እንደተገነዙ ከመቃብሩ ወጣ ፤
ፊቱም በጨርቅ እንደተጠመጠመ ነበር ፤ ኢየሱ
ስም "ፍቱትና ተዉት ፥ ይሂድ" አላቸው ።

### በክርስቶስ ላይ የተደረገ ሤራ
(ማቴ. 26፥1-5፤ ማር. 14፥1-2፤ ሉቃ. 22፥1-2)

45 ማርያምን ለማጽናናት መጥተው ከነበሩት
አይሁዳውያን ብዙዎቹ ፥ ያደረገውን አይተው

7* 11፥16 ዲዲሞስ ፦ "መንትያ" ማለት ነው ።

በኢየሱስ አመኑ ። 46 አንዳንዶቹ ግን ወደ ፈሪሳ
ውያን ሄደው ኢየሱስ ያደረገውን ነገሩአቸው ።
47 ስለዚህ የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን የሸንጎ
ውን አባሎች ሰብስበው እንዲህ አሉ ፤ "ይህ
ሰው ብዙ ተአምራት ስለሚያደርግ ምን ብናደ
ርግ ይሻላል? 48 እንዲሁ ብንተወው ሰው ሁሉ
በእርሱ ያምናል ፤ ሮማውያንም መጥተው ቤተ
መቅደሳችንንና ሕዝባችንን ሁሉ ይደመሰ
ሳሉ ።"
49 ነገር ግን ከእነርሱ አንዱ በዚያን ዓመት
ሊቀ ካህናት የነበረው ቀያፋ እንዲህ አለ ፤
"እናንተ ምንም አታውቁም ፤ 50 ሕዝብ ሁሉ
ከሚጠፋ አንድ ሰው ስለ ሕዝብ ቢሞት ለእና
ንተ የሚሻል መሆኑን ከቶ አልተገነዘባችሁ
ምን?" 51 እርሱም ይህን የተናገረው ከራሱ
አመንጭቶ አልነበረም ፤ ነገር ግን በዚያን
ዓመት እርሱ ሊቀ ካህናት ስለነበረ ኢየሱስ ስለ
ሕዝቡ መሞት እንደሚገባው ሲያመለክት ይህን
ትንቢት ተናገረ ። 52 የሚሞተውም ስለ ሕዝቡ
ብቻ ሳይሆን የተበተኑትንም የእግዚአብሔር
ልጆች በአንድነት ለመሰብሰብ ነው ።
53 ስለዚህ ከዚያ ቀን ጀምሮ ኢየሱስን ለመግ
ደል ተማከሩ ። 54 ከዚያን ወዲያ ኢየሱስ በአይ
ሁዳውያን መካከል በግልጥ አልተመላለሰም ፤
ነገር ግን ከዚያ ወጥቶ በበረሓ አጠገብ ወዳለ
ችው ኤፍሬም ወደምትባለው ከተማ ሄደ ፤
እዚያ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ቆየ ።
55 የአይሁዳውያን የፋሲካ በዓል ቀርቦ
ነበር ፤ ብዙዎቹም የፋሲካ በዓል ከመድረሱ
በፊት ራሳቸውን ለማንጻት ከየአውራጃው ወደ
ኢየሩሳሌም ሄዱ ፤ 56 እነርሱም በቤተ መቅደስ
ቆመው የኢየሱስን መምጣት ይጠባበቁ ስለነበር
"ምን ታስባላችሁ? ወደ በዓሉ የሚመጣ አይ
መስላችሁምን?" እያሉ እርስ በእርሳቸው ይጠ
ያየቁ ነበር ። 57 ደግሞም የካህናት አለቆችና
ፈሪሳውያን ኢየሱስን መያዝ እንዲችሉ ፤ ያለበ
ትን ቦታ የሚያውቅ ሰው ቢኖር እንዲጠቁማ
ቸው ሰውን ሁሉ አዝዘው ነበር ።

## ምዕራፍ 12

### ኢየሱስን ሽቶ የቀባች ሴት
(ማቴ. 26፥6-13፤ ማር. 14፥3-9)

1 የአይሁድ የፋሲካ በዓል ሊከበር ስድስት
ቀን ሲቀረው ፤ ኢየሱስ ወደ ቢታንያ ሄደ ፤
ቢታንያ ኢየሱስ ከሞት ያስነሣው አልዓዛር የሚ
ኖርባት መንደር ነች ። 2 እዚያ ራት አዘጋጁ
ለት ፤ ማርታ ታገለግል ነበር ፤ አልዓዛርም ከኢየ
ሱስ ጋር በማእድ ቀርበው ከነበሩት አንዱ
ነበር ። 3 በዚያን ጊዜ ማርያም ዋጋው እጅግ የከ
በረ ከንጹሕ ናርዶስ የተሠራ ግማሽ ሊትር የሚ
ሆን አንድ ብልቃጥ ሽቶ ወስዳ የኢየሱስን እግ
ሮች ቀባች ፤ በጠጕርዋም አበሰቻቸው ፤ ቤቱም
በሽቶው መዓዛ ተሞላ ። 4 ከደቀ መዛሙርቱ
አንዱ ፤ ኢየሱስን አሳልፎ የሚሰጠው አስቆሮታ
ዊው ይሁዳ ፤ 5 "ይህ ሽቶ በሦስት መቶ ብር
ተሽጦ ገንዘቡ ለድኾች ለምን አልተሰጠም?"
አለ ። 6 እርሱ ይህን የተናገረው ለድኾች አዝኖ
ሳይሆን ፤ ሌባ ስለነበረ ነው ፤ የገንዘብ ከረጢት
የሚይዝ እርሱ በመሆኑ በከረጢቱ የሚከተተ
ውን ገንዘብ መውሰድ ለምዶ ነበር ።
7 ኢየሱስም እንዲህ አለ ፤ "ለምቀበርበት
ቀን ያደረገችው ዝግጅት ስለሆነ ተዉአት ።
8 ድኾች ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ናቸው ። እኔ
ግን ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር አልሆንም ።"
9 በዚያን ጊዜ ብዙ አይሁዳውያን ኢየሱስ
በቢታንያ መሆኑን አውቀው መጡ ፤ የመጡ
ትም ስለ ኢየሱስ ብቻ ሳይሆን ኢየሱስ ከሞት
ያስነሣውን አልዓዛርንም ለማየት ነበር ። 10 የካህ
ናት አለቆች አልዓዛርንም ለመግደል ተማከሩ ።
11 ምክንያቱም በእርሱ የተነሣ ብዙ አይሁዳው
ያን ፤ መሪዎቻቸውን እየተዉ በኢየሱስ ያምኑ
ስለነበረ ነው ።

### ኢየሱስ በክብር ወደ ኢየሩሳሌም ገባ
(ማቴ. 21፥1-11፤ ማር. 11፥1-11፤
ሉቃ. 19፥28-40)

12 በማግሥቱ ለፋሲካ በዓል የመጡ ብዙ
ሰዎች ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም የሚመጣ መሆ
ኑን ሰሙ ። 13 ስለዚህ የዘንባባ ቅርንጫፍ ይዘው
ሊቀበሉት ወጡ ፤ "ሆሳዕና! በጌታ ስም የሚ
መጣ የእስራኤል ንጉሥ የተባረከ ነው!" እያሉ
ጮኹ ።
14 ኢየሱስ የአህያ ውርንጫላ አገኘና በእርሱ
ላይ ተቀመጠ ፤ ይህም የሆነው ፤
15 "አንቺ የጽዮን ከተማ ኢየሩሳሌም
አትፍሪ!
እነሆ ንጉሥሽ በአህያ ውርንጫላ ላይ
ተቀምጦ ይመጣል"
ተብሎ የተጻፈው ትንቢት እንዲፈጸም ነው ።
16 ደቀ መዛሙርቱ ይህ ነገር በመጀመሪያ
አልገባቸውም ነበር ፤ ግን ኢየሱስ በክብር ወደ
ሰማይ በወጣ ጊዜ ይህ ነገር ስለእርሱ እንደተጻ
ፈና ለእርሱም እንደተደረገለት አስታወሱ ።
17 ኢየሱስ አልዓዛርን ከመቃብር በጠራውና
ከሞት ባስነሣው ጊዜ አብረውት የነበሩ ሁሉ
ስለ ኢየሱስ ይመሰክሩ ነበር ። 18 ብዙ ሰዎች
ሊቀበሉት የወጡትም ይህን ተአምር እንዳደረገ
ሰምተው ስለነበር ነው ። 19 በዚህ ጊዜ ፈሪሳው
ያን "እነሆ ሕዝብ ሁሉ ተከትሎታል! እኛ
ምንም ማድረግ እንደማንችል ታያላችሁን?"
ተባባሉ ።

12፥3 ፦ ሉቃ. 7፥37-38 ። 12፥8 ፦ ዘዳ. 15፥11 ። 12፥13 ፦ መዝ. 118፥25-26 ። 12፥15 ፦ ዘካ. 9፥9 ።



20 በበዓሉ ጊዜ ሊሰግዱ ወደ ኢየሩሳሌም ከሄ
ዱት ሰዎች መካከል አንዳንድ ግሪካውያን ይገኙ
ነበር ። 21 እነርሱም ከገሊላ የቤተ ሳይዳ ሰው
ወደ ሆነው ወደ ፊልጶስ ቀርበው "ጌታዬ! ኢየ
ሱስን ማየት እንፈልጋለን" አሉት ።
22 ፊልጶስም ሄዶ ለእንድርያስ ነገረው ፤ እን
ድርያስና ፊልጶስ አብረው ሄደው ለኢየሱስ ነገ
ሩት ። 23 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፤
"እነሆ የሰው ልጅ የሚከበርበት ሰዓት ደርሶ
አል ፤ 24 እውነት ፤ እውነት እላችኋለሁ ፤ የስ
ንዴ ቅንጣት በመሬት ወድቃ ካልሞተች ብቻ
ዋን ትቀራለች ፤ ከሞተች ግን ብዙ ታፈራለች ።
25 ሕይወቱን የሚወድ ያጠፋታል ፤ በዚህ ዓለም
ሕይወቱን የሚጠላ ግን ለዘላለም ሕይወት ይጠ
ብቃታል ። 26 እኔን ማገልገል የሚፈልግ ይከተ
ለኝ ፤ እኔ ባለሁበት አገልጋዬ በዚያ ይሆናል ፤
የሚያገለግለኝንም አብ ያከብረዋል ።"

### ኢየሱስ ስለሚደርስበት መከራና ሞት ተናገረ

27 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፤ "እነሆ
ነፍሴ ተጨንቃለች ፤ 'አባት ሆይ! ከዚህች
ሰዓት አድነኝ ልበልን?' ይህን እንዳልል ግን
እኔ የመጣሁት ለዚህች የመከራ ሰዓት ነው ።
28 አባት ሆይ! ስምህን አክብረው ።"
ከዚህ በኋላ "ስሜን አክብሬዋለሁ ፤ ደግ
ሞም አከብረዋለሁ" የሚል ድምፅ ከሰማይ
መጣ ።
29 በዚያ የቆሙ ሰዎች ይህን በሰሙ ጊዜ ፤
"ነጐድጓድ ነው!" አሉ ። ሌሎች "መልአክ
ነው የተናገረው!" አሉ ።
30 ኢየሱስ ግን እንዲህ ሲል መለሰ ፤ "ይህ
ድምፅ የመጣው ስለ እናንተ ነው እንጂ ስለ እኔ
አይደለም ፤ 31 ይህ ዓለም የሚፈረድበት ጊዜ
አሁን ነው ፤ የዚህ ዓለም ገዥ ሰይጣን ወደ
ውጭ የሚጣለው አሁን ነው ፤ 32 እኔ ወደ ላይ
ከፍ ብዬ በተሰቀልሁ ጊዜ ሰውን ሁሉ ወደ እኔ
እስባለሁ ።" 33 ኢየሱስ ይህን የተናገረው በምን
ዐይነት ሞት እንደሚሞት ሲያመለክት ነበር ።
34 ሰዎቹም "በሕጋችን ተጽፎ የምናገኘው
'መሲሕ ለዘላለም ይኖራል' የሚል ነው ፤
ታዲያ አንተ 'የሰው ልጅ ወደ ላይ ከፍ ብሎ
መሰቀል አለበት' እንዴት ትላለህ? ይህ የሰው
ልጅ ማን ነው?" አሉት ።
35 ኢየሱስ እንዲህ አላቸው ፤ "አሁን ለጥ
ቂት ጊዜ ከእናንተ ጋር ብርሃን አለ ፤ ጨለማ
እንዳይደርስባችሁ ብርሃን ሳለላችሁ ተመላለሱ ፤
በጨለማ የሚመላለስ ወዴት እንደሚሄድ አያ
ውቅም ። 36 የብርሃን ልጆች እንድትሆኑ ብርሃን
ሳለላችሁ በብርሃን እመኑ ።" ኢየሱስ ይህን ከተ
ናገረ በኋላ ሄደና ተሰወረባቸው ።

### የአይሁዳውያን አለማመን

37 ኢየሱስም ምንም እንኳ ይህን ያህል ተአ
ምር በፊታቸው ቢያደርግም አይሁዳውያን በእ
ርሱ አላመኑም ። 38 ይህም የሆነው ነቢዩ ኢሳይ
ያስ ፤
"ጌታ ሆይ! ምስክርነታችንን ማን
አመነ?
የእግዚአብሔርስ ክንድ ለማን
ተገለጠ?"
ሲል የተናገረው ቃል እንዲፈጸም ነው ። 39 ስለ
ዚህ ማመን አልቻሉም ፤ ምክንያቱም ነቢዩ
ኢሳይያስ እንዲህ ሲል ደግሞ ስለጻፈ ነው ፤
40 "በዐይናቸው አይተውና
በልባቸው አስተውለው
እንዳይመለሱና እንዳይፈውሳቸው ፤
እግዚአብሔር ዐይናቸውን
አሳውሮአቸዋል ፤
ልባቸውንም አደንድኖአል ።"
41 ኢሳይያስ ይህን ያለው የመሲሕን ክብር
ስላየ ነው ፤ ስለዚህ ይህን ስለ ኢየሱስ ተናገረ ።
42 ሆኖም ከአይሁዳውያን አለቆች እንኳ ብዙ
ዎቹ በኢየሱስ አምነዋል ፤ ነገር ግን ከምኵራብ
እንዳያስወጡአቸው ፈሪሳውያንን በመፍራት በግ
ልጥ አልመሰከሩለትም ። 43 ይህንንም ያደረጉት
ከእግዚአብሔር ከሚገኘው ክብር ይልቅ ከሰው
የሚገኘውን ክብር ስለወደዱ ነው ።
44 ኢየሱስም ድምፁን ከፍ አድርጎ እንዲህ
አለ ፤ "በእኔ የሚያምን በእኔ ብቻ ሳይሆን በላከ
ኝም ያምናል ፤ 45 እኔን የሚያይ የላከኝን
ያያል ፤ 46 በእኔ የሚያምን ሁሉ በጨለማ እንዳ
ይኖር ፤ እኔ ብርሃን ሆኜ ወደ ዓለም መጥቻ
ለሁ ። 47 ቃሌን ሰምቶ በሥራ ላይ የማያውለ
ውን የምፈርድበት እኔ አይደለሁም ፤ ምክንያ
ቱም እኔ የመጣሁት ዓለምን ለማዳን ነው እንጂ
በዓለም ላይ ለመፍረድ አይደለም ። 48 እኔን የማ
ይፈልግና ቃሌንም የማይቀበለውን ሰው የሚፈ
ርድበት አለ ፤ እኔ የተናገርሁት ቃል በመጨ
ረሻ ቀን ይፈርድበታል ። 49 ምክንያቱም እኔ
በራሴ ሥልጣን አልተናገርሁም ፤ እኔ የምለው
ንና የምናገረውን ትእዛዝ የሰጠኝ ፤ የላከኝ አብ
ነው ። 50 የእርሱም ትእዛዝ የዘላለም ሕይወት
እንደሆነ ዐውቃለሁ ። ስለዚህ እኔ የምናገረው
አብ የነገረኝን ነው ።"

## ምዕራፍ 13

### ኢየሱስ የደቀ መዛሙርቱን እግር አጠበ

1 እነሆ ጊዜው ከአይሁድ ፋሲካ በዓል በፊት
ነበር ፤ ኢየሱስ ይህን ዓለም ትቶ ወደ አብ የሚ
ሄድበት ሰዓት መድረሱን ዐወቀ ። በዚህ ዓለም

12፥25 ፦ ማቴ. 10፥39፤ 16፥25 ፤ ማር. 8፥35 ፤ ሉቃ. 9፥24 ፤ 17፥33 ። 12፥34 ፦ መዝ. 110፥4 ፤ ኢሳ. 9፥7 ፤ ሕዝ. 37፥25 ፤
ዳን. 7፥14 ። 12፥38 ፦ ኢሳ. 53፥1 ። 12፥40 ፦ ኢሳ. 6፥10 ።

ያሉትን የራሱን ወገኖች ሁልጊዜ ወድዶአቸው
ነበር፤ እስከ መጨረሻም ወደዳቸው ።
2 ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ራት ይበሉ
ነበር፤ የስምዖን ልጅ አስቆሮታዊው ይሁዳ ኢየ
ሱስን አሳልፎ እንዲሰጥ ዲያብሎስ በልቡ ክፉ
አሳብ አገባበት ። 3 አብ ሥልጣንን ሁሉ እንደሰ
ጠውና ከእግዚአብሔር ወጥቶ እንደመጣ፤ ወደ
እግዚአብሔርም እንደሚሄድ ኢየሱስ ያውቅ
ነበር ። 4 ስለዚህ ከማእድ ተነሣና ልብሱን አስቀ
መጠ፤ ፎጣም አንሥቶ በወገቡ ታጠቀ ።
5 ከዚህ በኋላ በመታጠቢያ ሳሕን ውሃ አድርጎ
የደቀ መዛሙርቱን እግር ማጠብ ጀመረ፤ በታ
ጠቀውም ፎጣ እግራቸውን አበሰ ። 6 ኢየሱስ
ወደ ስምዖን ጴጥሮስ በመጣ ጊዜ፣ ስምዖን ጴጥ
ሮስ "ጌታ ሆይ! አንተ የእኔን እግር ታጥባለ
ህን?" አለው ።
7 ኢየሱስም "እኔ የማደርገውን አንተ አሁን
አታውቅም፤ በኋላ ግን ታውቃለህ" አለው ።
8 ጴጥሮስም "አንተ የእኔን እግር ከቶ አታጥ
ብም" አለው ።
ኢየሱስም "እኔ እግርህን ካላጠብሁህ ከእኔ
ጋር አንድነት አይኖርህም" አለው ።
9 ስምዖን ጴጥሮስም "ጌታ ሆይ! እንዲህስ
ከሆነ እግሬን ብቻ ሳይሆን እጄንም፣ ራሴንም
እጠበኝ!" አለው ።
10 ኢየሱስም "ሰውነቱን የታጠበ ሁለመናው
ንጹሕ በመሆኑ፤ እግሩን ከመታጠብ በቀር ሌላ
አያስፈልገውም፤ እናንተም ንጹሖች ናችሁ፤
ነገር ግን ሁላችሁም ንጹሖች አይደላችሁም"
አለው ። 11 ኢየሱስ "ሁላችሁም ንጹሖች አይደ
ላችሁም" ያለው አሳልፎ የሚሰጠው ማን እንደ
ሆነ ያውቅ ስለነበር ነው ።
12 እግራቸውን ካጠበ በኋላ ልብሱን ለበሰና
ወደ ቦታው ተመልሶ ተቀመጠ፤ እንዲህም አላ
ቸው፣ "ምን እንዳደረግሁላችሁ አስተዋላች
ሁን? 13 እናንተ 'መምህርና ጌታ' ትሉኛላ
ችሁ፤ እኔ መምህርና ጌታ ስለሆንሁ ያላችሁት
ትክክል ነው ። 14 እንግዲህ እኔ ጌታችሁና መም
ህራችሁ ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ፣ እናን
ተም እርስ በርሳችሁ እግራችሁን መተጣጠብ
ይገባችኋል ። 15 እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁት፣
እናንተም እንድታደርጉ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁ ።
16 እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ አገልጋይ
ከጌታው አይበልጥም፤ መልእክተኛም ከላከው
አይበልጥም ። 17 ይህን ነገር ብታውቁና በሥራ
ላይ ብታውሉት፣ የተመሰገናችሁ ናችሁ ።
18 ይህን የምናገረው ስለ ሁላችሁም አይደለም፤
እኔ የመረጥኋችሁን ዐውቃለሁ፤ ነገር ግን 'እን
ጀራዬን የበላ በእኔ ላይ በጠላትነት ተነሣብኝ'
የሚለው የመጽሐፍ ቃል መፈጸም አለበት ።
19 ይህ ከመሆኑ በፊት አሁን አስቀድሜ የምነግ
ራችሁ፤ ከተፈጸመ በኋላ በእኔ ማንነት እንድታ
ምኑ ነው ። 20 እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፤
እኔ የምልከውን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤ እኔ
ንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል ።"

### ኢየሱስ አሳልፎ የሚሰጠው ማን እንደሆነ አስቀድሞ ተናገረ
(ማቴ. 26፥20-25፤ ማር. 14፥17-21፤
ሉቃ. 22፥21-23)

21 ኢየሱስ ይህን ካለ በኋላ በመንፈሱ ተጨነ
ቀና "እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ ከእናንተ
አንዱ አሳልፎ ይሰጠኛል" ሲል ገልጦ ተናገረ ።
22 ደቀ መዛሙርቱ ይህን ስለማን እንደተና
ገረ ባለማወቃቸው፣ እርስ በእርሳቸው ተያዩ ።
23 ኢየሱስ ይወደው የነበረው፣ ከደቀ መዛሙ
ርቱ አንዱ በኢየሱስ ጐን ተቀምጦ ነበር ።
24 ስምዖን ጴጥሮስ እርሱን ጠቀሰና "ስለ ማን
እንደ ተናገረ እስቲ ጠይቅ" አለው ።
25 ስለዚህ እርሱ አንገቱን ወደ ኢየሱስ ጆሮ
አስጠጋና "ጌታ ሆይ! ማን ነው?" ሲል ጠየ
ቀው ።
26 ኢየሱስም "እርሱ ይህን እንጀራ በወጥ
አጥቅሼ የማጐርሰው ነው" አለ ። ይህንንም
ብሎ እንጀራ በወጥ አጠቀሰና የአስቆሮታዊው
ስምዖን ልጅ ለሆነው ለይሁዳ አጐረሰው ።
27 ይሁዳ ጉርሻውን ከተቀበለ በኋላ ወዲያውኑ
ሰይጣን ገባበት፤ ኢየሱስም ይሁዳን "ለማድረግ
ያሰብኸውን ቶሎ ብለህ አድርግ" አለው ።
28 ኢየሱስ ስለምን ይህን እንዳለ በማእድ ከተቀ
መጡት ማንም የገባው የለም ። 29 ይሁዳ ገንዘብ
ያዥ ስለነበረ ከደቀ መዛሙርቱ አንዳንዶቹ ኢየ
ሱስ "ለበዓሉ የሚያስፈልገንን ግዛ ወይም ለድ
ኾች ምጽዋት ስጥ" ያለው መስሎአቸው
ነበር ።
30 ይሁዳም ጉርሻውን እንደተቀበለ፣ ወዲያ
ውኑ ወጥቶ ሄደ፤ ጊዜውም ሌሊት ነበረ ።

### አዲሱ ትእዛዝ

31 ይሁዳ ወጥቶ ከሄደ በኋላ ኢየሱስ እንዲህ
አለ፣ "አሁን የሰው ልጅ ከብሮአል፤ በእርሱም
አማካይነት እግዚአብሔር ከብሮአል፤ 32 እግዚ
አብሔር በእርሱ አማካይነት ከከበረ፣ እግዚአብ
ሔርም እርሱን ያከብረዋል፤ ሳይዘገይም ያከብረ
ዋል ። 33 ልጆች ሆይ! ከእናንተ ጋር ብዙ ጊዜ
አልቆይም፤ እናንተም ትፈልጉኛላችሁ፤ ለአይ
ሁዳውያን ባለሥልጣኖች 'እኔ ወደምሄድበት
እናንተ ልትመጡ አትችሉም' እንዳልኋቸው፣
አሁንም ለእናንተ እንዲሁ እላችኋለሁ ።

13፥12-15 ፦ ሉቃ. 22፥27 ። 13፥16 ፦ ማቴ. 10፥24፤ ሉቃ. 6፥40፤ ዮሐ. 15፥20 ። 13፥18 ፦ መዝ. 41፥9 ።
13፥20 ፦ ማቴ. 10፥40፤ ማር. 9፥37፤ ሉቃ. 9፥48፤ 10፥16 ። 13፥33 ፦ ዮሐ. 7፥34 ።



34 እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ አዲስ ትእዛዝ
እሰጣችኋለሁ፤ እኔ እንደ ወደድኋችሁ እናን
ተም እርስ በእርሳችሁ ተዋደዱ ። 35 እርስ በእር
ሳችሁ ከተዋደዳችሁ የእኔ ደቀ መዛሙርት እን
ደሆናችሁ ሰው ሁሉ ያውቃል ።"

### ጴጥሮስ እንደሚክደው ኢየሱስ አስቀድሞ ተናገረ
(ማቴ. 26፥31-35፤ ማር. 14፥27-31፤
ሉቃ. 22፥31-34)

36 ከዚህ በኋላ ስምዖን ጴጥሮስ ኢየሱስን
"ጌታ ሆይ! ወዴት ነው የምትሄደው?" ሲል
ጠየቀው ።
ኢየሱስም "እኔ ወደምሄድበት አሁን ልትከ
ተለኝ አትችልም፤ በኋላ ግን ትከተለኛለህ"
ሲል መለሰለት ።
37 ጴጥሮስም "ጌታ ሆይ! ስለምን አሁን
ልከተልህ አልችልም? እኔ ሕይወቴን እንኳ ስለ
አንተ አሳልፌ እሰጣለሁ" አለው ።
38 ኢየሱስም "አንተ ሕይወትህን ስለ እኔ
አሳልፈህ ትሰጣለህን? እውነት፣ እውነት እልሃ
ለሁ፣ ዛሬ ዶሮ ከመጮኹ በፊት ሦስት ጊዜ
ትክደኛለህ" ሲል መለሰ ።

## ምዕራፍ 14

### ወደ አብ የሚወስደው መንገድ ኢየሱስ ነው

1 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ "ልባችሁ
አይጨነቅ፤ በእግዚአብሔር እመኑ፤ በእኔም
እመኑ፤ 2 በአባቴ ዘንድ ብዙ መኖሪያ አለ፤ አለ
በለዚያ ግን 'የምትኖሩበትን ስፍራ ላዘጋጅላ
ችሁ እሄዳለሁ' ባላልኋችሁም ነበር ። 3 ሄጄ
ስፍራ ካዘጋጀሁላችሁ በኋላ፣ እኔ ባለሁበት እን
ድትኖሩ እንደገና መጥቼ እወስዳችኋለሁ ።
4 እኔ የምሄድበትንም መንገድ ታውቃላችሁ ።"
5 ቶማስ "ጌታ ሆይ! ወዴት እንደምትሄድ
አናውቅም፤ ታዲያ መንገዱን እንዴት ማወቅ
እንችላለን?" አለው ።
6 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት፣ "መንገ
ድና እውነት ሕይወትም እኔ ነኝ፤ በእኔ በኩል
ካልሆነ በቀር ማንም ወደ አብ የሚመጣ
የለም ። 7 እኔን ዐውቃችሁኝ ቢሆን ኖሮ፣ አባቴ
ንም ባወቃችሁት ነበር፤ ከእንግዲህ ወዲህ ግን
ታውቁታላችሁ፤ አይታችሁታልም ።"
8 ፊልጶስም "ጌታ ሆይ! አብን አሳየንና ይበ
ቃናል" አለው ።
9 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት፣ "ፊል
ጶስ ሆይ! ይህን ያህል ጊዜ ከእናንተ ጋር ስኖር
አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን አይቶአል፤
ታዲያ አንተ 'አብን አሳየን' እንዴት ትላለህ?
10 እኔ በአብ እንዳለሁ፣ አብም በእኔ እንዳለ
አታምንምን? ለእናንተ የምናገረውን ቃል የም
ናገረው በራሴ ሥልጣን አይደለም፤ ነገር ግን
ሥራውን ሁሉ የሚሠራው በእኔ የሚኖረው
አብ ነው ። 11 እኔ በአብ እንዳለሁ፣ አብም
በእኔ እንዳለ እመኑ፤ አለበለዚያ በሥራዎቼ
ምክንያት እመኑኝ ። 12 እውነት እላችኋለሁ
በእኔ የሚያምን እኔ የምሠራውን ሥራ ይሠ
ራል፤ እንዲያውም ከዚህ የበለጠ ይሠራል፤
ምክንያቱም እኔ ወደ አብ እሄዳለሁ ። 13 አብ
በወልድ ምክንያት እንዲከበር በስሜ የምትለም
ኑትን ሁሉ አደርግላችኋለሁ ። 14 ማንኛውንም
ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ ።"

### ኢየሱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ የሰጠው ተስፋ

15 "የምትወዱኝ ከሆነ ትእዛዜን ትጠብቃላ
ችሁ፤ 16 እኔ አብን እለምነዋለሁ፤ እርሱም ለዘ
ላለም ከእናንተ ጋር የሚኖር ሌላ አጽናኝ ይሰ
ጣችኋል ። 17 ይህ አጽናኝ፣ ስለማያየውና ስለማ
ያውቀው ዓለም ሊቀበለው የማይችለው የእው
ነት መንፈስ ነው፤ እናንተ ግን ታውቁታላ
ችሁ፤ ምክንያቱም እርሱ ከእናንተ ጋር ስለሚ
ኖርና በውስጣችሁም ስለሚሆን ነው ።
18 "እናትና አባት እንደሌላቸው ልጆች
ብቻችሁን አልተዋችሁም፤ ተመልሼ ወደ እና
ንተ እመጣለሁ ። 19 ከጥቂት ጊዜ በኋላ ዓለም
አያየኝም፤ እናንተ ግን ታዩኛላችሁ፤ እኔ
ሕያው ስለሆንሁ እናንተም በሕይወት ትኖራላ
ችሁ፤ 20 እኔ በአብ እንዳለሁ፣ እናንተም በእኔ
እንዳላችሁ፣ እኔም በእናንተ እንዳለሁ በዚያን
ቀን ታውቃላችሁ ።
21 "ትእዛዜን የሚቀበልና በሥራ ላይ የሚያ
ውለው ይወድደኛል፤ እኔን የሚወድደኝን
አባቴ ይወድደዋል፤ እኔም እወድደዋለሁ፤ ራሴ
ንም እገልጥለታለሁ ።"
22 አስቆሮታዊው ሳይሆን ሌላው ይሁዳ
"ጌታ ሆይ! ራስህን ለዓለም ሳይሆን ለእኛ የም
ትገልጠው እንዴት ነው?" አለው ።
23 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት፣ "የሚ
ወድደኝ ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወድደ
ዋል፤ እኛ ወደ እርሱ መጥተን ከእርሱ ጋር
አብረን እንኖራለን ። 24 የማይወድደኝ ቃሌን
አይጠብቅም፤ ይህ የምትሰሙት ቃል የላከኝ
የአብ ነው እንጂ የእኔ አይደለም ።
25 "አሁን ከእናንተም ጋር እያለሁ ይህን
ነገር ነግሬአችኋለሁ፤ 26 አብ በእኔ ስም የሚል
ከው አጽናኙ መንፈስ ቅዱስ ግን ሁሉን ነገር
ያስተምራችኋል፤ እኔ የነገርሁአችሁንም ሁሉ
እንድታስታውሱ ያደርጋችኋል ።
27 "ሰላምን እተውላችኋለሁ፤ ሰላሜንም እሰ
ጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ሰላም ዓለም እንደ
ሚሰጠው ዐይነት አይደለም፤ ልባችሁ አይጨ
ነቅ፣ ደግሞም አይፍራ ። 28 'እኔ እሄዳለሁ፤

13፥34 ፦ ዮሐ. 15፥12፣17፤ 1ዮሐ. 3፥23፤ 2ዮሐ. 5 ።

ቀመልሼም ወደ እናንተ እመጣለሁ’ እንዳልሁ
ሰምታችኋል ፤ ብትወድዱኝስ ኖሮ ወደ አብ
በመሄዴ ደስ ባላችሁ ነበር ፤ ምክንያቱም አብ
ከእኔ ይበልጣል ። 29ይህ በሚሆንበት ጊዜ እን
ድታምኑ ፤ ከመሆኑ በፊት አስቀድሜ ነግሬ
እችኋለሁ ። 30የዚህ ዓለም ገዥ ሰይጣን መም
ጣቱ ስለሆነ ከእንግዲህ ወዲህ ከእናንተ ጋር
ብዙ አልነጋገርም ። እርሱ በእኔ ላይ ምንም
ማድረግ አይችልም ፤ 31ነገር ግን እኔ አብን እን
ደምወድድ ዓለም ያውቅ ዘንድ አብ ያዘዘኝን
ሁሉ እፈጽማለሁ ፤
“ተነሡ ከዚህ እንሂድ ።”

## ምዕራፍ 15

### ኢየሱስ እውነተኛ የወይን ግንድ ነው

1ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፦ “እውነ
ተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ ፤ አትክልተኛውም
አባቴ ነው ፤ 2በእኔ ላይ ያለውን የማያፈራ ቅር
ንጫፍ ሁሉ አባቴ ቈርጦ ይጥለዋል ፤ የሚያፈ
ራውን ቅርንጫፍ አብዝቶ እንዲያፈራ ገርዞ
ያጠራዋል ። 3እናንተም በነገርሁአችሁ ቃል
ምክንያት አሁን የጠራችሁ ንጹሖች ናችሁ ።
4በእኔ ኑሩ ፤ እኔም በእናንተ እኖራለሁ ፤ ቅርን
ጫፍ በወይኑ ግንድ ላይ ካልኖረ በቀር በራሱ
ብቻ ማፍራት እንደማይቻለው ፥ እናንተም
በእኔ ካልኖራችሁ ማፍራት አትችሉም ።
5“እኔ የወይን ግንድ ነኝ ፤ እናንተም ቅርን
ጫፎች ናችሁ ፤ ብዙ ፍሬ የሚያፈራው በእኔ
የሚኖርና እኔም በእርሱ የምኖርበት ነው ፤ ምክ
ንያቱም ያለ እኔ ምንም ማድረግ አትችሉም ።
6በእኔ የማይኖር እንደ ቅርንጫፍ ወደ ውጭ
ተጥሎ ይደርቃል ፤ ተሰብስቦም ወደ እሳት ይጣ
ልና ይቃጠላል ። 7በእኔ ብትኖሩ ፤ ቃሌም በእ
ናንተ ቢኖር ፥ የፈለጋችሁትን ስትጠይቁ ታገኛ
ላችሁ ። 8ብዙ ፍሬ ስታፈሩ አባቴ ይከብራል ፤
በዚህም ዐይነት የእኔ ደቀ መዛሙርት መሆናች
ሁን ታስረዳላችሁ ። 9አብ እኔን እንደወደደኝ ፥
እኔም እናንተን ወደድኋችሁ ፤ ስለዚህ በፍቅሬ
ኑሩ ። 10እኔ የአባቴን ትእዛዝ እንደፈጸምሁና
በፍቅሩ እንደምኖር ፥ እናንተም የእኔን ትእዛዝ
ብትፈጽሙ በፍቅሬ ትኖራላችሁ ። 11ይህን የነ
ገርሁአችሁ ደስታዬ በእናንተ እንዲሆንና የእና
ንተም ደስታ ፍጹም እንዲሆን ነው ። 12የእኔ
ትእዛዝ እኔ እንደወደድሁአችሁ እናንተም
እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ ነው ። 13ሰው
ሕይወቱን ስለወዳጆቹ አሳልፎ ከመስጠት የበ
ለጠ ፍቅር የለውም ። 14እናንተም እኔ የማዝዛ
ችሁን ብትፈጽሙ ወዳጆቼ ናችሁ ። 15አገል
ጋይ ጌታው የሚያደርገውን ስለማያውቅ ፥ ከእን
ግዲህ ወዲህ አገልጋዮች አልላችሁም ፤ ነገር
ግን ከአባቴ የሰማሁትን ሁሉ ስለ ገለጥሁላችሁ
ወዳጆቼ ብያችኋለሁ ፤ 16እኔ መረጥሁአችሁ
እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም ፤ ሄዳችሁ
ብዙ ፍሬ እንድታፈሩ ፥ ፍሬአችሁም ነዋሪ እን
ዲሆን ሾምሁአችሁ ። ስለዚህ በስሜ የምትለም
ኑትን ሁሉ አብ ይሰጣችኋል ። 17እንግዲህ እኔ
የማዝዛችሁ እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ
ነው ።”

### ኢየሱስ ስለ ዓለም ጥላቻ ተናገረ

18ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፦ “ዓለም
ቢጠላችሁ ከእናንተ በፊት እኔን እንደጠላኝ
ዕወቁ ። 19የዓለም ብትሆኑ ፥ ዓለም የራሱ የሆነ
ውን በወደደ ነበር ፤ ነገር ግን የዓለም ስላልሆና
ችሁና እኔ ከዓለም ለይቼ ስለመረጥሁአችሁ ፥
ዓለም ይጠላችኋል ። 20አገልጋይ ከጌታው አይበ
ልጥም ብዬ የነገርሁአችሁን አስታውሱ ፤ እኔን
ካሳደዱኝ ፥ እናንተንም ያሳድዱአችኋል ፤
ቃሌን ከጠበቁ ፥ ቃላችሁንም ይጠብቃሉ ።
21የላከኝን ስለማያውቁ በእኔ ምክንያት ይህን
ሁሉ ያደርጉባችኋል ። 22እኔ መጥቼ ባልነግራ
ቸው ኖሮ ኃጢአት ባልሆነባቸውም ነበር ፤
አሁን ግን ለኃጢአታቸው ምክንያት የላቸ
ውም ። 23እኔን የሚጠላ አባቴንም ይጠላል ፤
24ሌላ ሰው ያላደረገውን ሥራ በመካከላቸው
ባላደርግ ኖሮ ኃጢአት ባልሆነባቸውም ነበር ፤
አሁን ግን ይህን ሁሉ ካዩ በኋላ እኔንም አባቴ
ንም ጠልተዋል ። 25ይህም የሆነው ‘ያለ ምክን
ያት ጠሉኝ’ ተብሎ በሕጋቸው የተጻፈው ቃል
እንዲፈጸም ነው ።
26“ነገር ግን ከአብ የሚወጣና እኔም ከአብ
ዘንድ የምልክላችሁ ፥ የእውነት መንፈስ የሆ
ነው አጽናኝ ሲመጣ ፥ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክ
ራል ። 27እናንተም ከመጀመሪያ አንሥቶ ከእኔ
ጋር ስለነበራችሁ ትመሰክራላችሁ ።”

## ምዕራፍ 16

1ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፦ “እነሆ
ይህን ሁሉ የነገርሁአችሁ ፥ እምነታችሁ እንዳ
ይናወጥ ብዬ ነው ። 2ከምኵራቦች አስወጥተው
ያባርሩአችኋል ፤ እንዲያውም እናንተን የሚገድ
ላችሁ ሁሉ ፥ እግዚአብሔርን የሚያገለግል
የሚመስልበት ጊዜ ይመጣል ። 3ይህንንም የሚ
ያደርጉት አብንም ሆነ እኔን ስላላወቁ ነው ።
4ይህንን ለእናንተ መናገሬ ግን ጊዜው ሲደርስ
ምን እንዳልሁአችሁ እንድታስታውሱ ነው ።”

### የመንፈስ ቅዱስ ሥራ

ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፦ “ይህን ሁሉ
ከአሁን በፊት ያልነገርሁአችሁ ከእናንተ ጋር

15፥12 ፦ ዮሐ. 13፥34 ፤ 15፥17 ፤ 1ዮሐ. 3፥23 ፤ 2ዮሐ. 5 ። 15፥20 ፦ ማቴ. 10፥24 ፤ ሉቃ. 6፥40 ፤ ዮሐ. 13፥16 ።
15፥25 ፦ መዝ. 35፥19 ፤ 69፥4 ።



ስለ ነበርሁ ነው ፤ 5አሁን ግን ወደ ላከኝ
መሄዴ ነው ፤ ሆኖም ከእናንተ ‘ወዴት ትሄዳ
ለህ?’ ብሎ የሚጠይቀኝ የለም ። 6ይሁን እንጂ
ይህን ሁሉ ስለ ነገርሁአችሁ ልባችሁ በሐዘን
ተሞልቶአል ። 7እኔ ግን እውነት ፥ እውነት
እላችኋለሁ ፥ የእኔ መሄድ ለእናንተ ይጠቅ
ማችኋል ፤ ምክንያቱም እኔ ካልሄድሁ አጽናኙ
ወደ እናንተ አይመጣም ፤ እኔ ከሄድሁ ግን ወደ
እናንተ እልከዋለሁ ። 8እርሱ በመጣ ጊዜ ስለ
ኃጢአት ፥ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድም ሰዎችን
ያስረዳል ። 9ስለ ኃጢአት የሚያስረዳው በእኔ
ስለማያምኑ ነው ፤ 10ስለ ጽድቅ የሚያስረዳው
ወደ አብ ስለመሄዴና ከእንግዲህ ወዲህ ስለማታ
ዩኝ ነው ፤ 11ስለ ፍርድ የሚያስረዳው የዚህ
ዓለም ገዥ (ሰይጣን) ስለ ተፈረደበት ነው ።
12“ገና የምነግራችሁ ብዙ ነገር አለኝ ፤ ነገር
ግን አሁን ይከብዳችኋል ፤ 13የእውነት መንፈስ
በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል ፤
ምክንያቱም እርሱ የሚናገረው የሰማውን እንጂ
የራሱን አይደለም ። እርሱ ወደፊት የሚሆኑትን
ነገሮች ይነግራችኋል ። 14የእኔ ከሆነው ወስዶ
ስለሚነግራችሁ ፥ እኔን ያከብረኛል ። 15የአብ
የሆነው ሁሉ የእኔ ነው ፤ ‘የእኔ ከሆነው ወስዶ
ይነግራችኋል’ ያልሁአችሁ ስለዚህ ነው ።”

### ሐዘናችሁ ወደ ደስታ ይለወጣል

16ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ “ከጥቂት
ጊዜ በኋላ አታዩኝም ፤ ደግሞም ከጥቂት ጊዜ
በኋላ ታዩኛላችሁ ።”
17ከደቀመዛሙርቱ አንዳንዶች “ይህ ፥ ‘ከጥ
ቂት ጊዜ በኋላ አታዩኝም ፥ ደግሞ ከጥቂት
ጊዜ በኋላ ታዩኛላችሁ ፥ ደግሞ ወደ አብ እሄዳ
ለሁ’ የሚለን ነገር ምንድን ነው?” ተባባሉ ።
18“እንግዲህ ይህ ‘ከጥቂት ጊዜ በኋላ’ የሚለው
ነገር ምንድን ነው? የሚናገረውን ነገር አናው
ቅም” አሉ ።
19ኢየሱስም ሊጠይቁት እንደፈለጉ ዐውቆ
እንዲህ አላቸው ፥ “እርስ በርሳችሁ የምትጠያ
የቁ ‘ከጥቂት ጊዜ በኋላ አታዩኝም ፤ ደግሞም
ከጥቂት ጊዜ በኋላ ታዩኛላችሁ’ ስላልሁአችሁ
ነውን? 20እውነት ፥ እውነት እላችኋለሁ ፥ እና
ንተ ታለቅሳላችሁ ፤ ዓለም ግን ደስ ይለዋል ፤
እናንተ ታዝናላችሁ ፤ ነገር ግን ሐዘናችሁ ወደ
ደስታ ይለወጣል ። 21ሴት በምትወልድበት ጊዜ
የምጥ ቀንዋ ስለደረሰ ታዝናለች ፤ ከወለደች
በኋላ ግን በዓለም ላይ ሕፃን ስለተወለደ ከመደ
ሰትዋ የተነሣ ጭንቀትዋን አታስታውሰውም ።
22እንዲሁም እናንተ አሁን ታዝናላችሁ ፤ እንደ
ገና አያችኋለሁ ፤ ልባችሁም ደስ ይለዋል ፤ ደስ
ታችሁንም የሚወስድባችሁ የለም ።
23“በዚያን ቀን ከእኔ ምንም አትለምኑም ፤
እውነት ፥ እውነት እላችኋለሁ አብን በስሜ
ብትለምኑት ሁሉን ነገር ይሰጣችኋል ። 24እስከ
አሁን በስሜ ምንም ነገር አልለመናችሁም ፤
ለምኑ ትቀበላላችሁ ፤ ደስታችሁም ፍጹም ይሆ
ናል ።
25“እስከ አሁን በምሳሌ ነገርኋችሁ ፤ ከእን
ግዲህ ወዲህ በምሳሌ የማልናገርበት ጊዜ ይመ
ጣል ፤ ነገር ግን ስለ አብ ሁሉን ነገር ገልጬ
እነግራችኋለሁ ። 26በዚያን ቀን በስሜ ትለምና
ላችሁ ፤ እኔም ‘አብን እለምንላችኋለሁ’ አልላ
ችሁም ። 27ምክንያቱም አብ ራሱ ስለሚወድዳ
ችሁ ነው ፤ አብም የሚወድዳችሁ እኔን ስለወደ
ዳችሁኝና ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደመጣሁ
ስላመናችሁ ነው ። 28ከአብ ዘንድ ወጥቼ ወደ
ዓለም መጥቻለሁ ፤ እንደገናም ይህን ዓለም ትቼ
ወደ አብ እሄዳለሁ ።”
29ደቀ መዛሙርቱም እንዲህ አሉ ፥ “እነሆ
አሁን በምሳሌ ሳይሆን በግልጥ ተናገርህ ፤
30አንተ ሁሉን እንደምታውቅና ማንም ጥያቄ
ሊያቀርብልህ እንደማያስፈልግህ አሁን ዐወ
ቅን ፤ ስለዚህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደወጣህ
እናምናለን ።”
31ኢየሱስ እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፥ “አሁ
ንስ አምናችኋል! 32ይሁን እንጂ እያንዳንዳችሁ
በየበኩላችሁ የምትበታተኑበትና እኔን ብቻዬን
የምትተዉበት ሰዓት ይመጣል ፤ ሰዓቱም አሁን
ደርሶአል ፤ ነገር ግን አብ ከእኔ ጋር ስለሆነ ብቻ
ዬን አይደለሁም ። 33ይህን ለእናንተ መናገሬ
በእኔ ሆናችሁ ሰላም እንዲኖራችሁ ብዬ ነው ፤
በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ ፤ ነገር ግን አይ
ዞአችሁ ፥ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ ።”

## ምዕራፍ 17

### የኢየሱስ ጸሎት

1ኢየሱስ ይህን ከተናገረ በኋላ ወደ ሰማይ
ቀና ብሎ እንዲህ ሲል ጸለየ ፥ “አባት ሆይ!
እነሆ ሰዓቱ ደርሶአል ፥ ልጅህ እንዲያከብርህ ፥
ልጅህን አክብረው ፤ 2የምታከብረውም ለሰጠ
ኸው ሁሉ የዘላለም ሕይወትን እንዲሰጥ ፥ በሰ
ዎች ሁሉ ላይ ሥልጣን ስለሰጠኸው ነው ።
3የዘላለም ሕይወትም ፥ ብቻህን እውነተኛ አም
ላክ የሆንከውን አንተንና የላክኸውን ኢየሱስ
ክርስቶስን ማወቅ ነው ። 4እኔ የሰጠኸኝን ሥራ
ፈጽሜ በምድር ላይ አከበርሁህ ። 5አባት ሆይ
ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ከአንተ ጋር በነበረኝ
ክብር አሁንም በአንተ ዘንድ አክብረኝ ።
6“ከዓለም ውስጥ መርጠህ ለሰጠኸኝ ሰዎች
የአንተን ማንነት ገለጥሁላቸው ፤ እነርሱ የአንተ
ነበሩ ፤ አንተ እነርሱን ለእኔ ሰጠኸኝ ፤ እነር
ሱም ቃልህን ጠብቀዋል ፤ 7የሰጠኸኝ ሁሉ ከአ
ንተ እንደሆነ እነርሱ አሁን ዐውቀዋል ። 8የሰ
ጠኸኝን ቃል ሰጥቼአቸዋለሁ ፤ እነርሱም ተቀ
ብለውታል ፤ ከአንተ ዘንድ መውጣቴንም በእው
ነት ዐውቀዋል ፤ አንተ እንደላክኸኝም አምነ
ዋል ።

9 "እኔ የምጸልየው ለእነርሱ ነው ፤ እነዚህ
የሰጠኸኝ የአንተ ስለሆኑ ለእነርሱ እጸልያለሁ ፤
ለዓለም አልጸልይም ። 10 የእኔ የሆነው ሁሉ የአ
ንተ ነው ፤ የአንተም የሆነው የእኔ ነው ፤ እኔም
በእነርሱ እከብራለሁ ። 11 እኔ ከእንግዲህ ወዲህ
በዓለም ላይ አልኖርም ፤ እነርሱ ግን በዓለም
ናቸው ። እኔ ወደ አንተ መምጣቴ ነው ፤ ቅዱስ
አባት ሆይ! እነዚህ የሰጠኸኝ እንደእኛ አንድ
እንዲሆኑ ለእኔ በሰጠኸኝ ስምህ ጠብቃቸው ።[*]
12 እኔ አብሬአቸው በነበርሁ ጊዜ ፥ በሰጠኸኝ
ስምህ ጠብቄአቸዋለሁ ፤[**] እኔ ጠበቅኋቸው ፤
ስለዚህ የተጻፈው የትንቢት ቃል እንዲፈጸም
ከዚያ ከጥፋት ልጅ በቀር ከቶ ከእነርሱ ማንም
አልጠፋም ። 13 አሁን እኔ ወደ አንተ መምጣቴ
ነው ፤ በዓለም ላይ ሳለሁ ይህን የምናገረው ደስ
ታዬ በእነርሱ ፍጹም እንዲሆን ነው ። 14 እኔ
ቃልህን ሰጥቼአቸዋለሁ ፤ እኔ ከዓለም እንዳይደ
ለሁ እነርሱም ከዓለም አይደሉም ፤ ስለዚህ
ዓለም ጠላቸው ። 15 ከክፉው እንድትጠብቃ
ቸው እንጂ ከዓለም ውጪ እንድትወስዳቸው
አልለምንም ። 16 እኔ ከዓለም እንዳይደለሁ ፥ እነ
ርሱም ከዓለም አይደሉም ። 17 በእውነትህ ቀድ
ሳቸው ፤ ቃልህ እውነት ነው ። 18 አንተ እኔን
ወደ ዓለም እንደላከኸኝ እኔም እነርሱን ወደ
ዓለም ላክኋቸው ። 19 እነርሱ በእውነት ቅዱሳን
እንዲሆኑ ፥ እኔ ራሴን ስለ እነርሱ ቅዱስ አደር
ጋለሁ ።

20 "በእነርሱ ቃል አማካይነት በእኔ ስለሚያ
ምኑትም እለምናለሁ እንጂ ለእነርሱ ብቻ አል
ለምንም ። 21 እኔም የምለምነው ፥ ሁሉም
አንድ እንዲሆኑ ነው ፤ እንዲሁም አባት ሆይ!
አንተ በእኔ እንዳለህ ፥ እኔም በአንተ እንዳለሁ ፥
እነርሱም በእኛ እንዲሆኑ ነው ፤ አንተ እንደላ
ከኸኝም ዓለም እንዲያምን ነው ። 22 እኛ አንድ
እንደሆንን ፥ እነርሱም አንድ እንዲሆኑ ፥ ለእኔ
የሰጠኸኝን ክብር ሰጥቼአቸዋለሁ ። 23 እኔ የምለ
ምነው ፥ እኔ በእነርሱ ፥ አንተም በእኔ እንደሆ
ንህ ፥ እነርሱም በፍጹም አንድ እንዲሆኑ ነው ፤
እንዲሁም እኔን እንደላክኸኝና እኔን በወደድ
ኸኝ መጠን እነርሱንም እንደወደድሃቸው
ዓለም እንዲያውቅ ነው ።

24 "አባት ሆይ! ዓለም ሳይፈጠር ስለወደድ
ኸኝ የሰጠኸኝን ክብሬን እንዲያዩ ፥ እነዚህ
አንተ የሰጠኸኝም እኔ ባለሁበት ከእኔ ጋር እን
ዲኖሩ እወድዳለሁ ። 25 ጻድቅ አባት ሆይ!
ዓለም አላወቀህም ፤ እኔ ግን ዐውቅሃለሁ ፤ እነዚ
ህም አንተ እንደላክኸኝ ዐውቀዋል ። 26 አንተ
እኔን የወደድህበት ፍቅር በእነርሱ እንዲሆንና
እኔም በእነርሱ እንድሆን ፥ እነርሱ አንተን እን
ዲያውቁ አድርጌአለሁ ፤ ደግሞም እንዲያውቁ
አደርጋቸዋለሁ ።"

## ምዕራፍ 18

### ኢየሱስ በጠላቶቹ ተያዘ
(ማቴ. 26፥47-56፤ ማር. 14፥43-50፤
ሉቃ. 22፥47-53)

1 ኢየሱስ ይህን ካለ በኋላ ከደቀ መዛሙርቱ
ጋር ወደ ቄድሮን ወንዝ ማዶ ሄደ ፤ እዚያ ወደ
ነበረውም የአትክልት ቦታ ከደቀ መዛሙርቱ
ጋር ገባ ። 2 ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ እዚያ
ቦታ ዘወትር ይሰበሰቡ ስለነበር ፥ አሳልፎ የሰ
ጠው ይሁዳ ያን ቦታ ያውቅ ነበር ። 3 ስለዚህ
ይሁዳ ወታደሮቹን ከካህናት አለቆችና ከፈሪሳ
ውያን የተላኩትን ሎሌዎች አስከትሎ ወደዚያ
ቦታ መጣ ፤ እነርሱም ፋኖስና ችቦ ፥ የጦር
መሣሪያም ይዘው ነበር ። 4 ኢየሱስም የሚደርስ
በትን ሁሉ ዐውቆ ወደ እነርሱ ሄደና "ማንን
ትፈልጋላችሁ?" አላቸው ።
5 እነርሱም "የናዝሬቱን ኢየሱስ እንፈልጋ
ለን" አሉት ።
እርሱም "እኔ ነኝ" አላቸው ።
አሳልፎ የሰጠው ይሁዳም ከእነርሱ ጋር
ቆሞ ነበር ። 6 ኢየሱስ "እኔ ነኝ" ባላቸው ጊዜ
ወደ ኋላ አፈገፈጉና በምድር ላይ ወደቁ ።
7 ኢየሱስም "ማንን ትፈልጋላችሁ?" ሲል እን
ደገና ጠየቃቸው ።
እነርሱም "የናዝሬቱን ኢየሱስ እንፈልጋ
ለን" አሉ ።
8 እርሱም "እኔ ነኝ ብዬአችኋለሁ ፤ እንግ
ዲህ የምትፈልጉት እኔን ከሆነ እነዚህን ተዉአ
ቸው ፥ ይሂዱ" አለ ። 9 ይህም የሆነው "አባት
ሆይ! ከሰጠኸኝ ሰዎች አንዱን እንኳ አላጠፋ
ሁም" ያለው ቃል እንዲፈጸም ነው ።
10 ስምዖን ጴጥሮስ ሰይፍ ይዞ ስለ ነበረ መዘ
ዘና የሊቀ ካህናቱን አገልጋይ መትቶ ቀኝ ጆሮ
ውን ቈረጠ ፤ የአገልጋዩም ስም "ማልኮስ"
ይባል ነበር ። 11 ኢየሱስ ግን ጴጥሮስን "ሰይፍ
ህን ወደ አፎቱ ክተተው ፤ አብ የሰጠኝን የመ
ከራ ጽዋ የማልጠጣው ይመስልሃልን?"
አለው ።

### ኢየሱስ በሊቀ ካህናቱ
### በሐና ፊት ቀረበ

12 ከዚህ በኋላ ወታደሮቹና አዛዦቻቸው ፥ የአ
ይሁድ ሎሌዎችም ኢየሱስን ይዘው አሰሩት ።
13 በመጀመሪያ ወደ ሐና ወሰዱት ፤ ሐና በዚያ
ዓመት ሊቀ ካህናት ለነበረው ለቀያፋ ሀማቱ



ነበር ። 14 ቀያፋ "አንድ ሰው ስለ ሕዝቡ
ቢሞት የተሻለ ነው" ሲል አይሁዳውያን ባለሥ
ልጣኖችን የመከረ ነው ።

### ጴጥሮስ ኢየሱስን ካደ
(ማቴ. 26፥69-70፤ ማር. 14፥66-68፤
ሉቃ. 22፥55-57)

15 ስምዖን ጴጥሮስና ሌላው ደቀ መዝሙር
ኢየሱስን ተከተሉት ፤ ያ ሌላው ደቀ መዝሙር
በሊቀ ካህናቱ ዘንድ የታወቀ ነበር ፤ ስለዚህ
ከኢየሱስ ጋር ወደ ሊቀ ካህናቱ ግቢ ገባ ፤
16 ጴጥሮስ ግን በውጭ በበሩ አጠገብ ቆሞ
ነበር ፤ በሊቀ ካህናቱ የታወቀው ደቀ መዝሙር
መጣና ለበረኛይቱ ገረድ ነግሮ ጴጥሮስን አስገ
ባው ፤ 17 በረኛይቱም ገረድ ጴጥሮስን "አንተም
ከዚህ ሰው ደቀ መዛሙርት አንዱ አይደለህ
ምን?" አለችው ።
እርሱ ግን "አይደለሁም" አለ ።
18 ጊዜው ብርድ ስለ ነበረ አገልጋዮቹና
ሎሌዎች የከሰል እሳት አንድደው ፥ ቆመው
ይሞቁ ነበር ፤ ጴጥሮስም ከእነርሱ ጋር ቆሞ
ይሞቅ ነበር ።

### ከሊቀ ካህናቱ ለኢየሱስ የቀረበ ጥያቄ
(ማቴ. 26፥59-66፤ ማር. 14፥55-64፤
ሉቃ. 22፥66-71)

19 በዚያን ጊዜ ሊቀ ካህናቱ ኢየሱስን ስለ
ደቀ መዛሙርቱና ስለ ትምህርቱ ጠየቀው ።
20 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት ፥ "እኔ
ለሰው ሁሉ በግልጥ ተናገርሁ ፤ አይሁዳውያን
ሁሉ በሚሰበሰቡበት በምኵራብም ሆነ በቤተ
መቅደስ ሁልጊዜም አስተማርሁ ፤ በስውር የተ
ናገርሁት ምንም ነገር የለም ፤ 21 ታዲያ ስለምን
እኔን ትጠይቀኛለህ? ስናገራቸው የሰሙኝን
ጠይቃቸው ፤ የተናገርሁትን እነርሱ ያው
ቃሉ ።"
22 ኢየሱስ ይህን በተናገረ ጊዜ እዚያ ቆመው
ከነበሩት ሎሌዎች አንዱ "ለሊቀ ካህናቱ የም
ትመልሰው እንዲህ ነውን?" ብሎ ኢየሱስን
በጥፊ መታው ።
23 ኢየሱስም "ክፉ ቃል ተናግሬ እንደሆን
ክፉ መናገሬን መስክር ፤ የተናገርሁት ትክክል
ከሆነ ግን ስለምን ትመታኛለህ?" አለው ።
24 ከዚህ በኋላ ሐና ኢየሱስ እንደ ታሰረ ወደ
ሊቀ ካህናቱ ወደ ቀያፋ ሰደደው ።

### ጴጥሮስ ኢየሱስን እንደገና ካደ
(ማቴ. 26፥71-75፤ ማር. 14፥69-72፤
ሉቃ. 22፥58-62)

25 የዚያን ጊዜ ስምዖን ጴጥሮስ ቆሞ እሳት
ይሞቅ ነበር ፤ ሌሎች ሰዎችም "አንተስ ከኢየ
ሱስ ደቀ መዛሙርት አንዱ አይደለህምን?"
አሉት ።
እርሱም "አይደለሁም" ብሎ ካደ ።
26 ጴጥሮስ ጆሮውን የቈረጠው ሰው ዘመዱ
የሆነው ፥ ከሊቀ ካህናቱ ሎሌዎች አንዱ "በአ
ትክልቱ ቦታ ከእነርሱ ጋር አይቼህ አልነበረ
ምን?" አለው ።
27 ጴጥሮስም እንደገና ካደ ፤ ወዲያውኑ ዶሮ
ጮኸ ።

### ኢየሱስ በጲላጦስ ፊት ቀረበ
(ማቴ. 27፥1-2፥11-14፤ ማር. 15፥1-5፤
ሉቃ. 23፥1-5)

28 ከዚህ በኋላ ኢየሱስን ከቀያፋ ቤት ወደ
ገዥው ግቢ ወሰዱት ፤ ጊዜውም ጠዋት ማለዳ
ነበር ፤ አይሁዳውያን የፋሲካን በግ መብላት
ስለነበረባቸው እንዳይረክሱ በማለት ወደ ገዥው
ግቢ ውስጥ አልገቡም ። 29 ስለዚህ ጲላጦስ ወደ
እነርሱ ወጣና "በዚህ ሰው ላይ ያቀረባችሁት
ክስ ምንድን ነው?" ሲል ጠየቃቸው ።
30 እነርሱም "ይህ ሰው ክፉ አድራጊ ባይ
ሆን ኖሮ ለአንተ አሳልፈን ባልሰጠነውም
ነበር" ሲሉ መለሱለት ።
31 ጲላጦስም "እናንተ ራሳችሁ ወስዳችሁ
በሕጋችሁ መሠረት ፍረዱበት" አላቸው ።
አይሁዳውያን ባለሥልጣኖችም "እኛ ሰው
ለመግደል መብት የለንም" አሉት ። 32 ይህም
የሆነው ኢየሱስ በምን ዐይነት ሞት እንደሚ
ሞት የተናገረው ቃል እንዲፈጸም ነው ።
33 ጲላጦስ እንደገና ወደ ግቢው ተመልሶ
ገባ ፤ ኢየሱስንም ጠርቶ "አንተ የአይሁድ
ንጉሥ ነህን?" ሲል ጠየቀው ።
34 ኢየሱስ "አንተ ይህን የምትለው ከራስህ
ነውን? ወይስ ሌሎች ይህን ስለ እኔ ነግረው
ሃል?" አለው ።
35 ጲላጦስም "እኔ አይሁዳዊ ነኝን? አንተን
ለእኔ አሳልፈው የሰጡህ ወገኖችህና የካህናት
አለቆች ናቸው ፤ ምንድን ነው ያደረግኸው?"
አለው ።
36 ኢየሱስ "የእኔ መንግሥት ከዚህ ዓለም
አይደለችም ፤ መንግሥቴ ከዚህ ዓለም ብትሆን
ኖሮ በአይሁዳውያን ባለሥልጣኖች እጅ እንዳል
ወድቅ ሎሌዎቼ በተዋጉልኝ ነበር ፤ መንግሥቴ
ግን ከዚህ ዓለም አይደለችም" ሲል መለሰ ።
37 ጲላጦስም "ታዲያ አንተ ንጉሥ ነህን?"
አለው ።
ኢየሱስም "አንተ እንዳልኸው ነኝ ፤ እኔ
የተወለድሁትና ወደ ዓለም የመጣሁት ስለ እው
ነት ለመመስከር ነው ፤ ከእውነት የሆነ ሁሉ
ድምፄን ይሰማል" ሲል መለሰ ።

[*] 17፥11 ለእኔ በሰጠኸኝ ስምህ ጠብቃቸው ፦ አንዳንድ ቅጂዎች "ለእኔ የሰጠኸኝን ሁሉ ፥ በስምህ ጠብቃቸው" ይላሉ ።
[**] 17፥12 በሰጠኸኝ ስምህ ጠብቄአቸዋለሁ ፦ አንዳንድ ቅጂዎች "የሰጠኸኝን ሁሉ በስምህ ጠብቄአቸዋለሁ" ይላሉ ።
17፥12 ፦ መዝ. 41፥9 ፤ ዮሐ. 13፥18 ። 18፥11 ፦ ማቴ. 26፥39 ፤ ማር. 14፥36 ፤ ሉቃ. 22፥42 ።

18፥14 ፦ ዮሐ. 11፥49-50 ። 18፥32 ፦ ዮሐ. 3፥14 ፤ 12፥32 ።

38 ጲላጦስም “እውነት ምንድን ነው?”
አለ። ከዚህ በኋላ ጲላጦስ እንደገና ወደ አይሁ
ዳውያን ወጣና እንዲህ አላቸው፣ “እኔ ምንም
ጥፋት አላገኘሁበትም፤ 39 ነገር ግን በልማዳ
ችሁ መሠረት በፋሲካ በዓል ሁል ጊዜ አንድ
እስረኛ እፈታላችኋለሁ፤ ስለዚህ የአይሁዳውያ
ንን ንጉሥ እንድፈታላችሁ ትፈልጋላችሁን?”
40 እነርሱ ግን “በርባንን ፍታልን እንጂ
ይህን አይደለም!” እያሉ ጮኹ። በርባን ግን
ወንበዴ ነበር።

## ምዕራፍ 19

### ወታደሮች በኢየሱስ አፌዙበት
(ማቴ. 27፡27-32፤ ማር. 15፡15-21)

1 ከዚህ በኋላ ጲላጦስ ኢየሱስን ወስዶ አስገ
ረፈው። 2 ወታደሮችም የእሾህ አክሊል ጐንጉ
ነው በኢየሱስ ራስ ላይ አደረጉ፤ ቀይ ካባም
አለበሱት። 3 ወደ እርሱም እየመጡ በማፌዝ
“የአይሁድ ንጉሥ ሆይ! ሰላም ላንተ ይሁን!”
ይሉት ነበር፤ በጥፊም ይመቱት ነበር።
4 ጲላጦስ እንደገና ወደ ውጭ ወጥቶ “እነሆ
ምንም በደል እንዳላገኘሁበት እንድታውቁ፣
እርሱን ወደ ውጭ አወጣላችኋለሁ” አላቸው፤
5 ስለዚህ ኢየሱስ የእሾህ አክሊል ደፍቶና ቀይ
ካባ ለብሶ ወደ ውጭ ወጣ፤ ጲላጦስም “እነሆ
ሰውየው!” አላቸው።
6 የካህናት አለቆችና ሎሌዎች ኢየሱስን
ባዩት ጊዜ “ስቀለው! ስቀለው!” እያሉ ጮኹ።
ጲላጦስ ግን “እኔ በበኩሌ ምንም በደል አላ
ገኘሁበትም፤ ብትፈልጉ እናንተ ወስዳችሁ ስቀ
ሉት” አላቸው።
7 አይሁዳውያንም “እኛ ሕግ አለን፤ ይህ
ሰው ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ ስላደረገ በሕጋ
ችን መሠረት መሞት ይገባዋል” አሉ። 8 ይህን
ሁሉ ንግግር በሰማ ጊዜ ጲላጦስ በይበልጥ
ፈራ፤ 9 ወደ ግቢው ገባና ኢየሱስን “አንተ
ከየት ነህ?” ሲል ጠየቀው።
ኢየሱስ ግን ምንም አልመለሰለትም። 10 ስለ
ዚህ ጲላጦስ “አትነግረኝምን? እኔ ልፈታህ
ወይም ልሰቅልህ ሥልጣን እንዳለኝ አታውቅ
ምን?” አለው፤
11 ኢየሱስም “ከእግዚአብሔር ሥልጣን ባይ
ሰጥህ ኖሮ በእኔ ላይ ምንም ሥልጣን ባልኖረህ
ነበር፤ ሆኖም ለአንተ አሳልፎ የሰጠኝ የባሰ
ኃጢአት አለበት” አለው።

### ኢየሱስ የሞት ፍርድ ተፈረደበት
(ማቴ. 27፡15-31፤ ማር. 15፡6-20፤
ሉቃ. 23፡13-25)

12 ጲላጦስ ይህን የኢየሱስን አነጋገር በሰማ
ጊዜ ፈትቶ ሊለቀው ፈልጎ ነበር፤ አይሁዳው
ያን ግን “ይህን ሰው ከፈታኸው የሮም ንጉሠ
ነገሥት የቄሳር ወዳጅ አይደለህም፤ ምክንያ
ቱም ራሱን ንጉሥ የሚያደርግ ሁሉ የቄሳር
ጠላት ነው!” እያሉ ጮኹ።
13 ጲላጦስ ይህን በሰማ ጊዜ ኢየሱስን ወደ
ውጪ አስወጥቶ “ጠፍጣፋ ድንጋይ” በተባለው
ስፍራ በፍርድ ወንበር ተቀመጠ፤ ይህ ስፍራ
በዕብራይስጥ ቋንቋ “ገበታ” ይባላል። 14 የፋ
ሲካ ዝግጅት ቀን ነበረ፤ ጊዜውም ወደ ስድስት
ሰዓት ገደማ ነበረ፤ በዚያን ጊዜ ጲላጦስ አይሁ
ዳውያንን “እነሆ ንጉሣችሁ!” አላቸው።
15 እነርሱ ግን “ወዲያ ውሰደው! ወዲያ
ውሰደው! ስቀለው!” እያሉ ጮኹ።
ጲላጦስም “ንጉሣችሁን ልስቀለውን?” አላ
ቸው።
የካህናት አለቆችም “ከቄሳር በቀር ሌላ
ንጉሥ የለንም” ሲሉ መለሱለት።
16 በዚህ ጊዜ ኢየሱስ እንዲሰቀል ጲላጦስ
አሳልፎ ሰጣቸው። እነርሱም ኢየሱስን ይዘው
ወሰዱት።

### ኢየሱስ ተሰቀለ
(ማቴ. 27፡32-44፤ ማር. 15፡21-32፤
ሉቃ. 23፡26-43)

17 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ መስቀሉን ተሸክሞ
“የራስ ቅል” ወደሚባለው ስፍራ ወጣ፤ ይህ
ስፍራ በዕብራይስጥ ቋንቋ “ጎልጎታ” ይባላል፤
18 እዚያ ሰቀሉት፤ ኢየሱስን በመካከል አድር
ገው ከእርሱ ጋር ሌሎችንም ሁለት ሰዎች በግ
ራና በቀኝ ሰቀሉ። 19 ጲላጦስ “የናዝሬቱ ኢየ
ሱስ፣ የአይሁድ ንጉሥ” የሚል ማስታወቂያ
ጽፎ በመስቀሉ ላይ እንዲኖር አደረገ። 20 ኢየ
ሱስ የተሰቀለበት ስፍራ ለከተማ ቅርብ ስለነበር
ብዙዎቹ አይሁዳውያን ማስታወቂያውን አነበ
ቡት፤ ማስታወቂያውም የተጻፈው በዕብራይ
ስጥ፣ በላቲንና በግሪክ ቋንቋ ነበር። 21 የአይሁ
ዳውያን ካህናት አለቆች ጲላጦስን “አንተ ‘የአ
ይሁድ ንጉሥ’ ብለህ አትጻፍ፤ ነገር ግን ‘ይህ
ሰው እኔ የአይሁድ ንጉሥ ነኝ’ ብሎአል ብለህ
ጻፍ” አሉት።
22 ጲላጦስ ግን “የጻፍሁትን ጽፌአለሁ”
ሲል መለሰ።
23 ወታደሮቹ ኢየሱስን ከሰቀሉት በኋላ ልብ
ሶቹን ወስደው ለእያንዳንዱ ወታደር አንድ
ክፍል እንዲደርስ በአራት ከፋፈሉአቸው፤ እጀ
ጠባቡንም እንዲሁ አደረጉ፤ ነገር ግን እጀ
ጠባቡ ሳይሰፋ ከላይ እስከታች ወጥ ሆኖ የተ
ሠራ ነበር፤ 24 ስለዚህ ወታደሮቹ “ለማን እንደ
ሚደርስ ለማወቅ ዕጣ እንጣጣልበት እንጂ አን
ቀደደው” ተባባሉ። ይህም የሆነው፣





“ልብሴን ተከፋፈሉ፣
በእጀ ጠባቤም ዕጣ ተጣጣሉ”
የሚለው የመጽሐፍ ቃል እንዲፈጸም ነው፤
ወታደሮቹም እንዲሁ አደረጉ።
25 በኢየሱስ መስቀል አጠገብ እናቱና የእ
ናቱ እኅት፣ የቀልዮጳ ሚስት ማርያምና መግደ
ላዊት ማርያም ቆመው ነበር፤ 26 ኢየሱስ እናቱ
ንና የሚወድደውን ደቀ መዝሙር አጠገቡ
ቆመው ባያቸው ጊዜ፣ እናቱን “እናቴ ሆይ!
እነሆ ልጅሽ!” አላት።
27 ከዚህ በኋላ ደቀ መዝሙሩን “ይህችው
ልህ እናትህ!” አለው፤ ከዚያ ሰዓት ጀምሮ
ደቀ መዝሙሩ ወደ ቤቱ ወሰዳት።

### ኢየሱስ ሞተ
(ማቴ. 27፡45-56፤ ማር. 15፡33-41፤
ሉቃ. 23፡44-49)

28 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ አሁን ሁሉም ነገር
እንደተፈጸመ ዐውቆ በመጽሐፍ የተጻፈውም
ቃል እንዲፈጸም “ጠማኝ” አለ።
29 እዚያ ሆምጣጤ የሞላበት ዕቃ ተቀምጦ
ነበር፤ ስለዚህ እዚያ የነበሩ ሰዎች ሆምጣጤ
ውን በስፖንጅ ሞልተው በሂሶፕ እንጨት አንጠል
ጥለው ወደ አፉ አቀረቡለት፤ 30 ኢየሱስም
ሆምጣጤውን ከቀመሰ በኋላ “ተፈጸመ!”
አለ።
ራሱን ዘንበል አድርጎም ነፍሱን አሳልፎ
ሰጠ።

### ኢየሱስ ጐኑን በጦር ተወጋ

31 ከዚህ በኋላ አይሁዳውያን ባለሥልጣኖች
የተሰቀሉትን ሰዎች ጭን ሰብረው ከመስቀል
እንዲያወርዱአቸው ጲላጦስን ለመኑት፤ ይህን
ንም ያደረጉበት ምክንያት የሰንበት ዝግጅት
ቀን ስለነበረና ያ ሰንበትም ትልቅ በዓል ስለሆነ
በሰንበት ቀን ሥጋቸው በመስቀል ላይ እንዳይ
ሆን ነበር። 32 ስለዚህ ወታደሮቹ ሄደው ከኢየ
ሱስ ጋር የተሰቀሉትን ሰዎች ጭን ሰበሩ፤
33 ወደ ኢየሱስ በሄዱ ጊዜ ግን እርሱ ቀደም
ብሎ እንደሞተ አይተው ጭኑን አልሰበሩም።
34 ነገር ግን ከወታደሮቹ አንዱ፣ ጐኑን በጦር
ወጋው፤ ወዲያውኑ ከጐኑ ደምና ውሃ ወጣ።
35 ይህንን ያየ፣ እናንተ እንድታምኑ መሰከረ፤
ምስክርነቱም እውነት ነው፤ የሚናገረውም
እውነት እንደሆነ እርሱ ያውቃል። 36 ይህም
የሆነው “ከእርሱ አንድ አጥንት እንኳ አይሰበ
ርም” የሚለው የመጽሐፍ ቃል እንዲፈጸም
ነው። 37 ደግሞም ሌላ የትንቢት መጽሐፍ
“ያንን የወጉትን ያዩታል” ይላል።

### ኢየሱስ ተቀበረ
(ማቴ. 27፡57-61፤ ማር. 15፡42-47፤
ሉቃ. 23፡50-56)

38 አይሁዳውያን ባለሥልጣኖችን በመፍራት
በስውር የኢየሱስ ደቀ መዝሙር የነበረው የአር
ማትያሱ ዮሴፍ የኢየሱስን አስከሬን ለመውሰድ
ጲላጦስን ለመነ። ጲላጦስም ፈቀደለት። ስለ
ዚህ ዮሴፍ ሄዶ አስከሬኑን ወሰደ። 39 ከዚህ
በፊት በሌሊት ወደ ኢየሱስ ሄዶ የነበረው ኒቆ
ዲሞስም ሃያ አምስት ኪሎ ግራም የሚያህል
የከርቤና የሬት ቅልቅል ይዞ መጣ። 40 ሁለቱ
ሰዎች የኢየሱስን አስከሬን ወስደው እንደ አይ
ሁዳውያን አገናነዝ ልማድ ከሽቶ ጋር በቀጭን
ልብስ ከፈኑት። 41 ኢየሱስ ተሰቅሎ በነበረበት
ቦታ አንድ የአትክልት ስፍራ ነበረ፤ በዚያም
የአትክልት ስፍራ ውስጥ ማንም ያልተቀበረበት
አዲስ መቃብር ነበር። 42 የአይሁድ ሰንበት ዝግ
ጅት ቀን ስለ ነበረና መቃብሩም ቅርብ ስለነ
በረ፣ የኢየሱስን አስከሬን እዚያ ቀበሩት።

## ምዕራፍ 20

### ኢየሱስ ከሞት ተነሣ
(ማቴ. 28፡1-8፤ ማር. 16፡1-8፤ ሉቃ. 24፡1-12)

1 እሑድ ጠዋት በማለዳ ገና ጎሕ ሳይቀ
ድድ፣ መግደላዊት ማርያም ወደ ኢየሱስ መቃ
ብር ሄደች። እዚያም እንደደረሰች መቃብሩ
ተዘግቶበት የነበረው ድንጋይ ከመቃብሩ በር
ላይ ተነሥቶ አየች። 2 ስለዚህ እርስዋ ወደ ስም
ዖን ጴጥሮስና ኢየሱስ ወደሚወደው ወደ
ሌላው ደቀ መዝሙር እየሮጠች ሄደችና
“ጌታን ከመቃብሩ አውጥተው ወስደውታል፤
የት እንዳኖሩት አላውቅም” አለቻቸው።
3 በዚህ ጊዜ ጴጥሮስና ሌላው ደቀ መዝሙር
ወጡና ወደ መቃብሩ ሄዱ። 4 ሁለቱም አብረው
ይሮጡ ነበር፤ ነገር ግን ሌላው ደቀ መዝሙር
ከጴጥሮስ ይበልጥ ፈጥኖ ሮጠና ቀድሞ ወደ መቃ
ብሩ ደረሰ። 5 ጐንበስ ብሎም ወደ መቃብሩ ቢመ
ለከት የከፈኑ ጨርቅ እዚያ ተቀምጦ አየ፤ ነገር
ግን ወደ ውስጥ አልገባም። 6 ስምዖን ጴጥሮስም
ተከትሎት መጣና ወደ መቃብሩ ውስጥ ገባ፤ እር
ሱም የከፈኑን ጨርቅ እዚያ ተቀምጦ አየ፤ 7 የኢ
የሱስ ራስ ተጠምጥሞ የነበረበት ጨርቅ ከከፈኑ
ጨርቅ ጋር ሳይሆን ለብቻው በሌላ ስፍራ ተጠቅ
ልሎ እንደተቀመጠ አየ። 8 ቀጥሎም ያ ቀድሞ
የደረሰው ደቀ መዝሙር ወደ መቃብሩ ውስጥ
ገብቶ አየና አመነ። 9 ምክንያቱም “ከሞት መነ
ሣት ይገባዋል” የሚለውን የመጽሐፍ ቃል ገና
አልተገነዘቡም ነበር። 10 ከዚህ በኋላ ሁለቱም
ደቀ መዛሙርት ተመልሰው ወደ ቤታቸው ሄዱ።

19፡28 ፦ መዝ. 69፡21፤ 22፡15። 19፡36 ፦ ዘጸ. 12፡46፤ ዘኍ. 9፡12፤ መዝ. 34፡20። 19፡37 ፦ ዘካ. 12፡10፤ ራእ. 1፡7።
19፡39 ፦ ዮሐ. 3፡1-2።

### ኢየሱስ ለመግደላዊት ማርያም ታየ
(ማቴ. 28፥9-10፤ ማር. 16፥9-11)

11 መግደላዊት ማርያም እያለቀሰች ከመቃ
ብሩ በስተውጭ ቆማ ነበር ፤ እያለቀሰችም ጐን
በስ ብላ ወደ መቃብሩ ውስጥ ተመለከተች ።
12 የኢየሱስ አስከሬን በነበረበት ስፍራ ነጭ
ልብስ የለበሱ ሁለት መላእክት አንዱ በራስጌ
አንዱ በግርጌ ተቀምጠው አየች ። 13 እነርሱም
ማርያምን "አንቺ ሴት! ለምን ታለቅሻለሽ?"
አሉዋት ።
እርስዋም "ጌታዬን ወስደውታል ፤ የት እን
ዳደረጉትም አላውቅም" አለች ።
14 ይህንንም ብላ ወደ ኋላዋ ዞወር ስትል ፤
ኢየሱስን ቆሞ አየችው ፤ ኢየሱስ መሆኑን ግን
አላወቀችም ። 15 ኢየሱስ "አንቺ ሴት! ስለ ምን
ታለቅሻለሽ ፤ ማንንስ ትፈልጊያለሽ?" አላት ።
እርስዋም አትክልተኛው መስሎዋት "ጌታ
ሆይ! አንተ ወስደኸው እንደሆነ የት እንዳደረግ
ኸው እባክህ ንገረኝ ፤ እኔ እወስደዋለሁ" አለ
ችው ።
16 ኢየሱስም "ማርያም" አላት ። እርስዋም
ወደ እርሱ ዞር ብላ በዕብራይስጥ ቋንቋ
"ረቡኒ!" አለችው ፤ ትርጓሜውም "መምህር
ሆይ!" ማለት ነው ።
17 ኢየሱስ "ገና ወደ አባቴ አልወጣሁምና
አትያዥኝ ፤ ነገር ግን ወደ ወንድሞቼ ሂጂና
'እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ፤ ወደ አምላ
ኬና ወደ አምላካችሁ እወጣለሁ ብሎአል'
ብለሽ ንገሪያቸው" አላት ።
18 ስለዚህ መግደላዊት ማርያም ወደ ደቀ
መዛሙርቱ ሄዳ ጌታን እንዳየችና ይህንንም እን
ዳላት ነገረቻቸው ።

### ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ታየ
(ማቴ. 28፥16-20፤ ማር. 16፥14-18፤
ሉቃ. 24፥36-49)

19 በዚያኑ ቀን እሑድ ማታ ደቀ መዛሙርቱ
አይሁዳውያን ባለሥልጣኖችን በመፍራት በራፎ
ቹን ዘግተው በቤት ውስጥ ተሰብስበው ነበር ፤
በሮቹ ተዘግተው ሳለ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ
ወደ ተሰበሰቡበት ቤት ገባ ፤ በመካከላቸውም
ቆሞ "ሰላም ለእናንተ ይሁን!" አላቸው ።
20 ይህንንም ብሎ እጆቹንና ጐኑን አሳያቸው ፤
ደቀ መዛሙርቱም ጌታን ባዩ ጊዜ ደስ አላ
ቸው ። 21 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ እንደገና "ሰላም
ለእናንተ ይሁን! አብ እኔን እንደላከኝ እኔም
እናንተን እልካችኋለሁ" አላቸው ። 22 ይህን
ብሎ እፍ አለባቸውና "መንፈስ ቅዱስን ተቀ
በሉ ፤ 23 እናንተ የሰዎችን ኃጢአት ይቅር
ብትሉ ይቅር ይባልላቸዋል ፤ እናንተ የሰዎችን
ኃጢአት ይቅር ባትሉ ግን ይቅር አይባልላቸ
ውም" አላቸው ።

### ኢየሱስና ቶማስ

24 ኢየሱስ ወደ ደቀ መዛሙርቱ በመጣ ጊዜ
ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ ፥ ዲዲሞስ የተባለው
ቶማስ ከእነርሱ ጋር አልነበረም ። 25 ስለዚህ
ሌሎች ደቀ መዛሙርት ቶማስን "ጌታን እኮ
አየነው" አሉት ።
እርሱ ግን "በምስማር የተወጉትን እጆቹን
ካላየሁና ጣቴን ካላገባሁ ፥ እጄንም በጐኑ
ቍስል ካላገባሁ አላምንም" አላቸው ።
26 ከስምንት ቀን በኋላ ደቀ መዛሙርቱ እን
ደገና በቤት ውስጥ ነበሩ ፤ ቶማስም አብሮአ
ቸው ነበር ፤ በሮቹ ተዘግተው ሳሉ ኢየሱስ
መጥቶ በመካከላቸው ቆመና "ሰላም ለእናንተ
ይሁን!" አላቸው ። 27 ከዚህ በኋላ ቶማስን ፤
"ጣትህን ወዲህ አምጣና እጆቼን እይ ፤ እጅህ
ንም አምጣና በጐኔ ውስጥ አግባው ፤ እመን
እንጂ እምነተ ቢስ አትሁን" አለው ።
28 ቶማስም "ጌታዬ! አምላኬ!" ሲል መለሰ
ለት ።
29 ኢየሱስም ቶማስን "አንተስ ስለአየኸኝ
አመንህ ፤ ሳያዩኝ የሚያምኑ ግን የተመሰገኑ
ናቸው" አለው ።

### የዚህ መጽሐፍ ዓላማ

30 ኢየሱስ በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ ብዙ
ተአምር በደቀ መዛሙርቱ ፊት አድርጓል ፤
31 ነገር ግን ኢየሱስ መሲሕ የእግዚአብሔር
ልጅ መሆኑን እንድታምኑና ፥ አምናችሁም በእ
ርሱ ስም የዘላለም ሕይወት እንድታገኙ ይህ
ተጽፎአል ።

## ምዕራፍ 21

### ኢየሱስ ለሰባቱ ደቀ መዛሙርት ታየ

1 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በጥብርያዶስ ባሕር
አጠገብ ለደቀ መዛሙርቱ እንደገና ታየ ፤ የታየ
ውም እንዲህ ነው ፥ 2 ስምዖን ጴጥሮስ ፥ ዲዲ
ሞስ የተባለው ቶማስ ፥ የገሊላ ቃና የሆነው
ናትናኤል ፥ የዘብዴዎስ ልጆችና ሌሎች ሁለት
ደቀ መዛሙርትም አብረው ነበሩ ። 3 ስምዖን
ጴጥሮስ "ዓሣ ለማጥመድ መሄዴ ነው" አላ
ቸው ።
እነርሱም "ከአንተ ጋር እንሄዳለን"
አሉት ። ወጥተውም ሄዱና ወደ ጀልባ ገቡ ፤
ነገር ግን በዚያች ሌሊት አንድ ዓሣ እንኳ አል
ያዙም ። 4 ሲነጋ ኢየሱስ በባሕሩ ዳር ቆመ ፤
ደቀ መዛሙርቱ ግን ኢየሱስ መሆኑን አላወ
ቁም ። 5 ኢየሱስም "ልጆች ሆይ! ዓሣ አላች
ሁን?" አላቸው ።

20፥23 ፦ ማቴ. 16፥19 ፤ 18፥18 ። 21፥3 ፦ ሉቃ. 5፥5 ።



እነርሱም "ምንም የለንም" አሉት ።
6 እርሱም "መረቡን ከጀልባው በስተቀኝ
ጣሉና ታገኛላችሁ" አላቸው ። ስለዚህ መረቡን
በባሕሩ ውስጥ ጣሉት ፤ ብዙ ዓሣም ከመያዛ
ቸው የተነሣ መረቡን መጐተት አቃታቸው ።
7 በዚህ ጊዜ ኢየሱስ የሚወድደው ደቀ መዝ
ሙር ጴጥሮስን ፥ "ጌታ ነው እኮ!" አለው ።
ስምዖን ጴጥሮስ "ጌታ ነው እኮ!" ማለትን
በሰማ ጊዜ ፥ ለሥራ ብሎ ልብሱን አውልቆ ስለ
ነበረ ወዲያው ልብሱን ለበሰና ወደ ባሕሩ
ዘልሎ ገባ ። 8 ሌሎች ደቀ መዛሙርት ግን ከም
ድር የራቁት መቶ ሜትር ያህል ብቻ ስለነበረ ፥
ዓሣ የሞላበትን መረብ እየሳቡ በጀልባ መጡ ።
9 ከጀልባው በወረዱ ጊዜ ዓሣ በላዩ የነበረበት
የከሰል ፍምና እንጀራ አዩ ። 10 ኢየሱስም
"አሁን ካጠመዳችሁት ዓሣ አምጡ" አላ
ቸው ።
11 ስለዚህ ስምዖን ጴጥሮስ ወደ ጀልባው
ገብቶ መቶ ኀምሳ ሦስት ትልልቅ ዓሣዎች የሞ
ሉበትን መረብ ወደ ምድር ጐተተ ፤ ይህን
ያህል ብዙ ዓሣ ቢይዝም መረቡ አልተቀደ
ደም ። 12 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ "ኑ ብሉ" አላ
ቸው ። ጌታ ኢየሱስ መሆኑን ሁሉም አውቀው
ስለ ነበር ፥ ከደቀ መዛሙርቱ አንድ እንኳ
"አንተ ማን ነህ?" ብሎ ሊጠይቀው የደፈረ
አልነበረም ። 13 ኢየሱስ መጣ ፤ እንጀራውንና
እንዲሁም ዓሣውን አንሥቶ ሰጣቸው ።
14 ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ ወዲህ ደቀ መዛ
ሙርቱ ሲያዩት ይህ ሦስተኛ ጊዜ ነበር ።

### ኢየሱስና ጴጥሮስ

15 ከበሉ በኋላ ኢየሱስ ስምዖን ጴጥሮስን
"የዮሐንስ ልጅ ስምዖን ሆይ! እነዚህ ከሚወድ
ዱኝ ይበልጥ ትወድደኛለህን?" አለው ።
እርሱም "አዎ ጌታዬ ሆይ! እኔ እንደምወ
ድድህ አንተ ታውቃለህ" ሲል መለሰለት ።
16 ኢየሱስም "ግልገሎቼን መግብ" አለው ።
ሁለተኛ ጊዜም "የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ! ትወ
ድደኛለህን?" አለው ።
እርሱም "አዎ ጌታዬ ሆይ! እንደምወድድህ
ታውቃለህ" አለው ።
ኢየሱስም "ጠቦቶቼን ጠብቅ" አለው ።
17 ሦስተኛ ጊዜም "የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ!
ትወድደኛለህን?" አለው ።
ሦስተኛ ጊዜ "ትወድደኛለህን?" ስላለው
ጴጥሮስ አዘነና "ጌታ ሆይ! አንተ ሁሉን ታው
ቃለህ ፤ እኔ እንደምወድህም ታውቃለህ"
አለው ። ኢየሱስም እንዲህ አለው ፥ "በጎቼን
አሠማራ ፤ 18 እውነት ፤ እውነት እልሃለሁ ፥
አንተ ጐልማሳ ሳለህ ቀበቶህን በገዛ እጅህ ታጥ
ቀህ ወደ ፈለግህበት ትሄድ ነበር ፤ በሸመገልህ
ጊዜ ግን አንተ እጆችህን ትዘረጋና ሌላ ሰው
ያስታጥቅሃል ፤ ወደማትፈልግበትም ይወስድ
ሃል ።" 19 ይህንንም ያለው ጴጥሮስ በምን ዐይ
ነት ሞት እግዚአብሔርን ማክበር እንዳለበት
ሲያመለክት ነው ፤ ከዚህ በኋላ ጴጥሮስን "ተከ
ተለኝ" አለው ።

### ኢየሱስና ሌላው ደቀ መዝሙር

20 ጴጥሮስ ዞወር ብሎ ኢየሱስ የሚወድደው
ደቀ መዝሙር ሲከተለው አየ ፤ ይህ ደቀ መዝ
ሙር በራት ጊዜ ወደ ኢየሱስ ጀርባ ተጠግቶ
"ጌታ ሆይ! አሳልፎ የሚሰጥህ ማን ነው?"
ብሎ የጠየቀው ነው ። 21 ጴጥሮስ እርሱን አየና
"ጌታ ሆይ! ይህስ ሰው ምን ይሆናል?" ሲል
ኢየሱስን ጠየቀ ።
22 ኢየሱስም "እኔ እስክመጣ ድረስ እንዲ
ኖር ብፈቅድ አንተን ምን አገባህ? አንተ ተከተ
ለኝ" አለው ።
23 በዚህ ምክንያት በወንድሞች መካከል
"ይህ ደቀ መዝሙር አይሞትም" የሚል ወሬ
ተሰራጨ ፤ ነገር ግን ኢየሱስ "እኔ እስክመጣ
ድረስ እንዲኖር ብፈቅድ አንተ ምን አገባህ"
አለ እንጂ "አይሞትም" አላለም ። 24 ስለ እነ
ዚህ ነገሮች ሁሉ የመሰከረና እነዚህንም ነገሮች
የጻፈ ይህ ደቀ መዝሙር ነው ፤ የእርሱም ምስ
ክርነት እውነት እንደሆነ እናውቃለን ።
25 ኢየሱስ ያደረጋቸው ሌሎች ብዙ ነገሮች
ደግሞ አሉ ። እኔ እንደሚመስለኝ እርሱ ያደረ
ጋቸው ነገሮች ሁሉ አንድ በአንድ ቢጻፉ ኖሮ
የሚጻፉትን መጻሕፍት ዓለም ራሱ መሸከም
ባልቻለም ነበር ።

21፥6 ፦ ሉቃ. 5፥6 ።